አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የካፊቾ ብሔረሰብ የሴቶችና የወንዶች አለባበስና አጊያጊያጥ

## ገላጭ ጥናት

በ

አዜብ ወርቅነህ ፀጋ

ግንቦት ፣ 2006 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የካፊቾ ብሔረሰብ  የሴቶችና የወንዶች አለባበስና አጊያጊያጥ

## ገላጭ ጥናት

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን
ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድኅረ ምረቃ    መርሐ ግብር

የአርት ማስተርስ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ  ነጥቦች
ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት

በ
አዜብ ወርቅነህ ፀጋ

አማካሪ
ሰላማዊት መካ(ረ/ፕሮፌሰር)

ግንቦት ፤2006 ዓ.ም
አዲስ አበባ

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የካፊቾ ብሔረሰብ የሴቶችና የወንዶች አለባበስና አጊያጊያጥ ገላጭ ጥናት

በ

አዜብ ወርቅነህ ፀጋ

ግንቦት ፤2006 ዓ.ም

**የፈተና ቦርድ አባላት**

| | |
|---|---|
| የአማካሪ ስም | ፊርማ |
| ________________ | ________________ |
| የፈታኞች ስም | ፊርማ |
| የውስጥ ፈታኝ ________________ | ________________ |
| የውጭ ፈታኝ ________________ | ________________ |

# ምስጋና

ለዚህ ጥናት በርካታ ሰዎች እገዛ እንዳደረጉልኝ እሙን ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ይህንን ጥናት በማረም እና ምሁራዊ አስተያየታቸውን በመለገስ ለረዱኝ መምህሬና አማካሪዬ ወ/ሮ ሰላማዊት መካ በጣም አመሰግናለሁ፡፡

ይህንን የትምህርት እድል ለሰጠኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምስጋናዬ ይድረሰው፡፡ የተለያዩ የቁሳቁስ ድጋፎችን በማድረግ እና የሞራል ድጋፍ በመስጠት ለዚህ እንድበቃ ላደረጉኝ ቤተሰቦቼ እንዲሁም መረጃዎችን በመተርጎም ለረዳኝ ለአቶ ጀማል አብዱ እግዚአብሔር ውለታችሁን ይክፈልልኝ፡፡

የጥናቴን መረጃ ለመሰብሰብ በሄድኩበት ጊዜ ከጥሩ መስተንግዶ ጋር ለተቀበሉኝ ለበላይነሽ ተክሌ፣ ለየሻረግ ተክሌ እና ለካፋ ዞን ባህል ቱሪዝምና ኮሚዩኒኬሽን ሰራተኞች በሙሉ እንዲሁም ለመረጃ አቀባዮቼ በሙሉ በጣም አመሰግናችኋለሁ፡፡

# ማውጫ


ርዕስ ገጽ

ምስጋና……………………………………………………………………………I

ማውጫ……………………………………………………………………………II

የፎቶግራፍ ማውጫ………………………………………………………………V

የካፋ ዞን ካርታ…………………………………………………………………VII

አጠቃሎ…………………………………………………………………………VIII

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ ……………………………………………………………………1

1.1. የጥናቱ ዳራ ……………………………………………………………1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት…………………………………………………2

1.3. የጥናቱ አላማዎች…………………………………………………………3

1.3.1. የጥናቱ ዋና አላማ……………………………………………………3

1.3.2. የጥናቱ ዝርዝር አላማ…………………………………………………3

1.4. በጥናቱ የሚመለሱ ጥያቄዎች……………………………………………3

1.5. ጥናቱ የሚያስገኘው ጠቀሜታ……………………………………………4

1.6. የጥናቱ ወሰን……………………………………………………………4

1.7. የጥናቱ ዘዴዎች…………………………………………………………5

1.7.1. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ……………………………………………5

1.7.2. የመረጃ መመደቢያና መተንተኛ ዘዴ…………………………………6

1.8. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች………………………………6

1.9. የመስክ ቆይታ……………………………………………………………7

ምዕራፍ ሁለት

ክለሳ ድርሳን……………………………………………………………………9

2.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት…………………………………………………9

2.2. የንድፈ ሀሳቦች ቅኝት……………………………..…………………..….14

2.2.1. ቁሳዊ ባህል…………………………………………………...……14

2.2.1.1. የቁሳዊ ባህል መጠናት አስፈላጊነት……..…………...……16

2.2.1.2. የቁሳዊ ባህል ምደባ…………………..…………….....……18

2.2.1.3. የቁሳዊ ባህል የመተንተኛ ሞዴሎች…..……..……....……19

2.2.2. ሀገረሰባዊ አልባሳት…..………..………………………………..…20

2.2.2.1. ማንነትን መግለጽ………...…………………………...……21

2.2.2.2. ማህበራዊ ደረጃን መግለጽ...………………………………..….22

2.2.2.3. ሀይማኖታዊ ተግባር……………………………………..……23

2.2.3. ሀገረሰባዊ ጌጣጌጥ……………………………………..………………..23

## ምዕራፍ ሶስት

ጥናቱ የተደረገበት አካባቢ ገጽታና የማህበረሰቡ ዳራዊ መግለጫ……………..…………25

3.1. የካፋ ዞን ኢኮኖሚያዊ ገጽታ……………………………………………………….25

3.2. የካፋ ዞን የቡና መገኛ……………………...……………………………...…….27

3.3. የካፋ ነገስታት ታሪክ…………………...……………………………………..….28

3.4. የካፋ ጥንታዊ አልባሳትና ጌጣጌጥ………………………………………..……….30

3.5. የካፊቾ ብሔረሰብ ማህበረ-ባህላዊ ሁኔታ ………………..………………..31

3.5.1. የካፊቾ ብሔረሰብ የጋብቻ ሥነ-ስርዓት……………………………......….31

3.5.2. የካፊቾ ብሔረሰብ የለቅሶ ሥነ-ስርዓት……………………………...…..……34

3.5.3. የካፊቾ ብሔረሰብ የስራ ባህል………………………………………………38

## ምዕራፍ አራት

የካፊቾ ብሔረሰብ አልባሳትና ጌጣጌጥ……………………………………...…..………41

4.1. የካፊቾ ብሔረሰብ አልባሳት……………..………...………………………………41

4.1.1. የካፊቾ ሴቶች አልባሳት……………..…………..……………………………41

4.1.1.1. የልጃገረዶች ልብስ…...……………………….…………..……41

4.1.1.2. ያገቡ ሴቶች አልባሳት…………...………..……………………43

4.1.2. የካፊቾ ወንዶች አልባሳት………………………………..………..….50

4.1.2.1. የወጣት ወንዶች አልባሳት………..…………..…………………50

4.1.2.2. በዕድሜ የገፉ አባቶች አልባሳት……………………….……..54

4.2. የካፊቾ ብሔረሰብ ጌጣጌጥ……...………..…………………..……………57

4.2.1. የካፊቾ ብሔረሰብ ሴቶች ጌጣጌጥ………….………………...……58

4.2.2. የካፊቾ ብሔረሰብ ወንዶች ጌጣጌጥ……...………………………..….66

4.2.2.1. በአደን ጊዜ የሚደረጉ ጌጦች……………..…………………..….66

4.2.2.2. በስራ ጊዜ የሚደረጉ ጌጦች………….……………….………....68

4.2.3. የካፊቾ ብሔረሰብ ህጻናት ጌጣጌጥ…..…………………..……………70

4.3. የካፊቾ ብሔረሰብ ሴቶችና ወንዶች የፀጉር አቀራረጥ እና አሰራር..........…70

4.3.1. የሴቶች የፀጉር አቀራረጥና አሰራር…………………………………...…71

4.3.2. የወንዶች የፀጉር አቀራረጥ……..……………………………….……...…73

4.4. የአልባሳቱና የጌጣጌጦቹ የለውጥ ሁኔታና የማህበረሰቡ
አስተያየት...……………………………………………………………………..74

**ምዕራፍ አምስት**

ማጠቃለያና የይሁንታ ሀሳቦች………………………………………………..…..77

5.1. ማጠቃለያ…………………….………..………………………………..……77

5.2. የይሁንታ ሀሳቦች…………………..…………………………………………78

ዋቢ ጽሁፎች…..…………………………………..……………………………………80

አባሪ 1. ለመረጃ አቀባዮች የቀረቡ ጥያቄዎች

አባሪ 2. የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር

አባሪ 3. ግጥሞች

አባሪ 4. ፎቶግራፎች

# የፎቶግራፍ ማውጫ


**ፎቶግራፍ** **ገጽ**

ፎቶግራፍ 1. ኪቶ የለበሰች ልጃገረድ……………………………………………………43

ፎቶግራፍ 2. ገመኖ የለበሰች ወጣት…………………………………………………45

ፎቶግራፍ 3. ዋንደሮ የለበሰች እናት …………………………………………………46

ፎቶግራፍ 4. በእድሜ የገፉ እናቶች የሚለብሱት ዳዶ………………………………47

ፎቶግራፍ 5. ዮኮ የለበሰች ሴት ……………………………………………………48

ፎቶግራፍ 6. ሸቆ የለበሰች ሴት ……………………………………………………50

ፎቶግራፍ 7. በስራ ጊዜ የሚለበስ ሾሮ………………………………………………51

ፎቶግራፍ 8. ዱቦ የለበሰ ወጣት……………………………………………………52

ፎቶግራፍ 9. ጎፈር የለበሰ ወጣት…………………………………………………53

ፎቶግራፍ 10. ካፊ ቆጨ ኮቶ የለበሰ ወጣት…………………………………………54

ፎቶግራፍ 11. ሸናፊሎ…………………………………………………………………55

ፎቶግራፍ 12. በዳኝነት ጊዜ የሚለበስ ተነፋነፍ ………………………………………57

ፎቶግራፍ 13. ጊጆ ለመስራት የሚያገለግል ጨሌ ……………………………………59

ፎቶግራፍ 14. ብረዌ አሉቦ……………………………………………………………61

ፎቶግራፍ 15. ጊቦ አሉቦ………………………………………………………………61

ፎቶግራፍ 16. ጎሾ………………………………………………………………………62

ፎቶግራፍ 17. ጋፊዮ እና ጊሺሺ ጊጃሮ ………………………………………………64

ፎቶግራፍ 18. ቲፎ ያደረገች የአላሞ ሚስት……………………………………………………..65

ፎቶግራፍ 19. የሴቶች ቦርሳ (ደንገቿ ጌሾ)………………………………………………….66

ፎቶግራፍ 20. በአደን ጊዜ የሚያዙ ጌጦች…………………………………………………68

ፎቶግራፍ 21. ኡኮ……………………………...………………………………………69

ፎቶግራፍ 22. በራስ ላይ የሚደረግ ኦጎ……………………………………………………..70

ፎቶግራፍ 23. ዛጎሎ ያደረገች ህጻን……………...…………………………………………70

ፎቶግራፍ 24. ህጻናት የሚቆረጡት ጌፖ ……………………………...…………..71

ፎቶግራፍ 25.ጌንጎ……………………………………………………………………………73

ፎቶግራፍ 26. ዲጾ……………………………………………………………………………73

# የካፋ ዞን ካርታ




## የካርታ ማውጫ

1. ጋዋቲ/Gawaatti
2. ጊምቢ/Gimbi
3. አዲዮ/Addiyi
4. ጠሎ/Xalli
5. ጨቲ/Catti
6. ዴጪ/Deechi
7. ጪኒ/Canni
8. ጊሺ ጌሺ/Giishi Geshi(Bixxi)
9. ጌሺ/Geeshi
10. ሳይለም/Saaylemi

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት ሲዘጋጅ የካፊቾ ብሄረሰብ የሴቶችና የወንዶች የአለባበስና አጊያጊያጥ ባህሎችን በመመርመር ልብሶቹና ጌጣጌጦቹ እንዲሁም የፀጉር አሰራር አይነቶቹ በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸውን ማህበራዊ ፋይዳ ማሳየት እንዲሁም ሰንዶ ማኖርን አላማው አድርጎ ነው፡፡ አላማው ከግብ እንዲደርስ ለማድረግም ቁሶቹን፣ የቁሶችን አሰራር፣ የቁሶችን ተግባርና በቁሶቹና በማህበረሰቡ መካከል ያለውን ግንኙነት፣ የተደረገባቸውን ለውጥ አጉልተው ሊያሳዩ የሚችሉ ዝርዝር አላማዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

ይህ ጥናት የካፊቾ ብሄረሰብ አልባሳት፣ ጌጣጌጦችና የፀጉር አሰራር አይነቶች ምን ምን እንደሆኑ፣ የእነዚህ ቁሶች ቁሳዊ ገጽታ ምን እንደሚመስል፣ ማህበረ-ባህላዊ ፋይዳቸው ምን እንደሆነ እና በቁሶቹ ላይ እየተካሄደ ያለውን ለውጥና ምክንያቱ ምንድን ነው? የሚሉ ጥያቄዎችን የሚመልስ ነው፡፡ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች በምልከታ፣ በቃለመጠይቅና በተተኳሪ ቡድን ውይይት አማካኝነት ተሰብስበዋል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎች ገላጭ የምርምር ዘዴን በመጠቀም የተተነተኑ ሲሆን የተሰበሰቡት ግጥሞች ደግሞ የይዘት ትንተና ተደርጎባቸዋል፡፡ ለትንታኔው ማስኬጃነት 9ኙ የSchlereth ሞዴሎች አገልግለዋል፡፡ እነዚህን ዘዴዎች መሰረት ተደርጎ የተተነተኑት መረጃዎች የሚከተሉትን ውጤቶች አስገኝተዋል፡፡

በአጠቃላይ ይህ ጥናት ከተከናወነ በኋላ በካፊቾ ብሔረሰብ 12 አልባሳት፣ 19 ጌጣጌጦች እንዲሁም 4 የፀጉር አሰራር አይነቶች እንዳሉ ለማወቅ ተችሏል፡፡ እነዚህም አልባሳት ከጥጥ፣ የፋብሪካ ውጤቶች ከሆኑ ጨርቆች፣ ከቃጫና ከቆዳ የሚዘጋጁ ናቸው፡፡ ማጌጫዎቹ ከሚውሉበት የሰውነት ክፍል አንፃር ተከፍለው የተቀመጡ ናቸው፡፡ የፀጉር አሰራሮቹ ደግሞ የህፃናት፣ የወጣቶች፣ ያላገቡና ያገቡ ተብለው ተቀምጠዋል፡፡ እነዚህም ጌጣጌጦች ከጨሌ፣ ከብር፣ ከመዳብ፣ ከዝሆን ጥርስ፣ ከብረታ ብረት፣ ከቆዳ፣ ወዘተ. የሚዘጋጁ መሆናቸው ታውቋል፡፡

ቁሶቹ ከመለበስ ወይም ከማስጌጥ ባለፈ የብሔረሰቡን ማንነት፣ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታና ማህበራዊ ደረጃዎችን የሚያመላክቱ ናቸው፡፡ ነገር ግን እነዚህ ቁሶች በተለያዩ ሁኔታዎች ምክንያት በመሰሪያ ቁሳቸው፣ በቅርጻቸው፣ በመደረጊያ አጋጣሚያቸው እና በቁጥራቸው ላይ ለውጥ እየተደረገባቸው እንደሚገኝ ጥናቱ ያመለክታል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

በዚህ ጥናት ውስጥ የሚገኘው የመጀመሪያው ምዕራፍ ዘጠኝ ርዕሰ ጉዳዮችን አካትቶ ቀርቧል፡፡ እነዚህም የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች፣ የጥናቱ ዓላማዎች፣ በጥናቱ የሚመለሱ ጥያቄዎች፣ ጥናቱ የሚያስገኘው ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የጥናቱ ዘዴዎች፣ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች እንዲሁም የመስክ ቆይታ የሚሉት ናቸው፡፡

በአልባሳትና ጌጣጌጦች ላይ የተሰሩ የመመረቂያ ጽሁፎችና ንድፈ ሀሳቦች የተዳሰሱበት ሌላው የጥናቱ አካል ምዕራፍ ሁለት ነው፡፡ በቅድሚያ የተዳሰሱት የመመረቂያ ጽሁፎች ሲሆኑ ዳሰሳውም ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የተሰሩትን ጥናቶች ቀዳሚ፣ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡትን ጥናቶች ደግሞ ተከታይ በማድረግ ተካሂዷል፡፡ ከዚያም የመስኩ ምሁራን በጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ያቀረቧቸው ንድፈ ሀሳቦች ተቃኝተዋል፡፡

ሶስተኛው ምዕራፍ ደግሞ ጥናቱ ስለተካሄደበት አካባቢ ገጽታና ስለ ማህበረሰቡ ዳራዊ መግለጫ የተሰጠበት ክፍል ነው፡፡ በዚህም ስር ከማህበረሰቡ፣ ከመጻሕፍትና ከመጽሄቶች የተገኙትን ወረጃዎች መሰረት በማድረግ የዞኑ አጠቃላይ ገጽታ፣ የብሔረሰቡ ማህበረ-ባህላዊ ሁኔታ ምን እንደሚመስል ተቃኝቷል፡፡

አራተኛው ምዕራፍ ደግሞ ጥናቱ በተካሄደበት አካባቢ ያሉ ሴቶችና ወንዶች የሚጠቀሙባቸው ሀገረሰባዊ አልባሳትና ጌጣጌጦች ምን ምን እንደሆኑ፣ ምን አይነት ማህበራዊ ፋይዳና ትርጓሜ እንዳላቸው ትንተና የተካሄደበት ነው፡፡ በተጨማሪም ስለ አልባሳቱና ጌጣጌጦቹ የተባሉ ስነ-ቃሎችን ከአልባሳቱና ጌጣጌጦቹ ጋር በማዋሀድ አውዳዊ ትንታኔ ተደርጓል፡፡ በስተመጨረሻም ለአልባሳቱና ጌጣጌጦቹ መለወጥና መጥፋት ምክንያት ናቸው ተብለው የሚነሱ ጉዳዮች፣ ማጠቃለያ (በማጠቃለያው ውስጥ በጥናቱ የተደረሰባቸው ግኝቶች) እና የይሁንታ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

የሰው ልጅ በዕለት ተዕለት ኑሮው ከሚጠቀምባቸው ቁሳቁሶች መሀከል አልባሳት በመሰረታዊ ፍላጎትነት ከሚመደቡት ውስጥ የሚካተቱ ናቸው፡፡ አልባሳት ከቁሳዊ

ፋይዳቸው ባሻገር የማህበረሰቡን ማንነት፣ እደ ጥበብ፣ ስነ-ውበታዊ ፍላጎቶች በመግለጽ እንዲሁም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃን በመግለጽ ረገድ ከፍተኛ ድርሻ አላቸው፡፡ ቁሶቹ ይህን ተግባር እንዲጎናጸፉ ያደረጋቸው በሀገረሰባዊ አልባሳትና በተጠቃሚው ማህበረሰብ መካከል የሚኖረው ትስስርና መስተጋብር ነው፡፡ ስለዚህም አንድ የማህበረሰብ አባል ከለበሰው ልብስ እና ካደገረው ጌጣጌጥ ተነስተን ማንነቱን እና ምንነቱን መገመት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በአልባሳቱ ተጠቃሚና በተመልካቹ መካከል ተግባቦትን ይፈጥራሉ፡፡

ሀገረሰባዊ አልባሳትን ስናነሳ ተያይዘው የሚመጡ ሌሎች ቁሳዊ ባህሎች አሉ፡፡ እነዚህም ጌጣጌጦች ናቸው፡፡ ጌጣጌጦች ማህበረሰቡን በመግለጽ ረገድ የራሳቸው የሆነ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ እነዚህን ሁሉ ማህበራዊና ባህላዊ ፋይዳዎች የያዙ ቁሶች ደግሞ መጠናት አለባቸው፡፡ ምክንያቱም አሁን ባለንበት ሁኔታ አልባሳቱ በዘመናዊ አልባሳት እየተተኩ እና እየጠፉ ስለሚገኙ ቢያንስ ለተተኪው ትውልድ በጽሁፍ ሰንዶ ማስቀመጥ ስለሚገባ ነው፡፡ በነዚህ ቁሶች ላይ ጥናት መደረጉ ከመሰነድ ባሻገር ማህበረሰቡ ስለ ባህሉ ጠለቅ ብሎ እንዲያውቅና ቁሶቹን ለመጠበቅም እንዲነሳሳ ሞራል ይፈጥራል፡፡

አልባሳትንና ጌጣጌጦችን በተመለከተ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በመጀመሪያ ዲግሪና በሁለተኛ ዲግሪ ተማሪዎች አማካኝነት የተወሰኑ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ ጥናቶቹ የተደረጉበት አካባቢ በጣም ጥቂት ከመሆኑም ባሻገር እስካሁን የተደረጉ ጥናቶች በቁሶቹ ላይ ትንታኔ ሲያካሂዱ "ለትንታኔ የተመረጡ ቁሶች" ከሚል መግለጫ ጋር አስደግፈው የሚተነትኑት የተወሰኑ ቁሶችን በመምረጥ ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህ ጥናቶች በቂም ሙሉም አይደሉም፡፡ ይህ ጥናት በተደረገበት የካፊቾ ብሔረሰብ ላይም እነዚህን ቁሶች በተመለከተ ምንም ጥናት አልተካሔደም፡፡ የጥናቱን አካባቢ የመረጥኩትም ጥናት እንዳልተደረገበት ካረጋገጥኩ በኋላ ነው፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የቁሳዊ ባህል ጥናት የአንድ አካባቢ ማህበረሰቦች የሰሯቸውን የእጅ ስራ ውጤቶች እና ከስራዎቹ ጋር ተያይዘው የሚመጡ ባህላዊ ጉዳዮች ላይ በመመስረት ስለማህበረሰቡ ለሚነሱ ጥያቄዎች ምርምራዊ ምላሽ የሚሰጥበት መስክ ነው፡፡ ስለሆነም ቁሳዊ ባህልን በማጥናት የሰው ልጅን አስተሳሰብ፣ እምነት፣ የአካባቢውን ማህበረሰብ ባህል፣ የፈጠራ ችሎታ፣ የአኗኗር ዘይቤና  የእርስ  በርስ ግንኙነት መረዳት ይቻላል የሚል እምነት

አለኝ፡፡ ይህን ጥናት ለማድረግ የተነሳሁትም በዚህ ምክንያት ሲሆን በተጨማሪም የማህበረሰቡ አለባበስ እና አጊያጊያጥ በተወሰነ መልኩ እየጠፋ ያለ በመሆኑ ለመሰነድ፣ ከሚደረጉበት ሁኔታና ጊዜ እንዲሁም ከሚለብሱት ሰዎች አንጻር ማህበረሰቡ ለልብሶቹም ሆነ ለጌጣጌጦቹ የሚሰጠውን ትርጓሜ የመፈተሽ ጉጉቴና በትምህርት ክፍሉ በማህበረሰቡ ዙሪያ የተሰሩ አጥጋቢ ጥናቶች ባለማየቴ ክፍተቱን ለመሙላት በማሰብ ነው፡፡

## 1.3. የጥናቱ አላማዎች

### 1.3.1. የጥናቱ ዋና አላማ

የጥናቱ ዋና አላማ የካፊቾ ብሄረሰብ የሴቶችና የወንዶች የአለባበስና አጊያጊያጥ ባህሎችን በመመርመር ልብሶቹና ጌጣጌጦቹ እንዲሁም የፀጉር አሰራር አይነቶቹ በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸውን ማህበራዊ ፋይዳ ማሳየት እንዲሁም ሰንዶ ማኖር ነው፡፡

### 1.3.2. የጥናቱ ዝርዝር አላማ

- የአልባሳቱንና የጌጣጌጦቹን ምንነትና የመሰሪያ ቁሳቁስ መግለፅ እንዲሁም የሚታይ ለውጥ ካለ የለውጡን ሁኔታ ከማህበረሰቡ አስተያየት ጋር ማቅረብ፤
- አልባሳቱና ጌጣጌጦቹ በምን መልኩ፣ መቼና በማን እንደሚደረጉ መግለፅ፤
- የአልባሳቱና የጌጣጌጦቹ እንዲሁም የፀጉር አሰራር አይነቶቹን ከተጠቃሚዎቻቸው (ከአድራጊዎቻቸው) አንፃር ማህበረሰቡ የሚሰጠውን ትርጓሜ ማቅረብ፤
- ከአለባበስና አጊያጊያጥ ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ስነ-ቃሎችን መሰብሰብና ተግባራቸውን ማሳየት የሚሉት ናቸው፡፡

## 1.4. በጥናቱ የሚመለሱ ጥያቄዎች

ይህ ጥናት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል፡፡

- የካፊቾ ብሄረሰብ አልባሳት፣ ጌጣጌጦችና የፀጉር አሰራር አይነቶች ምን ምን ናቸው?
- የእነዚህ ቁሶች ቁሳዊ ገጽታ ምን ይመስላል?
- የአልባሳቱ፣ የጌጣጌጦቹና የፀጉር አሰራሮቹ ማህበረ-ባህላዊ ፋይዳዎች ምንድን ናቸው?

❖ በቁሳዊ ባህሎቹ ላይ በጊዜ ሂደት የመው ለውጥ ምን አይነት ነው? ለለውጡ በምን ምክንያትነት የሚነሳው ጉዳይ ምንድን ነው?

## 1.5. ጥናቱ የሚያስገኘው ጠቀሜታ

ሀገረሰባዊ አልባሳቱና ጌጣጌጦቹ የማህበረሰቡ ውጤቶች በመሆናቸው ከማህበረሰቡ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊና ማህበራዊ ህይወት ጋር ያላቸው ትስስር ከፍተኛ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት መደረጉ የአካባቢውን ቁሳዊ ባህል በፅሁፍ ቀርሶ ለቀጣዩ ትውልድ በማስተላለፍ ረገድ አስተዋፅኦ የሚያበረክት ሲሆን በተጨማሪም ስለ አካባቢው ቁሳዊ ባህል ለማሳወቅ ይጠቅማል፤ በካፊቾ ብሄረሰብ ላይም ሆነ በአለባበስና አጊያጊያጥ ላይ ወደፊት ጥናት ለሚያካሂዱ አካላት ለመነሻ ሀሳብ የሚሆን መረጃ ይሰጣል፤ በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ በካፊቾ ብሔረሰብ ላይ ጥናት ባለመደረጉ ያለውን ክፍተት በመሙላት ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በቁሳዊ ባህል ዘርፍ ከሚካተቱት ውስጥ በሀገረሰባዊ አልባሳትና ጌጣጌጦች ላይ ብቻ የተገደበ ነው፡፡ ከቦታ አንጻር ደግሞ በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ስር የሚገኘው የካፋ ዞን ርዕሰ ከተማ በሆነችው ቦንጋ ከተማ እንዲሁም በዙሪያዋ በሚገኙት የአዲዮ ወረዳ (ኦቤራ ቀበሌ) እና የጠሎ ወረዳ (ኮባ ቀበሌ) ላይ ያተኮረ ነው፡፡

እነዚህ አካባቢዎች ለጥናቱ የተመረጡበት ምክንያት ኦቤራና ኮባ ቀበሌዎች አልባሳቱና ጌጣጌጦቹ በብዛት የሚገኙባቸው በመሆናቸውና በቦንጋ ከተማ ደግሞ አልባሳቱ በብዛት ጥቅም ላይ የማይውልበት ቦታ በመሆኑ ጥናቱን ከሁለቱም ወገን ለማየት የሚረዱ በመሆናቸው ነው፡፡ ስለዚህም በዚህ ጥናት የተዳሰሰው በካፋ ዞን ውስጥ ከሚገኙት ሶስት ብሔረሰቦች መካከል የካፊቾ ብሔረሰብ ብቻ ነው፡፡ በጥናቱ የብሔረሰቡ አለባበስና አጊያጊያጥ በጥልቀት የታየ ሲሆን ባለሙያዎቹን በቀላሉ ማግኘት ባለመቻሉና ለባለሙያዎቹም የተለየ እይታ ባለመኖሩ የባለሙያዎቹ ህይወት አልተዳሰሰም፡፡

## 1.7. የጥናቱ ዘዴዎች

### 1.7.1.የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ቀዳማይ እና ካልዓይ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅሜያለሁ፡፡ ከማህበረሰቡ ያገኘሁት መረጃ ቀዳማይ ሲሆን ሌሎች የተጠቀምኩባቸው መጻሕፍት ደግሞ ካልዓይ ምንጮቼ ሆነው አገልግለዋል፡፡ ከቀዳማይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ውስጥ ምልከታ፣ ቃለመጠይቅ እና ተተኳሪ የቡድን ውይይት ከመስክ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በዋናነት ተመራጭ ዘዴዎች እንደሆኑ Goldstein (1964፣77-104) ይገልፃሉ፡፡ ፈቃደም (1991፣90) እንደዚሁ መረጃን በምልከታና በቃለመጠይቅ መሰብሰብ እንደሚቻል ይመክራሉ፡፡ ለዚህ ጥናትም መረጃዎች በምልከታና በቃለመጠይቅ የተሰበሰቡ ሲሆን በተጨማሪም በተተኳሪ የቡድን ውይይት መረጃ ተሰብስቧል፡፡ እነዚህን ዘዴዎች በተከተለ መልኩ መረጃዎች በመቅረፀ ድምጽ፣ በፎቶ ግራፍ እና በቪዲዮ ተሰንደዋል፡፡

በምልከታ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተፈጥሯዊ መቼት፣ አርቴፊሻል መቼት እና ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት መጠቀም ይቻላል፡፡ በዚህ ጥናትም መረጃዎች በተፈጥሯዊ መቼት የተሰበሰቡ ሲሆን በተፈጥሯዊ መቼት ለማግኘት ያልተቻሉ መረጃዎችን ለማሳየት ደግሞ የብሔረሰቡን ባህል በሚያሳይ መልኩ ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት ተዘጋጅቷል፡፡

ቃለመጠይቅ ለምናካሂደው ምርምር መረጃን ለመሰብሰብ አይነተኛ መሳሪያ ነው፡፡ በዚህ ጥናትም ቃለመጠይቅ ለመረጃ መሰብሰቢያነት ያገለገለ ሲሆን ቃለመጠይቅ የተደረገላቸው ሰዎች በዓላማ ተኮር ናሙና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ በዚህም መሰረት ጾታንና እድሜን ባገናዘበ መልኩ 15 ሴቶችና 17 ወንዶች በአጠቃላይ 32 መረጃ አቀባዮች ተመርጠው መረጃ እንዲሰጡ ተደርገዋል፡፡

ተተኳሪ የቡድን ውይይት ከተለያዩ መረጃ ሰጪዎች የተገኙ መረጃዎች የተለያየ አይነት አቅጣጫ በመያዝ ጥናቱን የተዛባ እንዳያደርጉት ለመጠበቅ ይጠቅማል፡፡ በዚህም መሰረት ለዚህ ጥናት ተተኳሪ የቡድን ውይይት የተደረገው መረጃ ሰጪዎችን በሶስት ቡድን እንዲደራጁ በማድረግ ሲሆን የመጀመሪያው ቡድን 3 ሴቶችንና 3 ወንዶችን በአጠቃላይ 6 የሀገር ሽማግሌዎችን ያቀፈ ሲሆን የሁለተኛው ቡድን ደግሞ 2 ሴቶችንና 4 ወንዶችን በአጠቃላይ 6 ወጣቶችን የያዘ ነው፡፡ ሶስተኛው ቡድን 3 የሀገር ሽማግሌዎችን፣ 2

ወጣቶችንና 2 ታዳጊዎችን ያካተተ ነው፡፡ የመጀመሪያዎቹ እና ሁለተኛዎቹ ቡድኖች የተወያዩት ስለ አልባሳቱና ጌጣጌጦቹ ሲሆን በሶስተኛው ቡድን ያሉት ደግሞ ስለ ማህበረሰቡ ማህበራዊ ሁኔታ በመወያየት መረጃ ሰጥተዋል፡፡ እነዚህም ውይይቶች በተለያየ ቦታና ሰዓት የተካሔዱ ናቸው፡፡

### 1.7.2. የመረጃ መመደቢያና መተንተኛ ዘዴ

መረጃው ከተሰበሰበ በኋላ የምሁራኑን ትውሮችና የአካባቢውን ማህበረሰብ ገለፃ መሰረት በማድረግ አልባሳቱንና ጌጣጌጦችን በምድብ መከፋፈል ቀዳሚው ሂደት ነው፡፡ በዚህም መሰረት አልባሳቱን ማህበራዊ ደረጃን መሰረት በማድረግ (የወንድ፣ የሴት፣ የልጃገረድ፣ ያገባች፣ የወጣቶች፣ የአባቶች፣ ወዘተ.) ጌጣጌጦችን ደግሞ ከሚውሉበት ቦታ አንጻር (የጆሮ፣ የአንገት፣ የእጅ፣ የእግር፣ የወገብ ወዘተ.) በማለትና የፀጉር አሰራር አይነቶችንም ከፆታ አኳያ ከፋፍዬ ተመልክቻለሁ፡፡ ከምደባው በኋላ የገለፃ ዘዴን በመጠቀም የካፊቾ ብሄረሰብ አለባበስና አጊያጊያጥ ተተንትኗል፤ ግጥሞቹም የይዘት ትንተና ተደርጎባቸዋል፤ ከአለባበሱ ጋር የተያያዙ ማህበራዊ እሴቶች ተገልጸዋል፤ ፎቶግራፎች መግለጫ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

በዚህ ጥናት የSchlereth 9 ሞዴሎች ለትንታኔ ማስኬጃነት አገልግለዋል፡፡ ሞዴሎቹም የባህላዊ ቁስን ጥበብ ታሪካዊነት፣ ባህላዊነት፣ አካባቢያዊነት፣ አገልግሎት፣ መዋቅራዊነት፣ ባህርይ አመልካችነት፣ ተምሳሌታዊነት፣ ማህበረሰባዊነትና ማህበረሰባዊ ታሪካዊነትን የትኩረት አቅጣጫ ያደረጉ ናቸው፡፡ በተጨማሪም prown (1982፣7-10) ካስቀመጧቸው 3 የመተንተኛ ሂደቶች መካከል ገለጻን በመጠቀም መረጃዎችን ተንትኛለሁ፡፡ የግጥሞቹን ተግባር ለማሳየት ደግሞ የይዘት ትንተና ተጠቅሚያለሁ፡፡

## 1.8. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች

በመስክ ቆይታዬ ወቅት ያጋጠሙኝ ችግሮች ቀላል የሚባሉ አይደሉም፡፡ ከነዚህም መካከል በመጀመሪያ ደረጃ የሚቀመጠው ለጥናቴ መረጃ ሊሰጡ ይችላሉ ብዬ የመረጥኳቸውን መረጃ ሰጪዎች በቀላሉ ማግኘት አለመቻሌ ነው፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ አንዳንድ መረጃ አቀባዮች ገንዘብ እንድከፍላቸው መጠየቃቸው ሌላው ችግር ነበር፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ አካባቢዎች መረጃ ለመሰብሰብ በምንቀሳቀስበት ወቅት የመሬቱ አቀማመጥ

ዳገታማ በመሆኑ በምፈልገው አካባቢ በቀላሉ ተመላልሼ መረጃዎቼን መሰብሰብ ለኔ ፈተና ነበር፡፡

ምንም እንኳን በጊዜው ያጋጠሙኝ ችግሮች ቀላል የሚባሉ ባይሆኑም ያስቸገሩኝን መረጃ ሰጪዎች ከአካባቢው ነዋሪዎች እርዳታ በመጠየቅና እንዲያናግሩልኝ በማድረግ የመጀመሪያውን ችግር ለማስወገድና መረጃ ለማግኘት ችያለሁ፡፡ በወቅቱ ከነበረው ጠንካራ ፀሀይ ጋር ተዳምሮ በጣም ከባድ የነበረውን ዳገታማ መሬት በእግዚአብሄር ረዳትነት ልቋቋመውና መረጃዬን ልሰበስብ ችያለሁ፡፡

## 1.9. የመስክ ቆይታ

ለጥናት የመረጥኩትን አካባቢ ከዚህ በፊት የማላውቀው ቦታ በመሆኑ ስለአካባቢው ለማወቅ ወደ መስክ ከመውጣቴ በፊት ብዙ ጥረቶችን አድርጌያለሁ፡፡ ለዚህም የአካባቢው ተወላጅ የሆኑ ጓዋደኞቼንና በጓደኞቼ በኩል ያወቅኳቸውን ሰዎች በስልክ እና በአካል አነጋግሬያለሁ፡፡ በተለይም ከርዕስ መረጣው ጀምሮ በመስክ ቆይታዩ ማድረግ ስላሉብኝ አንዳንድ ጉዳዮች ቅድመ መረጃ በመስጠት አቶ ጀማል አብዱ እና አቶ ወርቃገኘሁ ካሳ ከፍተኛ ትብብር አድርገውልኛል፡፡ በተጨማሪም በአካባቢው ዙሪያ የተጻፉ መጽሐፍትን በማንበብ ስለ አካባቢው ፍንጭ አግኝቻለሁ፡፡ ወደ መስክ ከማምራቴ በፊትም ጽሁፋዊ መረጃዎችን አጠናክሬ ለመነሻ የሚሆኑ ጥያቄዎችን አሰናድቻለሁ፡፡

በመቀጠልም ከትምህርት ክፍሉ ደብዳቤ በማስጻፍ የመጀመሪያውን የመስክ ጉዞዬን ታህሳስ 27 ቀን 2006 ዓ.ም አደረግኩ፡፡ በጥናቱ አካባቢ እንደደረስኩም በጓደኛዬ ቤተሰብ ቤት ያረፍኩ ሲሆን ሰኞ ታህሳስ 28 ወደ ዞኑ ባህል፣ ቱሪዝምና ኮሚዩኒኬሽን ቢሮ በመሄድ የያዝኩትን ደብዳቤ አስገብቼ አላማየን እና አጠቃላይ ስለጥናቴ ለቢሮ ሰራተኞች በማስረዳት ይሁንታን አገኘሁ፡፡ ለጥናቴ የሚረዱኝን አካባቢዎችም መረጥን፡፡ በቀጣዮቹ ቀናትም ወደተመረጡት ቦታዎች (ጠሎ እና አዲዮ) ወረዳዎች በመሄድ ስለ ባህሉ ያውቃሉ የተባሉ ሰዎችን ቃለመጠይቅ አድርጌ ወዳረፍኩባት የዞኑ ከተማ ቦንጋ ተመለስኩ፡፡

ከተመረጡት ሶስት ቦታዎች ውስጥ አንዷ ቦንጋ ከተማ በመሆኗ በዚህች ከተማ ውስጥ የሚገኙ የባህል አዋቂዎችን በአቶ ጀማልና ቤተሰቦቹ፣ በአካባቢው ነዋሪዎች እና በባህልና ቱሪዝም ሰራተኞች ረዳትነት የናሙና ዘዴየን ተጠቅሜ መርጫለሁ፡፡ ከዛም ወደተመረጡት

ግለሰቦች ቤትና የስራ ቦታ በመሄድ መረጃየን ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡ ቃለመጠይቁን ለማድረግ በተዘዋወርኩባቸው ቦታዎችና ምልከታ ለማካሄድ በተገኘሁባቸው የካፋ (የሸግግር) ሙዚየም፣ የገበያ ቦታዎችና ወዘተ. የተለያዩ ሁኔታዎችን ለመገንዘብና ለመታዘብ ችያለሁ፡፡

ባደረግኳቸው ቃለመጠይቆች ጥሩ የሆነ ማብራሪያ ባገኝም ሁሉንም አልባሳትና ጌጣጌጦች እንዲሁም የፀጉር አሰራር አይነቶች በተፈጥሯዊ መቼታቸው ማግኘት አልቻልኩም፡፡ የሄድኩበት ወቅት የገና እና የጥምቀት በዓላት የሚከበሩበት ጊዜ በመሆኑ የካፋን የገና እና የጥምቀት በዓላት አከባበር ለመታደምና በበዓላት ጊዜ የሚለበሱ አልባሳትን በተፈጥሯዊ መቼታቸው ለማግኘት ችያለሁ፡፡ ያላገኘኋቸውን ደግሞ በካፋ ዞን ባህላዊ የሙዚቃ ቡድን አባላት እና በአቶ መሰረት ረዳትነት አርቴፊሻል ተፈጥሯዊ መቼት አዘጋጅቻለሁ፡፡

ከላይ በተጠቀሰው መልኩ እስከ ጥር 20 ቀን 2006 ዓ.ም ድረስ መረጃዎቼን ካሰባሰብኩ በኋላ በ23ተኛ ቀኔ ወደ አዲስ አበባ በመመለስ በድምጽ የተቀረጹ ቃለመጠይቆችንና የተተኳሪ ቡድን ውይይቶችን ወደ ጽሁፍ ቀይሬያለሁ፣ ፎቶ ግራፎችንም አሳትሚያለሁ፡፡ በማስታወሻ እና በድምጽ የተሰበሰቡ መረጃዎችንም በማናበብ ጽፌያቸዋለሁ፡፡

በመጀመሪያ የሄድኩበት ወቅት በጋ በመሆኑ የክረምት ልብሶችንና በሰርግ ጊዜ የሚለበሱ ልብሶችን ማግኘት ባለመቻሌ ተመልሼ ወደ ጥናት ቦታየ ለመሄድ ችያለሁ፡፡ በዚህም መሰረት ሚያዝያ 9 ቀን 2006 ዓ.ም በድጋሚ ወደ ካፋ ሄጄ መረጃዎችን በመሰብሰብ ሚያዝያ 23 ቀን 2006 ዓ.ም በ15ኛ ቀኔ ወደ አዲስ አበባ ተመልሻለሁ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳን

በዚህ ክፍል ሁለት ጉዳዮች የሚነሱ ሲሆን በመጀመሪያው ንዑስ ርዕስ ከጥናቱ ጋር በተወሰነ መልኩ ተያያዥነት ያላቸው ቀደምት ጥናታዊ ጽሁፎች ተቃኝተዋል፡፡ በቀጣዩ ንዑስ ርዕስ ደግሞ ስለ ቁሳዊ ባህል፣ ስለ አልባሳትና ጌጣጌጥ የመስኩ ምሁራን የሰነዘሯቸው ትውራዊ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

### 2.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ከእኔ የጥናት ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ጥናታዊ ጽሁፎች ያነሱት መሰረታዊ ጉዳይ ይጠቀሳል፡፡ ከጥናቴ ጋር ያላቸው ተመሳስሎና ልዩነትም ይገለጻል፡፡ የእኔ ጥናት የሞላቸው ክፍተቶችም የሚጠቆሙ ይሆናል፡፡

ይህ ክፍል የሚያተኩረው ለአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል በቀረቡት አምስት የሁለተኛ ዲግሪ ጥናቶች እና ሁለት የመጀመሪያ ዲግሪ ጥናቶች ላይ ነው፡፡ የሁለተኛ ዲግሪ ጥናቶች በአመልማል ተሻለ (2004)፣ አፀደ ያረጋል (2003)፣ ሰይድ ይማም (2002)፣ ያሬድ ተፈራ (2002) እና በየኔአለም አረዶ (2000) የተሰሩ ሲሆን የመጀመሪያ ዲግሪ ጥናቶች ደግሞ በአያል አድማሱ (1992) እና በውብሸት አስፋው (1972) ተሰርተዋል፡፡ እነዚህ ጥናቶች በተወሰነ መልኩ በሚያነሷቸው ርዕሰ ጉዳዮች ከኔ ጥናት ጋር የሚቀራረቡ ሲሆን ለጥናት የተመረጠውን የካፊቾን ማህበረሰብ በማጥናታቸው ደግሞ የያዕቆብ ወ/ማሪያም (1974) “የካፊኛ ተረታ ተረቶች” እና የደምሴ በቀለ (1965) “የካፊኛ ተረትና ምሳሌዎች” የሚሉት ጥናቶች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ነገር ግን የሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ ከኔ ጥናት ጋር የማይዛመድ በመሆኑ አልመለከታቸውም፡፡

ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ ከተሰሩትና ከኔ ጥናት ጋር ከሚቀራረቡት መካከል “በባንጃ ወረዳና አካባቢዋ የአዊ ብሄረሰብ አለባበስና ጌጣጌጦች ገላጭ-ጥናት” በሚል ርዕስ የተደረገው የአመልማል ተሻለ (2004) ጥናት አንዱ ነው፡፡ የጥናቱ ዋና አላማ በአዊ ብሔረሰብ ባንጃ ወረዳና አካባቢዋ ያሉትን አለባበስና አጊያጊያጥ ውክልናቸውን መመርመር፣ መሰነድ፣ መግለጽና ማሳየት የሚል ነው፡፡ በዚህም መሰረት በተመረጠው አካባቢ የሚገኙ አልባሳትና

ጌጣጌጦችን የአሰራር ሒደት፣ ተግባር፣ ትርጓሜና የመደረጊያ (የመለበሻ) ወቅት በዝርዝር ገልጻለች፡፡ በተመረጠው አካባቢ የሚገኙ ወጣቶች፣ እናቶችና አባቶች የሚለብሷቸው ልብሶችና ጌጣጌጦች ከማህበረሰቡ ማንነት ጋር ያላቸውን ቁርኝት እንዲሁም የጸጉር አሰራርና ውቅራትን በተመለከተ ትንተና ሰጥታለች፡፡ ትንተና የተካሔደባቸው ለትንተና የተመረጡ የተባሉት 10 አልባሳት፣ ስድስት ጌጣጌጦችና ሶስት የፀጉር አሰራር አይነቶች ናቸው፡፡ ምልከታ ቃለመጠይቅና ተተኳሪ የቡድን ውይይት መረጃ መሰብሰቢያ መንገዶቿ ሲሆኑ ትንታኔዋን ደግሞ ገላጭ የምርምር ዘዴን በመጠቀም አካሂዳለች፡፡

የአመልማል ጥናት በአለባበስና አጊያጊያጥ እንዲሁም የፀጉር አሰራር ላይ ማተኮሩ ከኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡ የእኔ ጥናት ሥነ-ቃሎችን መሰብሰብ እና ተግባራቸውን ማሳየት አንዱ አላማው በመሆኑ ደግሞ ከአመልማል ጥናት ይለያል፡፡

ሌላው የሁለተኛ ዲግሪ ጥናት በአፀደ ያረጋል (2003) የተካሄደው "የኮንሶ ሃገረሰባዊ አልባሳት እና ጌጣጌጦች፡- ገላጭ- ተንታኝ ጥናት" የሚለው ነው፡፡ የዚህ ጥናት አላማ የኮንሶን ሃገረሰባዊ አልባሳትና ጌጣጌጦች አበይት ቁሳዊ ገጽታዎችን ማህበራዊና ጥበባዊ ፋይዳዎችን መመርመር ነው፡፡ አፀደ በጥናቷ የባህላዊ አልባሳቱን፣ ጌጣጌጦችንና የማህበረሰቡን የጸጉር አሰራር ገጽታ በመግለጽ የአለባበስ ስርዓቱን፣ አጋጣሚዎችንና ማህበራዊ ፋይዳዎቹን አሳይታለች፡፡ በተጨማሪም አልባሳቱ የማህበረሰቡን አባላት ማንነት እና እሴቶች እንዴት እንደሚገልጹ እንዲሁም በቁሶቹ ዙሪያ እየተደረጉ ያሉ ለውጦችን ከነምክንያታቸው አሳይታለች፡፡ ለዚህም ማሳያነት የተመረጡ ሶስት የጸጉር አሰራር፣ ሰባት አልባሳትን እና አስራ ሁለት የጌጣጌጥ አይነቶችን ተንትናለች፡፡

የአፀደ ጥናት በአልባሳትና ጌጣጌጥ እንዲሁም የጸጉር አሰራር ላይ መካሄዱ ከኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡ በተጨማሪም የቁሶቹን የመደረጊያ አጋጣሚ፣ አልባሳቱ የማህበረሰቡን አባላት ማንነትና እሴቶች እንዴት እንደሚገልጹ ማሳየቷ እና የቁሶቹን ለውጦች ከነምክንያታቸው በመግለጻ ከኔ ጥናት ጋር ያመሳስላታል፡፡ አፀደ ለጥናቷ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ምልከታንና የቃለመጠይቅ ዘዴን የተጠቀመች ሲሆን በእኔ ጥናት ግን መረጃዎችን ለመሰብሰብ ከምልከታና ከቃለመጠይቅ በተጨማሪ የቡድን ውይይት ለመረጃ መሰብሰቢያነት አገልግሏል፡፡ ይህንም ዘዴ መጠቀሙ በሁለቱ ዘዴዎች ማግኘት ያልተቻለን መረጃ ለማግኘት ያስችላል ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለሆነም በመረጃ መሰብሰቢያ

ዘዴዬ እና ስለ አልባሳቱም ሆነ ጌጣጌጦቹ የተባሉ ሥነ-ቃሎችን የጥናቴ አካል በማድረጌ የኔን ጥናት ከአፀደ ጥናት የተለየ ያደርገዋል፡፡

ሰይድ ይማም (2002) “በከሚሴ ከተማ ዙሪያ በሚገኙ ገጠር አካባቢዎች የወጣት ወንዶችና ሴቶች አለባበስና አጊያጊያጥ” በሚለው ጥናቱ በከሚሴ ዙሪያ በሚገኙ አምስት የገጠር አካባቢዎች የሚገኙ ወጣት ወንዶችና ሴቶች የሚለብሷቸውን ባህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጦችን ምንነት፣ አገልግሎትና ማህበረ-ባህላዊ ፋይዳ ያነሳል፡፡ በጥናቱ የሚዳሰሱ ወጣት ወንዶችና ሴቶች ሲሆኑ በተለይም ሴቶች ከመታጨታቸው በፊት፣ በሚታጩበት ወቅትና ካገቡ በኋላ በሚጠቀሙባቸው አልባሳትና ጌጣጌጦች ላይ ትንተና ሰጥቷል፡፡ ትንተና የሰጠባቸውም 6 አልባሳትና 15 ጌጣጌጦች ናቸው፡፡ በምልከታ፣ በቃለመጠይቅ እና በቡድን ውይይት የሰበሰባቸውን መረጃዎች ገላጭ የምርምር ዘዴን በመጠቀም ተንትኖ አቅርቧል፡፡

የሰይድን ጥናት ከኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው የአልባሳትና ጌጣጌጦችን ምንነት፣ ማህበራዊ ፋይዳ መግለጹ እና ከጌጣጌጦቹ ጋር ተያያዥነት ባላቸው የተወሰኑ ቃላዊ ግጥሞች ላይ ይዘታዊ ትንተና በማካሔዱ እንዲሁም በተጠቀምናቸው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴያችን ነው፡፡ የሰይድ ጥናት ወጣቱ ላይ ብቻ ትኩረት ያደረገ ሲሆን የእኔ ጥናት ግን የእድሜ ገደብ ሳይለይ ሁሉንም የሚያጠቃልል በመሆኑ ይለያል፡፡

ያሬድ ተፈራ (2002) “በሰቆጣና በአበርገሌ ገጠራማ ወረዳዎች የሴቶችና የወንዶች የአለባበስና የአጊያጊያጥ ማህበራዊ እሴቶች” በሚለው ጥናቱ በሁለቱ ወረዳዎች ያለውን የአለባበስና አጊያጊያጥ ልማዶችን የሚመረምር ሲሆን ቁሶቹን፣ የቁሶቹን አሰራር፣ ተግባር፣ ባለሞያዎቹን፣ የተደረገባቸውን ለውጥና ከቁሶቹ ጋር ተያይዘው የሚባሉ ሥነ-ቃሎችን የሚዳስስ ነው፡፡ ቃለመጠይቅ፣ ምልከታና የተተኳሪ ቡድን ውይይትን በመጠቀም የተሰበሰቡ መረጃዎችን ከንድፈ ሃሳቦቹ ጋር በማገናዘብ ትንተናውን ያቀረበ ሲሆን የFlemingን 5 የትኩረት አቅጣጫዎች መሰረት በማድረግ ለማሳያነት የተመረጡ አራት አልባሳትና ሰባት ማጌጫዎችን ተንትኗል፡፡ በተጨማሪም በአልባሳቱና ጌጣጌጦቹ ላይ ያለውን ለውጥ፣ የለውጡን ምክንያት እና ማህበረሰቡ ለለውጡ ያለውን አመለካከት አሳይቷል፡፡

ይህ ጥናት በተመረጠው ቦታ የወንዶችንና የሴቶችን አለባበስና አጊያጊያጥ የሚመለከት በመሆኑ፣ የአልባሳቱን የመሰሪያ ቁስ መግለጹ፣ በአልባሳቱና ጌጣጌጦቹ ላይ ያለውን ለውጥና የለውጡን ምክንያት መዳሰሱ እና በርዕሰ ጉዳዩና በተጠቃሚዎቹ ዙሪያ በማህበረሰቡ የተባሉ ስነ-ቃሎችን የሰበሰበ በመሆኑ ከኔ ጥናት ጋር ይመሳሰላል፡፡ በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴውም ተመሳሳይነት ይታይበታል፡፡ ያሬድ ለትንታኔው ማስኬጃነት የFlemingን 5 የትኩረት አቅጣጫዎች የተጠቀመ ሲሆን የእኔ ጥናት ግን ከሚከተላቸው የትንተና ሂደቶች ጋር የሚጎዳኙ በመሆናቸው የSchlerethን 9 ሞዴሎች የትኩረት አቅጣጫ በማድረግ ተተንትኗል፡፡

ከኔ ጥናት ጋር የሚቀራረበው የመጨረሻው የሁለተኛ ዲግሪ ጥናት የየኔአለም አረዶ (2000) “የአርሲ ሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጥ ጥናት (በኮኮሳና ገደብ ሀሳሳ ወረዳዎች)” የሚለው ነው፡፡ የዚህ ጥናት አላማ በሁለቱ ወረዳዎች የሴቶችን የባህል አልባሳትና ጌጣጌጥ የቀድሞና የአሁን ይዞታ መመርመርና ያሉበትን ሁኔታ ማሳየት ነው፡፡ ጥናቱ በተካሔደባቸው ወረዳዎች የሚገኙት ሴቶች በቀደሙት ጊዜያት የሚለብሷቸው ልብሶች በአብዛኛው ከቆዳ የተሰሩ እንደነበሩ፣ እነዚህም የተለያየ የአለባበስ ስርዓትና የመለበሻ አጋጣሚዎች እንዳላቸው አስረድታለች፡፡ በተጨማሪም ጌጣጌጦቹን ከሚውሉበት የሰውነት ክፍል አንጻር በተናጠል ትንተና ሰጥታባቸዋለች፡፡ ትንታኔውን ያካሄደችውም ገላጭ የምርምር ዘዴን በመጠቀም ሲሆን በ12 አልባሳትና በ28 ጌጣጌጦች ላይ ትንታኔ ሰጥታለች፡፡

የእኔና የየኔአለም ጥናት ከርዕሰ ጉዳዩ መመሳሰል በተጨማሪ በልብሶቹ ላይ ለውጥ መከሰት አለመከሰቱን መፈተሽ ከአላማችን አንዱ መሆኑ እና ቁሳዊ ባህሉን ከማህበረሰቡ አተያይ አንጻር መመልከታችን ያመሳስለናል፡፡ የየኔአለም ጥናት በሴቶች ላይ የተወሰነ ሲሆን የኔ ጥናት ግን የጾታ ገደብ አለማድረጉ እና የእኔ ጥናት ስለአልባሳትና ጌጣጌጦቹ እንዲሁም ስለተጠቃሚ ማህበረሰቦቹ የተባሉ ስነቃሎችን በጥናቱ የተተኮረበትን ጉዳይ ለማጉላትና ተጨባጭ ለማድረግ መጠቀሙ ከየኔአለም ጥናት ይለየዋል፡፡

ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራርበው ከተገኙት የመጀመሪያ ዲግሪ ጥናቶች ውስጥ የመጀመሪያው የአያል አድማሱ (1992) “የጎጃም አካባቢ የአልባሳት ስያሜ” የሚለው ጥናት ነው፡፡ አያል ጥናቱን ሲያደርግ ለመዳሰስ የተነሳው የአልባሳቱ ስሞች ሥነ-ቃላዊ ሆነው የተፈጠሩ መሆን አለመሆናቸውን ማረጋገጥ፣ የስያሜዎቹም መሰረት ምን እንደሆነ መግለጽና ማህበረሰቡን እንዴት እንደሚገልጹ ማሳየትን ነው፡፡ በዚህ ጥናት የፋብሪካ ውጤት የሆኑትና ከዘመናዊ

ፋሽን ጋር የተያያዙት አልባሳት ወዲያው በሚመጡበት ወቅት ዋጋቸውን፣ ቀለማቸውን እና ተፈላጊነታቸውን መሰረት ያደረጉ ስያሜዎች እንደሚሰጧቸው እየቆዩ ሲሄዱ ግን የሚለብሷቸውን ሰዎች የእድሜ ደረጃ፣ ሙያ እንዲሁም የልብሶቹን የመሰልቸት ሁኔታ፣ ወዘተ. በሚገልጹ ቃላት እንደሚጠሩ ተገልጿል፡፡ በተጨማሪም የልብሶቹ ስያሜ በተጠቃሚዎቻቸው ላይ ከሚያሳድሩት ተጽእኖ ጋር የተያያዙ እንደሆኑ ተገልጿል፡፡ ለማሳያነትም 60 ስሞች መጠነኛ ትንታኔ ተደርጎባቸዋል፡፡

የአያል ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚቀራረበው የጥናቱ መሰረታዊ ጉዳይ አልባሳት በመሆናቸው፣ አልባሳቱ የአካባቢውን ማህበረሰብ ሊገልጹት መቻላቸውን ሥነ-ቃሎችን መሰረት አድርጎ በመጠቆሙ ነው፡፡ በአያል ጥናት የአልባሳቱ የመለበሻ አጋጣሚዎች እና ባህላዊ አንድምታቸው አልታየም፡፡ የእኔ ጥናት አልባሳትንና ማጌጫዎችን ከማህበረሰቡ እምነትና አመለካከት አንጻር በመዳሰስ የአልባሳቱን የመለበሻ አጋጣሚዎች፣ ያላቸውን ባህላዊ አንድምታ የገለጸ መሆኑና ለጥናቱ የሚሰበሰቡት መሰረታዊ መረጃዎች ከተተኳሪው ማህበረሰብ በቀጥታ የተገኙ መሆናቸው እንዲሁም ሥነ-ልሳናዊ ጉዳዮች በእኔ ጥናት ውስጥ የማይነሱ መሆናቸው ከአያል ጥናት እንዲለይ አድርጎታል፡፡

ሁለቱንም ቁሶች ርዕሰ ጉዳይ በማድረጉ ከኔ ጥናት ጋር የተቀራረበው የውብሸት አሰፋ (1978) "የወይዛዝርት አልባሳትና ጌጣጌጥ ስሞች በአማራው ባህል" የሚለው ጥናት ነው፡፡ የዚህ ጥናት አላማ በመጥፋት ላይ ያሉ አልባሳትና ጌጣጌጦችን ስያሜ መሰብሰብና የተሰበሰቡትን አልባሳት የመለበሻ አጋጣሚና ቅርጽ በመግለጽ የአማራው ወይዛዝርት አለባበስ ምን ይመስል እንደነበር ማሳየት ነው፡፡ ቁሶቹ የሚለበሱባቸውን አጋጣሚዎች በመግለጽ አልባሳቱም ሆኑ ጌጣጌጦቹ ከተጠቃሚው ማህበረሰብ እምነት እና አስተሳሰብ ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዳላቸው አሳይቷል፡፡ አጥኚው የተከተለው የአሰራር ዘዴ የአልባሳቱንና የጌጣጌጡን የመጠሪያ ስሞች ከተለያዩ መጻሕፍት በመልቀም ቃላቱ ፍቻቸው ምን እንደሆነ ከመዝገበ ቃላት በመረዳት ለጥናቱ የሚሆን መረጃ ሊያቀብሉ የሚችሉ ግለሰቦችን በማነጋገር መስራትን ነው፡፡ ይህን ዘዴ በመጠቀምም 34 የአልባሳት፣ 2 የጫማ እና 60 የጌጣጌጥ ስሞችን ሰብስቧል፡፡

የውብሸት ጥናት አልባሳትንና ጌጣጌጥን ርዕሰ ጉዳይ በማድረግ አገልግሎታቸውንና የሚሰሩበትን ቁስ ከነስማቸው ለመግለጽ መሞከሩ ከኔ ጥናት ጋር ተዛማጅ ያደርገዋል፡፡ የውብሸት ጥናት በወይዛዝርት ላይ የተገደበ ሲሆን የኔ ጥናት ግን የጾታ ገደብ አላደረገም፡፡

የአልባሳቱንና የጌጣጌጦችን መጠሪያ ስሞች፣ ፍቻቸው ምን እንደሆነ ለማወቅ የተጠቀመው ዘዴ ካልዓይ ሲሆን የኔ ጥናት ግን የተካሔደው የጥናቱ ተተኳሪ ወደሆነው አካባቢ መስክ ተወጥቶ ከባህሉ ባለቤቶች በምልከታ፣ በቃለመጠይቅና በተተኳሪ የቡድን ውይይት መረጃዎችን በመሰብሰብ ነው፡፡ በተጨማሪም የጥናቴ አብይ ትኩረት ከቁሶቹ ስያሜ ይልቅ ቁሶቹና ማህበራዊ ጉዳዮች መሆናቸው ጥናቴ ከውብሸት የተለየበት ነው፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ ጥናት ጋር በከፊል ተዛማጅ ናቸው ተብለው ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ጥናቶች ዋና ትኩረታቸው ለጥናት የመረጧቸውን ቁሶች የአሰራር ሂደት ምን እንደሚመስል፣ ቁሶቹ ከምን ከምን እንደተሰሩ መግለጽ፣ ለማህበረሰቡ የሚሰጡት አገልግሎት ምን እንደሆነ፣ ማህበረሰቡ ለቁሶቹ የሚሰጠው ትርጓሜ ምን እንደሆነ እንዲሁም ከቁሶቹ ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ቃላዊ ግጥሞችን መሰብሰብና የባለሙያዎቹ ማህበራዊ ህይወት ምን እንደሚመስል ማሳየት ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ በመሆኑም አጥኚዎቹ ለጥናት በመረጧቸው ቁሶች፣ በሌሎቹ ጥናቶችም እንደታየው ቁሶቹ ለማህበረሰቡ የሚሰጡት አገልግሎትና ማህበረሰቡ ለቁሶቹ የሰጠው ተምሳሌትነት በዚህ ጥናትም የታዩ መሆናቸው ይህን ጥናት ከላይ ከተገለጹት ጥናቶች ጋር ሲያመሳስለው ከያሬድ ጥናት ውጭ ባሉት በሌሎቹ ጥናቶች በአላማነት ያልተነሳውን ጉዳይ ማለትም ስለቁሶቹ የተባሉ ቃላዊ ግጥሞችን አላማ አድርጎ የተነሳ በመሆኑ ከሌሎቹ ጥናቶች የተለየ ያደርገዋል፡፡ የካፊቾ ማህበረሰብ አልብሳትና ጌጣጌጦች በሙሉ በትንታኔ የቀረቡበት በመሆኑ ከሌሎች ጥናቶች በበለጠ ሙሉ ያደርገዋል፡፡ በተተኳሪው ማህበረሰብ መለየቱም የጥናቱ አዲስነት ነው፡፡

## 2.2. የንድፈ ሀሳቦች ቅኝት

በዚህ ንዑስ ክፍል በቁሳዊ ባህል ዙሪያ የተሰነዘሩ ንድፈ ሀሳቦች፤ ስለ አልባሳትና ጌጣጌጥ ምንነት፣ ፋይዳ እና ስለመጠናታቸው አስፈላጊነት፤ ስለ አመዳደብ ስልትና የመተንተኛ ዘዴዎች ምሁራን የሰነዘሯቸው ንድፈ ሀሳቦች ተካተው ቀርበዋል፡፡

### 2.2.1. ቁሳዊ ባህል

ቁሳዊ ባህል ከፎክሎር ዘሮች መካከል አንዱ መሆኑን በርካታ ምሁራን የገለጹ ሲሆን ከምሁራኑ መካከል Dorson (1972፣ 3)፣ Wilson (1986፣ 228) እና ፈቃደ (1991፣ 10-16)

ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ቁሳዊ ባህልም የተለያዩ ክፍሎች ኑረውት የሚጠና ሰፊ የፎክሎር ዘር ነው፡፡

ቁሳዊ ባህልን የተለያዩ ምሁራን በተለያዩ መንገዶች በይነውታል፡፡ Glassie (1999)፣ ፈቃደም (1991) እና Woodward (2007) ቁሳዊ ባህል የጥናት ዘርፍ እንደሆነ የሚገልጹ ሲሆን Cleary (2004) ደግሞ ቁሳዊ ባህል በቀጥታ ቁሶቹን የሚመለከት መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ እንደ ጥናት ዘርፍ ከሚቆጥሩት መካከል አንዱ የሆኑት Glassie ቁሳዊ ባህልን እንደሚከተለው በይነውታል፡፡

> Material culture is the culture made material; it is inner wit at work in the world. Beginning necessarily with things, but not ending with them, the study of material culture uses objects to approach human thought and action. (1999:41)

ከዚህ ሀሳብ ለመረዳት እንደሚቻለው ቁሳዊ ባህል ተጨባጭ ለሆኑና የሰው ልጅ ባህልን መሰረት አድርጎ ለዕለት ተዕለት ኑሮው ማከናወኛ የሚሰራቸውን ቁሶች የሚመለከት መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም የቁሱ ባለቤት የሆነውን የሰው ልጅን አስተሳሰብና ፍልስፍና በቁሶች አማካኝነት መመርመር እንደሚቻል መረዳት ይቻላል፡፡

ፈቃደም (1991፣15) በበኩላቸው ዶርሰንን ጠቅሰው ቁሳዊ ባህል የሰው ልጅ በዘመናዊ ኢንዱስትሪ መጠቀም ከመጀመሩ በፊት ፈጥሮ የተገለገለባቸውን ቁሳቁሶች፣ እነዚህ ቁሳቁሶች የተሰሩበትን ዘዴ ወይም ቴክኒክ እና ስራቸውን ለማከናወን የሚጠቀሙባቸውን መሳሪያዎች የሚያጠና የጥናት ዘርፍ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ Woodward (2007፣15) ስለቁሳዊ ባህል ጥናት ሲያስረዱ ቁሳዊ ባህል ተቀዳሚ አላማው በማህበረሰቡና በቁሱ መካከል ያለውን የጋራ ግንኙነት ማጥናት ሲሆን ማህበረሰቡ ቁሱን ለምን አገልግሎት ያስቀምጠዋል? ቁሱስ ለማህበረሰቡ የሚሰጠው አገልግሎት ምንድነው? የሚሉትን ጉዳዮች ይፈትሻል በማለት ገልጸዋል፡፡

የGlassieን፣ የፈቃደንና የWoodwardን ሀሳብ ተቃርነው የሚገኙት ደግሞ Cleary ናቸው፡፡ Cleary (2004፣2) ቁሳዊ ባህል በባህላዊ መንገድ የተሰሩና በዕለት ተዕለት ተግባር የምንገለገልባቸው ቁሶችን ወይም የቁሶችን ስብስብ የሚያሳይ እንጂ የጥናት ዘርፍ አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡

ከሁለቱም ወገን የሚነሱትን ተቃራኒ ሀሳቦች አንድ ላይ በማቀናጀት አስታራቂ ሀሳብ የሚያነሱ ምሁራንም አሉ፡፡ እነዚህም Prown እና Schlereth ናቸው፡፡ Prown በበኩላቸው ቁሳዊ ባህልን ሲበይኑ በተወሰነ ጊዜ በእጅ የተሰሩ እቃዎች (መሳሪያዎች) ውስጥ የተወሰነን ማህበረሰብ ወይንም አካባቢ እምነቶች፣ እሴቶች፣ ሀሳቦች፣ ምልከታዎች እና አመለካከቶችን የሚያጠና የጥናት ዘርፍ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ቁሳዊ ባህል እንደ ባህላዊ ምርመራ ቁሶችን እንደ መጀመሪያ መረጃ በመጠቀሙ ነጠላ እንደሆነና በጥናታዊ ዓላማው እንደ ባህላዊ ታሪክ ወይንም ባህላዊ አንትሮፖሎጂ ቅርንጫፍ ሊታይ ይችላል በማለት ያስቀምጣሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በቁሳዊ ባህል ውስጥ የሚገኘው ቁስ ለብቻው ሰፊ ነገር ግን የተገደቡ እቃዎችን፣ ሙሉ በሙሉ በሰው እጅ የተሰሩ ወይንም የተሻሻሉ የመሳሪያዎችን ክፍል የሚገልጽ ትርጓሜ ሊይዝ እንደሚችል እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡ “The word material in material culture refers to a broad, but not unrestricted of objects known as artifacts-objects made by man or modified by man.” (1982፡2)

Schlereth (1985፣22) ክርክሩን ለማርገብ ያስቀመጡት ሀሳብ ደግሞ የቁሳዊ ባህልን በይነ-ዲስፕሊናዊነት የሚገልጽ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ቁሳዊ ባህልን በተለያዩ ዘርፎች የሚገኙ ምሁራን እየተጠቀሙበት እንደሚገኙ፣ እነዚህም ምሁራን እራሳቸው የሚገኙበትን የትምህርት መስክ አመለካከት በሚያንጸባርቅ መልኩ በተለያየ መንገድ እንደሚበይኑትና እንደሚጠቀሙበት በመግለጽ ቁሳዊ ባህል በቁስነት ወይም ደግሞ በጥናት ዘርፍነት የሚታይበት አጋጣሚ ሊኖር እንደሚችል ጠቁመዋል፡፡

የቁሳዊ ባህል ብያኔ ብቻ ሳይሆን በውስጡ የሚያካትታቸውን ጉዳዮች በተመለከተም በምሁራን ዘንድ የተለያዩ ሀሳቦች ይነሳሉ፡፡ Dorson (1972፣233) ቁሳዊ ባህል በውስጡ አምስት ጉዳዮችን ማለትም ሀገረሰባዊ የእጅ ሥራ፣ ሀገረሰባዊ ሥዕል፣ ሀገረሰባዊ ምህንድስና፣ ሀገረሰባዊ ልብስ እና ሀገረሰባዊ የምግብ አሰራር ያካትታል ብለዋል፡፡ Prown (1982፣3) ደግሞ ጥበብ፣ ጊዜ ማሳለፊያዎች፣ መደነቂያዎች፣ የመሬት አቀማመጥ ማሻሻሎች፣ ተግባራዊ ጥበቦች፣ መሳሪያዎች በማለት በስድስት ይከፍሏቸዋል፡፡

### 2.2.1.1. የቁሳዊ ባህል መጠናት አስፈላጊነት

Prown (1982፣3-5) ቁሳዊ ባህል ለምን ይጠናል? በሚል ርዕስ ስር የቁሳዊ ባህልን መጠናት አስፈላጊነት ከጠቀሜታው ጋር አያይዘው ገልጸውታል፡፡ በማብራሪያቸውም እጅግ ባህላዊ

ሥነ-ጽሁፋዊና ባህሪያዊ ምንጮች ከሆኑት ልንማረው ከምንችለው የሚለይ፣ በተለዋጭነት ሊያገለግል የሚችል፣ አጋዥ ሊሆን የሚችል ወይንም የሚቃረን እውቀት ከእቃዎች ሊገኝ እንደሚችል ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም ታሪካዊ ክስተትን ለመጠበቅም እንደዚሁ ያለፈውን ጊዜ በአንደኛ ደረጃ የምንገናኝበትን፣ ከቀጠሉ ታሪካዊ ክስተቶች ቀጥተኛ የስሜት ልምድ የሚኖረንን እድል ይሰጡናል፤ ከቃላትም የበለጠ ወካይና የመረጃ ምንጭ ናቸው፡፡ ለዚህም ነው የኛ የምርምር ባህል እና ልምድ በተለይ ጥበብን፣ ህንጻንና የውበት ጥበብን በተመለከተ በከፍተኛ ሁኔታ እቃዎች ላይ ያተኮሩ የሆኑት በማለት ገልጸዋል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የተነሳ ቁሳዊ ባህልን ያላካተተ ጥናት ሙሉ እንዳልሆነ "The study of artifacts is only one route to the understanding of culture; it is a special, important, and qualitatively different route. An investigation that ignores matrial culture will be impoverished." Prown (1982፡5) በማለት ገልጸዋል፡፡

ከ Prown ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው የቁሶች ጠቀሜታ ዘርፈ ብዙ በመሆኑ የቁሳዊ ባህል ጥናት የሚያበረክተው አስተዋጾ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ቁሶችን ማጥናት ቁሱ የሚገኝበትን ወይንም የቁሱ ባለቤት የሆነውን ማህበረሰብ ማጥናት ማለት ነውና፡፡ ስለዚህም ቁሳዊ ባህልን ችላ ያለ ጥናት ጎደሎ ነው ማለት ይቻላል፡፡

Glassie (1999፣1) በበኩላቸው ከቁሳዊ ባህል ተግባር ጋር አያይዘው የመጠናቱን አስፈላጊነት ሲገልጹ ባህላዊ የሆኑ ቁሶች ከእለት ተእለት ግልጋሎታቸው ባለፈ የሰው ልጅ ለመኖር ሲል ከተፈጥሮ ጋር ሲያደርግ የነበረውን ትግልና በትግሉም አሸናፊ ለመሆን ተፈጥሮን ደጋግሞ ይቀርጽ የነበረበትን መንገድ እንደያዙና ይህ በመሆኑም በቁሳዊ ባህል ጥናት ወስጥ ታሪክና ጥበብ ተዋህደው የሚመጡ በመሆኑ ቁሳዊ ባህል መጠናት እንዳለበት አስረድተዋል፡፡

Mayo በበኩላቸው የቁሳዊ ባህልን የመጠናት አስፈላጊነት ቁሶች ወካይ በመሆናቸው ስለ አንድ ማህበረሰብ ሀይማኖታዊ እምነቶች፣ አስተዳደራዊ መዋቅር፣ የጠቢብነትን ደረጃና የአምራቹን ማህበረሰብ ሳይንሳዊና ስሜታዊ ውስብስብነት የማብራራት አቅም እንዳላቸው እንደሚከተለው ገልጸውታል፡፡

> Artifacts are symbols and can explain much about society; religious beliefs, forms of government, manual dexterity, level of intelligence, artistic

comprehension, available natural materials, structure of commerce, and scientific and emotional sophistication of the producing society. (1984፡3)

ፈቃደ (1991፣13) በፎክሎር ጥናት ውስጥ የዘመናዊውና የከተማው ባህል በሀገረሰባዊው ላይ እንዲሁም ሀገረሰባዊው በዘመናዊው ላይ የሚያመጣው ለውጥ መጠናት እንዳለበት ይገልፃሉ፡፡ Mayo (1984፣2) በበኩላቸው ቁሳዊ ባህሎች መጠናት ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ጥናቶችም ይረዱ ዘንድ ተሰብስበው ስርዓት ባለው መንገድ መሰነድ እንዳለባቸው ይጠቅሳሉ፡፡

በአጠቃላይ ከቀረቡት ሀሳቦች ቁሳዊ ባህልን ማጥናት ቁሱን ከማጥናት ባለፈ ሰዎችን በተለያየ መልኩ ማጥናትም ጭምር መሆኑን እንረዳለን፡፡ ይህ ጥናትም አልባሳቱና ጌጣጌጦቹ ከቁስነት ባለፈ ሌሎች ማህበራዊ ጠቀሜታዎች አሏቸው በሚል መነሻነት ተካሂዷል፡፡ ለዚህም የትንታኔው ክፍል አስረጂ ነው፡፡

### 2.2.1.2. የቁሳዊ ባህል ምደባ

የቁሳዊ ባህልን ምደባ አስመልክቶ ምሁራን የተለያዩ የመመደቢያ መስፈርቶችን በመዘርዘር መስፈርቶቹ ላይ የሚታየውን አንድ ያለመሆን ችግር ገልጸዋል፡፡

Prown (1982፣2) በቁሳዊ ባህል ስር የሚወድቁ እቃዎች እጅግ ሰፊ በመሆናቸው በቁሳዊ ባህል ጥናት ምደባ አስፈላጊ መሆኑን በመጥቀስ ከቁሶቹ ብዛት የተነሳ የእቃዎች አካላዊ ገጽታ ብቻ መሰረት አድርጎ ምደባ ማካሄድ አስፈላጊ እንዳልሆነ ጠቅሰዋል፡፡ በዚህም ምክንያት የቁሶቹን አገልግሎት መሰረት በማድረግ መመደብ አስፈላጊ መሆኑን “The most promising mode of classification is by function” በማለት አስቀምጠዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ሁሉም መስፈርቶች ከችግር ያልፀዱ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

Ames (1978፣20) ከ Prown መስፈርቶች በተጨማሪ ቅርጽ፣ ዘመን እና ባለሙያ የሚሉትን ጉዳዮች እንደ መስፈርት በመውሰድ ቁሶችን መመደብ እንደሚቻል ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን መስፈርቶቹ ምሉዕ አለመሆናቸውን አመልክተዋል፡፡

እነዚህ በ Prown እና በ Ames የተዘረዘሩ ነጥቦች በመስክ የተሰበሰቡ ቀዳማይ መረጃዎችን በቀላሉ ለመመደብ የሚያስችሉ ዘዴዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ዘዴዎች ምሉዕ ባለመሆናቸው የመስፈርቶቹን ጠንካራና ደካማ ጎን ለይቶ በማወቅ እንደሚጠናው ርዕሰ ጉዳይ መመደቢያ

መስፈርቶችን እያሰባጠሩ መጠቀም የተሻለ አማራጭ ነው፡፡ በመሆኑም ከመስክ የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች ማህበራዊ ደረጃን፣ የመደረጊያ ቦታንና የቁሶቹን አገልግሎት (ተግባርን) በመጠቀም ምደባ አካሒጄ ተንትኛለሁ፡፡

### 2.2.1.3. ቁሳዊ ባህልን የመተንተኛ ሞዴሎች

ቁሳዊ ባህልን ለመተንተን ዘጠኝ ሞዴሎችን መከተል እንዳለብን Schlereth (1980፣7-10) ገልጸዋል፡፡ ይህ ጥናትም ከነዚህ ሞዴሎች ጋር ተዋህዶ የሚቀርብ ሲሆን እነዚህን ሞዴሎች የተከተለበት ምክንያትም ሞዴሎቹ ጥናቱ ከሚከተላቸው የትንተና ሂደቶች ጋር የሚነዳኙ በመሆናቸው ነው፡፡ ግልጽ ለማድረግም በሚከተለው መልኩ በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

- **ተምሳሌታዊነት፡-** አንድ ማህበረሰብ ለሚጠቀምባቸው ቁሶች የተለየ ተምሳሌታዊ ውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡ ለምሳሌ ማህበረሰቡ ለተወሰኑ ሰዎች ከጀግንነት እና ከሀይማኖት ጋር አያይዞ የተለየ ማንነት ሊሰጣቸው ይችላል፡፡ ስለሆነም አንድ አጥኚ ቁሶቹን በሚተነትንበት ወቅት እነዚህን ተምሳሌቶች ከነትርጉማቸው አውጥቶ ማሳየት አለበት፡፡
- **ታሪካዊ ጥበብ ገላጭነታቸው፡-** ቁሶችን በምንተነትንበት ጊዜ ከጠቃሚነታቸው አኳያ ሳይሆን ጥበባዊ መስህብነታቸውን ማሳየት ይገባል፡፡ ይህንንም የምናደርገው ቁሶች በተፈጥሯቸው ውበትን የተላበሱ በመሆናቸው ነው፡፡ ስለሆነም የቁሶችን ቀለም፣ ቅርጽ፣ ልስላሴና ሸካራነት በገለጻ ወቅት አጉልቶ በማውጣት ታሪካዊ እሴት አመላካችነታቸውን ማሳየት ይጠበቃል፡፡
- **ባህላዊነት፡-** ይህ ሞዴል የምናጠናው ቁስ የተለየ ባህሪ አለው ወይ? የተወሰነ ባህልን የሚወክልበት ሁኔታ አለ ወይ? ብሎ በመመርመር፣ ማጤንና መግለጽን ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም ቁሱ የአንድን ማህበረሰብ ባህል መግለጽና አለመግለጽ የምንፈትሽበት ነው፡፡
- **መዋቅራዊነት፡-** ይሄ ሞዴል ቁሱ ከምን እንደተሰራ እና መሰሪያ ቁሱ ከየት እንደተገኘ በመግለጽ ትንታኔውን ማስኬድ እንደሚጠበቅብን የሚያወሳ ነው፡፡
- **ማህበራዊነት፡-** ይህ ሞዴል ቁሱ ለማህበረሰቡ ምን አይነት ማህበረሰባዊ ጠቀሜታ አለው? ማህበረሰቡስ ለቁሱ ተመሳሳይ እይታ አለው ወይ? የሚሉ ጥያቄዎችን

በመጠየቅ ቁሱ ያለውን ማህበራዊ ጠቀሜታ በትንታኔያችን ውስጥ ማሳየት እንደሚገባን የሚገልጽ ነው፡፡

- **አገልግሎት ሰጭነት፡-** ይህ ሞዴል ትንታኔያችንን በምናካሂድበት ወቅት የቁሶች ቀዳሚ አላማ ምንድን ነው? አገልግሎት የሚሰጡትስ እንዴት ነው? አገልግሎቱን የሚሰጡት እስከመቸ ነው? አሁንም በመስጠት ላይ ናቸው? የሚሉ ጥያቄዎችን ማንሳት እንዳለብን የሚጠቁም ነው፡፡
- **አካባቢያዊነት፡-** ይህ ሞዴል አንድ ቁስ በሚኖርበት አካባቢያዊ ሁኔታ (ለውጥ) የተነሳ የሚደርስበት ተጽዕኖ መኖር አለመኖሩን የምንፈትሽበት ነው፡፡
- **የማህበረሰብ ታሪክ ጠቋሚነት፡-** በዚህ ሞዴል አማካኝነት የቁሱን ታሪክ፣ የኖረበትን ዘመንና የሰራውን ሰው ማንነት በመጠየቅ ቁሱ የማህበረሰቡን ታሪክ እንዴት እንደሚጠቁም ማሳየት ይቻላል፡፡
- **ባህሪ ገላጭነት፡-** ትንታኔያችንን በምናካሂድበት ወቅት በቁሱና በማህበረሰቡ መካከል ያለው ባህሪያዊ ግንኙነት ምንድን ነው? ብሎ በመጠየቅ የቁሶችን ባህሪ ገላጭነት የምናሳይበት ነው፡፡

የቁሳዊ ባህል ጥናት ስናካሂድ መሰረታዊ የሆኑ ሞዴሎችን መከተል ያለብንን ያህል ሞዴላችንን መሰረት አድርገን የተገነዘብናቸውን ጉዳዮች ልናሳይባቸው የሚገቡ የመተንተኛ ሂደቶች መኖራቸውን ማወቅ እንዳለብንም ምሁራን ጠቁመዋል፡፡ Prown (1982፣7-10) አንድ ጥናት በገለጻ (Description)፣ በትርጓሜ (Deduction) እና በመላመምታት (Speculation) የመተንተኛ ሂደቶች ሊከናወን እንደሚችል ገልጸዋል፡፡ በዚህ ጥናትም ከነዚህ የመተንተኛ ሂደቶች መካከል ገለጻ ለመረጃ መተንተኛነት ውሏል፡፡ የግጥሞቹን ተግባር ለማሳየት ደግሞ የይዘት ትንተና ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

### 2.2.2. ሀገረሰባዊ አልባሳት

የሰው ልጅ ልብስ መልበስ ጀመረ ከሚባልበት ጊዜ አንስቶ አሁን ያለንበት ዘመን ድረስ አልባሳቱን ከአካባቢው ከሚያገኛቸው ጥሬ እቃዎች ሲያበጅ ኑሯል፡፡ እነዚህን አልባሳት የሚለብስባቸው ምክንያቶችም የተለያዩ ናቸው፡፡ ከነዚህ ምክንያቶች ውስጥ ቀዳሚው ራሱን ከተለያዩ ተፈጥሯዊ ተጽዕኖዎች ለምሳሌ ከዝናብ፣ ከብርድ፣ ወዘተ. ለመከላከል (ለመሸፈን)

ሲሆን በተጨማሪም ለማጌጫነት፣ የስራ ሁኔታዎችን ምቹ ለማድረግ እና ባህልን ለማንጸባረቅ፣ ወዘተ. የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

Bradshaw (1965፣10) የአልባሳትን መስሪያ ቁሶች የመገኘት ሁኔታ ከአካባቢው ጋር አያይዘው በብዙዎቹ የአለማችን ክፍሎች ሀገረሰባዊ አልባሳቱ በአካባቢው በሚገኝ ጥሬ እቃ ላይ ተወስነው ይሰሩ እንደነበርና አሁንም እየተሰሩ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ለምሳሌ ያህልም በጎች በስፋት በሚረቡባቸው ቦታዎች ለአልባሳቱ ስራ የሚውሉት ቁሶች የበግ ፀጉርና ቆዳ፣ ተራራማ በሆኑ ቦታዎች የፍየል ፀጉር፣ የሀር ትሎች በሚረቡበት ቦታ ደግሞ ሀር በጥሬ እቃነት ያገለግላል በማለት ይገልጻሉ፡፡

የሀገረሰባዊ አልባሳት ተግባር ከሆኑት ውስጥ ማንነትን መግለጽ፣ ማህበራዊ ደረጃን መግለጽ እና ሀይማኖታዊ ተግባራትን መግለጽ የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

### 2.2.2.1. ማንነትን መግለጽ

የሰው ልጅ በአካባቢው በሚገኙ ቁሶች አማካኝነት ማንነቱን ይገልጻል፡፡ እነዚህም ቁሶች በማህበረሰቡ የተለያዩ ማህበራዊ ትርጓሜዎች ይሰጧቸዋል፡፡ በመሆኑም ቁሶች በአንድ ባህል ውስጥ የማህበረሰብንም ሆነ የግለሰብን ምንነት በማሳየት እና በመግለጽ ረገድ ድርሻቸው የጎላ ነው፡፡ ምንነት (Identity) ማለት አንድ ግለሰብ ወይም ማህበረሰብ "እኔ ማነኝ" ለሚለው ጥያቄ የሚያስቀምጠው (የሚፈጥረው) በማህበራዊ መንገድ የተወሰነና የተገደበ መልስ መሆኑን Woodward (2007፣134) ያስረዳሉ፡፡

ልብሶች ከሚለበሱባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ማንነትን ከመግለጽ ጋር የተያያዘ እንደሆነ Lurie (1981፣5) ሰፊ ትንታኔ በመስጠት ተልጸዋል፡፡ በትንታኔያቸውም አልባሳት ያግባባሉ፤ በመሆኑም የአለባበስ ሁኔታን በማየት የግለሰብን ብሎም የማህበረሰብን ማንነት መገመትና መናገር ይቻላል፡፡ ይኸውም ጉዳይ ብዙ አመታትን ያስቆጠረ ሲሆን ለብዙ ሺህ አመታት ሰዎች አንዱ ከሌላው ጋር በልብስ ቋንቋ ሲግባቡ ኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ልብስን በማየት የለባሹን ማህበረሰብ ከየትነት እና ባህል መናገር የሚቻልበት አጋጣሚ አለ፡፡ በተለይም ባህላዊ አልባሳትን የለበሰ ሰው ከሆነ በቀላሉ ስለግለሰቡ ማንነት መናገር ይቻላል፡፡ ይህም የልብስ የማግባባት ሀይል ከሌሎች ቁሶች የተሻለ ያደርገዋል በማለት ገልጸዋል፡፡

Yoder በበኩላቸው የአውሮፓ ሰራተኞችን (የገበሬዎችን) የአለባበስ ባህል በምሳሌነት ጠቅሰው የባህል ልብስን እንደሚታይ የባህላዊ ቡድን ማንነት ውጫዊ ባጅ ይቆጥሩታል፡፡ አልባሳትም ይህን ማንነት ለማሳየት ሆን ተብለው የሚለበሱ እንደሆኑና አካባቢያዊነትን እና ክልልን (ቀጠናን) እንደሚያሳዩ እንደሚከተለው ገልጸውታል፡፡ Folk costume is the visible, outward of folk- group identity, worn consciously to express that identity. … Identity was determined geographically, and the local costumes expressed locality, region, or province. (1972:295)

ከ Yoder ገለጻ እንደምንረዳው ባህላዊ ልብስ የለበሰን አንድ ግለሰብ ወይም ማህበረሰብ በማየት የለባሹን ከየትነት እና አጠቃላይ ማንነት መረዳት ይቻላል፡፡

### 2.2.2.2. ማህበራዊ ደረጃን መግለጽ

የሀገረሰባዊ አልባሳት ተግባር አንድ ማህበረሰብ ተለይቶ የሚታወቅባቸውን ገጽታዎች ማሳየት ብቻ ሳይሆን በአንድ ማህበረሰብ ውስጥም ያለን ክፍፍል ማሳየት እንደሆነ Yoder ይገልጻሉ፡፡ ስለ ክፍፍሉ ሁኔታም አልባሳት በማህበረሰቡ ውስጥ የልብሱን ለባሽ ከማህበራዊ ደረጃ፣ ከስራ መስክ፣ በስራ ላይ ከመሆን፣ በቅንጦት ላይ ከመሆን፣ በንሰሀ ላይ ከመሆን አንጻር አንዱ ከአንዱ እንዲለያይ ያደርጉታል በማለት አብራርተዋል Yoder (1972፣304)፡፡

በተጨማሪም የባህል አልባሳት በውጭው የባህላዊ አካባቢውን ማንነት የሚወክሉና የግለሰቡን ከማህበረሰቡ ጋር እንዲሁም በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን የተለያዩ ግንኙነቶች የሚገልጹ እንደሆኑ ገልጸዋል፡፡ አልባሳት ገበሬውን ገበሬነቱን፣ እንጨት ቆራጩን እንጨት ቆራጭነቱን፣ እረኞችንም እንዲሁ የሚለዩ እንደሆኑም ያስረዳሉ፡፡ በተጨማሪም በአንድ የተወሰነ አካባቢ ወይም ቦታ ከሚኖረው ህዝብ መካከል የሰዎችን ማንነት በአለባበሳቸው ልንረዳ እንችላለን፡፡ በዚህ መሰረት በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን የወንድና የሴት ጾታ፣ ከህጻንነት ጀምሮ እስከ ሽምግልና ወቅት ያለውን የእድሜ መለያየት እና ያገቡትን ካላገቡት ሴቶች ነጥሎ ማመልከት የሀገረሰባዊ አልባሳት ተግባራት እንደሆነ ማጤን ይቻላል ብለዋል Yoder (1972፣296-304)፡፡

### 2.2.2.3. ሀይማኖታዊ ተግባር

ቁሶች ማህበረሰቡ እምነቱን፣ አመለካከቱን፣ ብልሀቱን፣ እውቀቱን፣ ወዘተ. የሚቀርጽባቸውና የሚያስተላልፍባቸው መንገዶች መሆናቸውን በመግለጽ ማንኛውም ባህላዊ ቁስ አካላዊ ከሆነው ተግባሩ በተጨማሪ መንፈሳዊ በሆነ መንገድ የሚያስተላልፈው መልዕክት ሊኖረው እንደሚችል Bronner ያስረዳሉ፡፡ በርግጥም በአንድ ሀገር ውስጥ የሚኖሩ ህዝቦች የተለያዩ ሀይማኖቶችን የሚከተሉበት አጋጣሚ የሰፋ እስከሆነ ድረስ እንደሚከተሉት ሀይማኖት መለያየት ሁሉ ሀይማኖታቸውን የሚያንጸባርቁበት መንገድም የተለያየ ይሆናል፡፡ የየትኛው ሀይማኖት ተከታይ እንደሆኑ ለማሳወቅም አልባሳት የራሳቸው ሚና አላቸው፡፡ በሀገራችን ኢትዮጵያም በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያናት አካባቢ በቄሶችና ካህናት እንዲሁም በሀይማኖቱ ተከታዮች የሚለበሱ አልባሳት በእስልምና እምነት አካባቢ የሀይማኖቱ መሪዎች ከሚለብሷቸው አልባሳት የተለዩ እንደሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡ በሌሎችም ሀይማኖቶች እንደዚሁ የተለያየ አይነት አለባበስ ይታያል፡፡

አልባሳት የሰውን ልጅ ውጫዊ አካል ከተለያዩ ክስተቶች ከመጠበቅ ባለፈ የሰውን ልጅ ከተለያዩ ክፉ መናፍስት የመከላከል ተግባር እንዳላቸው Gracia (2008) ገልጸዋል፡፡ ስለዚህም አልባሳት መንፈሳዊ ተግባር እንዳላቸው መረዳት ይቻላል፡፡

### 2.2.3. ሀገረሰባዊ ጌጣጌጥ

ሀገረሰባዊ ጌጣጌጥ ከጥንት (ከቆዩ) የማጌጫያ ጥበቦች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ይህም ጥበብ የሰው ልጅ አካልን ለማቆንጀት ያለውን ጥልቅ ምኞትና ለውብ ቁሶች ያለውን ጥልቅ ፍቅር የሚያሳይ ነው፡፡ በእነዚህ ቁሶች አማካኝነት የሰው ልጅ ምስጢራዊነት ያላቸውን ነገሮች የሚገልጽባቸው ናቸው፡፡ ስለሆነም ሰዎች እንዲያስውቧቸው የሚያበጇቸውና በባህላዊ መንገድ ተሰርተው የሚጠቀሙባቸው የጥበብ ውጤቶች ናቸው፡፡ ይህም ጥበብ ቀደም ያለ ታሪክ ያለው የጥበብ አይነት ነው Evans (1970፣39)፡፡

ሀገረሰባዊ ጌጣጌጦች እንደ ማህበረሰቡና እንደመኖሪያ አካባቢው መለያየት ሁሉ በሚበጁበት ቁስና ቅርጽም ልዩነት ያሳያሉ፡፡ Clark (1986፣6) በዚህ ጉዳይ ላይ ሰፊ ትንታኔ የሰጠ ሲሆን በትንታኔውም ጌጣጌጥን ለመስራት የዋሉት ቁሶችና የጌጣጌጡ ቅርጽ እንደ ቁሱ መገኘት፣ እንደማህበረሰቡ ፍላጎትና እንደባለሙያው የጥበብ ብቃት ከአካባቢ

አካባቢ እንዲሁም ከባህል ባህል ይለያያሉ፡፡ በአንዱ ማህበረሰብ አካባቢ የዝሆን ቀንድ እንደልብ የሚገኝ ከሆነ ብዙዎቹ ጌጦችም የዚያው ውጤቶች የመሆን ሰፊ እድል አላቸው፡፡ እነዚህን ቁሶች ከጊዜ ወደጊዜ እየለመዱና እየተጠቀሙ መሄዳቸው ደግሞ የማህበረሰቡ ፍላጎት ወደነዚህ እንደልብ የሚገኙ የቁስ መስሪያዎች እንዲያዘነብል ያደርገዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በተለያዩ ባህሎች ውስጥ ያሉ ባለሞያዎች በሚኖራቸው የአሰራር ችሎታ መለያየትም በየአካባቢው የሚገኙ ጌጣጌጦች ሊለያዩ ይችላሉ፡፡

ጌጣጌጦች እንደ አልባሳት ሁሉ የሚጠቀምባቸውን ግለሰብ እንዲሁም ማህበረሰብ ማንነትና የኑሮ ደረጃ ያመለክታሉ፡፡ ሀገረሰባዊ ጌጣጌጦች ከመዋቢያነት ባለፈ ተምሳሌታዊ ፋይዳ እንዳላቸው እና አንድን ማህበረሰብ ከማህበረሰብ፣ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥም እድሜን፣ ፆታን እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታን የማሳየት አቅም እንዳላቸው Clark (1986፣10) ገልጸዋል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## ጥናቱ የተደረገበት አካባቢ ገጽታና የማህበረሰቡ ዳራዊ መግለጫ

ይህ ክፍል በሶስት ንዑሳን ክፍሎች የቀረበ ሲሆን ስለተጠኘው ማህበረሰብ አጠቃላይ ገጽታ (መልክአ ምድራዊ ሁኔታ፣ የአየር ፀባይ፣ የቱሪስት መስህቦች እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ) እና ማህበረ-ባህላዊ ሁኔታ የተገለጸበት ነው፡፡

### 3.1. የካፋ ዞን ገጽታ

የካፋ ዞን በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ከሚገኙ 14 ዞኖችና 4 ልዩ ወረዳዎች አንዱ ነው፡፡ ዞኑ በ10 ወረዳዎችና በ1 የከተማ አስተዳደር የተዋቀረ ነው፡፡ የዞኑ ርዕሰ ከተማ ቦንጋ ከተማ ናት፡፡ ቦንጋ በገናናውና ጥንታዊው የካፋ ነገስታት ማዕከልነቷ የምትታወቅ ሲሆን ከአዲስ አበባ በ449 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡

የካፋ ዞን 10,636.8 ካሬ ሜትር ስፋት ሲኖረው ከአጠቃላይ የክልሉ ቆዳ ስፋት ውስጥ 9.09 በመቶውን ይሸፍናል፡፡ ዞኑ በሰሜን ምስራቅና ሰሜን ምዕራብ ከኦሮሚያ ክልል፣ በምስራቅና ደቡብ ምስራቅ ከዳውሮ ዞን፣ በደቡብ ከደቡብ ኦሞ ዞን፣ በደቡብ ምዕራብ ከቤንች ማጂ ዞን እና በምዕራብ ከሸካ ዞን ጋር ይዋሰናል፡፡

ካፋ ከምድር ወገብ በላይ በስተሰሜን ከ6°15 ሰሜን እስከ 8°08 ሰሜን ኬክሮስ፣ ከ35°30 ምስራቅ እስከ 36°46 ምስራቅ ኬንትሮስ ላይ ትገኛለች፡፡ የዞኑ ምድር ከባህር ወለል በላይ ከ500 እስከ 3500 ሜትር ከፍታ ላይ ያረፈ ሲሆን ከአጠቃላይ ቆዳ ስፋቱ 70 በመቶ ወይና ደጋማ 4 በመቶ ደጋማ እና 26 በመቶ ቆላማ የአየር ንብረት የተሸፈነ ነው፡፡ አማካይ አመታዊ የዝናብ መጠኑ ከ1400 እስከ 2000 ሚ.ሜ ይደርሳል፡፡ የሙቀት መጠኑ አማካይ ከ12-26°C መካከል ነው፡፡ ሂኖክ (34)

ካፋ ከደን ሽፋኑና ከአየር ንብረቱ ጋር ተዳምሮ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ አካባቢዎች ከፍተኛውን የዝናብ መጠን የያዘ ነው፤ ለምድር ሰቅም ቅርብ ነው፡፡ ከባህር ወለል በላይ ያለው ከፍታ አብዛኛው በተፈጥሮ ደን የተሸፈነ ሲሆን የመልክአምድሩ አቀማመጥም ተራራማና ወጣ ገባ የበዛበት ነው፡፡

በካፋ ምድር ያለው የማዕድን ሀብት በሳይንሳዊ ጥናት የተደገፈ ባይሆንም ከባህላዊና ከህብረተሰቡ ከእለት ተእለት አጠቃቀም በመነሳት ለመረዳት የሚቻለው በዞኑ ዝቅተኛ ቦታዎች ማለትም እንደ ጨታ ቆላና ጮጫ ማኪራ በመሳሰሉት አካባቢዎች የብረት ማዕድን፣ የኖራና የሸክላ አፈር እንደሚገኝ ነው፡፡

በዞኑ በዋናነት ሶስት ብሔሮች የሚኖሩ ሲሆን እነዚህም ካፊቾ፣ ጫራ እና ናኦ ናቸው፡፡ ከእነዚህ በተጨማሪ በስራና በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ዞኑ መጥተው የሰፈሩ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ሲኖሩ ከዞኑ ብሔረሰቦች ጋር ተስማምተውና ተከባብረው የሚኖሩ ናቸው፡፡ በ1999 ዓ.ም በተደረገው የህዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ ውጤት መሰረት የዞኑ ዓመታዊ የህዝብ እድገት 2.9 በመቶ ሲሆን በዚህ ስሌት መሰረትም የ2004 ዓ.ም የዞኑ የህዝብ ቁጥር በከተማና በገጠር በአጠቃላይ 1,011,780 ይደርሳል፡፡ ሂኖክ (35)

የካፋ ህዝብ ዋነኛ የኢኮኖሚ መሰረቱ ግብርና ነው፡፡ የካፋ ገበሬ የእሻ መሬቱን በማፈራረቅና ማሳውንም በማቃጠል ያርሳል፡፡ አንዱ የእርሻ መሬት ደከም ያለ ምርት የሚሰጥ ከሆነም ይህንኑ የእርሻ መስክ እስከተወሰነ አመት ድረስ በመተው ወደ ሌላ ዘመዶቹ አካባቢ በመሄድ ማረስ የተለመደ ነው፡፡ በአብዛኛው የኢትዮጵያ ግዛቶች እንደተለመደው ሁለት በሬዎች አቀናጅቶ ጠምዶ ማረስ ከጥንት ጀምሮ በካፋም የተለመደ አስተራረስ ነው፡፡ በቆላማው አካባቢ ከሚበቅለው አዝመራ ቀድሞ በደጋው አካባቢ የሚበቅለው አዝመራ የሚደርስ ሲሆን ከባድ የእርሻ ስራ፣ የቤት ግንባታና ሌሎችም ስራዎች ሲሆኑ በህብረት ይከናወናሉ፡፡ በመስከረምና በጥቅምት ወራት ገበሬዎች ቀፎ ይሰቅላሉ፡፡ ብርቱ ገበሬም በዓመት ሶስት ጊዜ የማር ምርት ይሰበስባል፡፡ ካፋ ውስጥ ቆጮ የሌለበት ምግብ ተወዳጅ አይደለም፤ በመሆኑም በአካባቢው በብዛት ይተከላል፡፡ በካፋ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታቸው የጎላ የተለያዩ የጋማ እንስሳት ይገኛሉ፡፡ በአሁኑ ጊዜ ጥርኝ (ዋንጌ፣ ዋንጎ) በዱር አውሬነት የሚታወቅ ቢሆንም በካፋ ታሪክ ግን ይህ እንስሳ በደንብ እንዲቀለብ ይደረግና የጥርኙ (ዋንጌ፣ ዋንጎ) ዝባድ ለውጭ ገበያ ይቀርብ እንደነበር የአካባቢው ሰዎች ይናገራሉ፡፡ በቀለ (1996፣35-38)

ቱሪዝም ጭስ አልባ ኢንዱስትሪ ሲሆን በዓለም ላይ ፈጣን እንቅስቃሴ እያሳየ የሚገኝ ነው፡፡ ይህ ኢንዱስትሪ በካፋ ዞን በተለያዩ ቦታዎች ይገኛል፡፡ ከእነዚህም ዋና ዋናዎቹ ፏፏቴዎች፣ የእምነት ተቋማት፣ ጥቅጥቅ ያሉ የተፈጥሮ ደኖችና የተለያዩ የዱር እንስሳትና አእዋፍ ይገኛሉ፡፡ በርካታ ቱሪስቶችም ወደዞኑ በመሄድ ይጎበኛሉ፡፡ በካፋ ዞን ባህልና

ቱሪዝም የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች መምሪያ ባተዘጋጀው መጽሔት ላይ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው በዞኑ የሚገኙ የቱሪስት መዳረሻዎች የሚከተሉት ናቸው፡

| | የፏፏቴዎች ስም | የሚገኝበት ወረዳ | የዋሻው ስም | የሚገኝበት ወረዳ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ባርታ | ጊምቦ | ሃዊት | ጨታ |
| 2 | ኤሊሎ | ጌሻ | ቦርቲ | ጠሎ |
| 3 | ወሺ | ጨና | ዶሺ | ጨና |
| 4 | አዲዮ | አዲዮ | ኤኬሮ | ጊምቦ |
| 5 | ጉማ | ዴቻ | ኮታ | ጊምቦ |
| 6 | ሻኪ | ገዋታ | ጣቀ ኬጠ | ጌሻ |
| 7 | ቶታ | ዴቻ | ያየ | -------- |

ጉርጉቶ የተፈጥሮ ድልድይ (የእግዜር ድልድይ)፣ ጎራ ፍል ውሃ፣ ዳዲበን ፍል ውሃ፣ የተፈጥሮ ደን፣ በሃ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያን፣ የተንጎላ መስጂድ እና የተለየው የቦናጋ በግ ዝርያ ተጨማሪ የቱሪስት መስህቦች ናቸው፡፡ ቡኖ መጽሔት (22-23)

## 3.2. የካፋ ዞን የቡና መገኛ

ዛሬ በአለም ላይ በስፋት ከሚጠጡ መጠጦች አንዱ የሆነው ቡና በእርካታ ሰጭነቱና በማነቃቃት ሀይሉ ቀዳሚው ነው፡፡ ይህም ቡና የተገኘው በታላቋ ኢትዮጵያ ምድር በካፋ ዞን ዴቻ በሚባለው ወረዳ ነው፡፡ ቡና የተገኘባት ቀበሌ ማኪራ ትባላለች፤ በማኪራ ቀበሌ ቡኒ በተባለው ስፍራ ስለመገኘቱም የጉዞ ጸሀፍት፣ ጋዜጠኞችና የግብርና ተመራማሪዎች ይመሰክራሉ፡፡ ሂኖክ (39)

የካፋ ዞን የመጀመሪያዋ የቡና መገኛ መሆኗን በርካታ ምሁራን ባደረጉት ጥናት ማረጋገጥ ችለዋል፡፡ ከነዚህም መካከል Orentን እና Langeን መጥቀስ ይቻላል፡፡ Orent ቡና የኢትዮጵያ ዋና የኢኮኖሚ ምንጭ ሲሆን ምንጩም ካፋ መሆኑ ለዘለአለም የሚታወስ ነው በማለት ገልጸዋል፡፡ Lange በበኩላቸው ካፋ የቡና መገኛ ሀገር መሆኗንና በአፍሪካ ዋናዋ ቡና አምራች ምድር መሆኗን “Kafa may very well be, as Bruce (1804) noted two centuries ago, the birth place of coffee plant. Prior toKafa-Amhara war, Kafa

was said to have been the principal coffee producing land in Africa" በማለት ገልጸውታል፡፡ በቀለ (1996፣41)

የቡና ስያሜ ምንጭ የካፊኛ ቋንቋ እንደሆነ የአካባቢው ነዋሪዎች እና አጥኝዎች ይገልጻሉ፡፡ "ቡኖ" የቡና የካፊኛ መጠሪያ ቃል ሲሆን በኢትዮጵያ በአብዛኛዎቹ ቋንቋዎችም የዚሁ ቃል መነሻ ሆኜ ተቀጥላ ሆኜያት እንዳሉና ሁለተኛው ሆኜ እየተለወጠ ለተመሳሳይ ነገር (ለምሳሌ ሲጠብቅና ሲላላ ቡና፣ ቡን፣ ቡኔ፣ ቡኒ ወዘተ) በሚል መጠሪያነት ያገለግላል፡፡ በቀለ (1996፣42)

## 3.3. የካፋ ነገስታት ታሪክ

የካፋ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በጽሁፍ የቀረበው ከ1520-1526 ገደማ ሰሜን ኢትዮጵያን በጎበኙት ፖርቹጋላዊ ቄስ በአባ አላቫሬዝ አማካኝነት ነው፡፡ ስለ ካፋ ወይም ስለ ጎንጋ ህዝቦች ማወቅና ማጥናት ይበልጥ የተጀመረው ከቄስ አላቫሬዝ በኋላ ቢሆንም በተለይም አውሮፓዊያን፣ በእነ አማኑኤል ዴ አልሜዳ፣ በአንቶኒዮ ፈርናንዴስ (1613-1614)፣ እንዲሁም በፍሌሚንግ አማካኝነት ነው፡፡ ስለ ካፋ በተሻለ ሁኔታ የሚገልጹ ጽሁፎች የታዩትና የተነበቡትም ከ16ኛ ክ/ዘ (1390-1897) ነው፡፡ በአጠቃላይ እስካሁን የታዩት ቀደምትና የቅርብ ጊዜ የውጭና የሀገር ውስጥ የታሪክ ጸሐፊዎች የካፋ መንግስት ከመካከለኛው ዘመን (ከ500 ዓ.ም እስከ 1500 ዓ.ም) በፊት ጀምሮ የተመሰረተ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ እንግዲህ በእነዚህ ጸሐፊዎች አገላለጽ መሰረት የካፋ-ጎንጋ መንግስት የተቋቋመው ከ500 ዓ.ም በፊት ነው ማለት ይቻላል፡፡ በቀለ (1996፣72)

ካፋ ራሱን ችሎ በመንግስትነት በነበረባቸው ዘመናት የመንጀ፣ ማቶና ሚንጆ ሥርወ-መንግስታት በስልጣን ላይ ቆይተዋል፡፡ የማቶ ሥርወ-መንግስት ከ14ኛው ክ/ዘመን በኋላ ስልጣንን ለሚንጆ ሲያስረክብ ከዛን ጊዜ አንስቶ ደግሞ ከሚንጆ የሆኑ የተለያዩ ነገስታት በስልጣን ላይ ተፈራርቀዋል፡፡ በዚህም ሚንጆዎች ከሰዎች በላይ እንደሆኑ ተደርጎ እንደሚታሰብ Huntingford "The Minjo are described in tradition as being a people more than human…." (1993፡7) በማለት አስቀምጠዋል፡፡

የካፋ ነገስታት "ታቶ" ተብለው ይጠራሉ፡፡ የንጉሱ (ታቴኖ) ስልጣን ዘርፈ ብዙ ቢሆንም ከሌሎች ሀገራት ጋር ያለን ግንኙነት መመስረትና ማስቀጠል፣ ጦርነትን ማወጅ፣ የተለያዩ

ኅሳዎች የሚገባቸውን የስልጣን ቦታ መለየትና ማረጋገጥ፣ የጦር ምርኮኞችን መቆጣጠር እና የእንግዶችን ጉዳይ መቆጣጠር የሚሉት ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ የካፋ ንጉስም ምግብ በራሱ እጅ እንደማይበላና መጋቢ ያጎርሰው እንደነበር Lange (1982፣116) ገልጿል፡፡

የካፋ ሥርወ-መንግስት ከ14ኛው ክ/ዘመን ጀምሮ እስከ 19ኛው ክ/ዘመን ድረስ 19ኙ ያህል ነገስታት ተፈራርቀውበታል፡፡ የመጨረሻው ንጉስ ታቴኖ ጋኪ ሻሮቺ በምኒሊክ ጦር ተማርከው ወደ ማዕከላዊ መንግስት እስከተወሰዱበት ጊዜ ድረስ ያለውን የነገስታት ስም ዝርዝርና የነገሱበትን ዓ.ም Huntingford (1993፣9-10) እንደሚከተለው አስቀምጠውታል፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1390 | The Minjo King | Minjiloch | Minjo |
| 1425 | Girra | | Gire |
| 1460 | The Adio King | | Odhe |
| 1495 | The shadda King | Shaddi | Sadi |
| 1530 | Madi Gafo | Shonge | Madi Gafine |
| 1565 | The Bonga King | Borrete | Bong-he |
| 1605 | Giba Nechocho | Bonge | Giba Ninok |
| 1640 | Gali Gafocho | | Gali Ginok |
| 1675 | Gali Ginocho | Gali Ginocho | Tan Ginok |
| 1710 | Gaki Gaocho | Otti Sheroch | Taki Gaok |
| 1742 | Gali Gaocho | Kanechoch | Galli |
| 1775 | Shagi Sherocho | Gali Keffoch | Sagi Saro |
| 1795 | Beshi Ginocho | Kaye Sheroch | Beshi Gino |
| 1798 | Hotti Ginocho | Beshi Gino | Oto |
| 1821 | Gaha Nerocho | Gali Sheroch | Ganecho |
| 1845 | Gawi Nerocho | Haji Ginoch | Gaul Saro |
| 1854 | Kaye Sherocho(Kamo) | | Kamo |
| 1870 | Gali Sherocho | | |
| 1890 | Gaki Sherocho,deposed in 1897 by Menelik of Abyssinia. | | |

## 3.4. የካፋ ጥንታዊ አልባሳትና ጌጣጌጥ

የካፋ ህዝብ ከንጉሱ አንስቶ እስከታችኛው ህዝብ ድረስ የተለያዩ አልባሳት እንደነበሯቸው እና የወንድ፣ የሴትና የልጆች አልባሳትም የተለያዩ እንደሆኑ Bieber “The traditional costumes of the men, women and children were different.” (1984:59) በማለት ገልጸውታል፡፡ ሴቶቹም በዘንግ ላይ ፈትለው እጅግ የሚያምሩ ልብሶችን እንደሚሰሩ “At the ancient spindle and pulled the threads, from which she wove the precious sheets of clothes with her agile, skiful fingers from the thick ball of cotton.” (1984:59) በማለት ገልጸውታል፡፡ ሴቶቹ በወገባቸው ላይም ልብሳቸውን ሰብስብ አድርጎ ለመያዝ መቀነትም ያስሩ ነበር፡፡ የካፋ ንጉስ ዘርፉ በመሬት የሚሳብ እና በተከታይ ልጅ የሚያዝ ረዥም ካባ እንደሚለብስ እና በላዩም ላይ የብር ክዋክብት እንደነበሩበት Lange (1982፣117) ይገልጻሉ፡፡



ጥንታዊው የካፋ ነገስታት ዘውድ

የካፋ ወንዶች አልባሳት ነጭ ሆነው ብዙን ጊዜ መስመሮቹ በቀለም የተኽጎረጎሩ እንደነበሩ Bieber (1984:59) “The big,white ciothes for men were usually interweaved with colourful strips.” በማለት ገልጸውታል፡፡ በተጨማሪም የካፋ ሴቶች ራሳቸውን ከዝናብ ለመከላከል ከላያቸው ላይ ከቅጠል ደርቀው የተሰሩ ግልድሞችን ይለብሱ እንደነበረ ገልጸዋል፡፡

ጌጣጌጥን በተመለከተ የካፋ ንጉስ በአንገቱ ላይ ከወርቅ የተሰራ ሰንሰለት እንደሚያደርግ፣ የብር ወይም የወርቅ ጎራዴ እንደሚይዝ፣ በራሱም ላይ በወርቅ እና በብር የተለበጠ የፍየል

ቆዳ፣ ሶስት ነጫጭ ላባዎች የተሰኩበት ዘውድ ያደርግ እንደነበር እንዲሁም ወርቅ የሚጠቀሙት ንጉሱ፣ የእርሱ ዘሮችና እርሱ የፈቀደላቸው ብቻ እንደነበሩ Lange (1982፣117) ገልጸዋል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚነሳው የካፋ ህዝቦች የፀጉር አሰራር ነው፡፡ የካፋ ህጻናት ሙሉ በሙሉ ተላጭተው ከማንጅራታቸው አካባቢ ትንሽ ፀጉር እያስቀሩ እንደሚሰሩ፣ ሴቶቹ ለአቅመ አዳም እስኪደርሱ ድረስ ሁለት ጥቅልል ፀጉሮች ከአንዱ ጆሯቸው እስከ ሌላኛው ጆሯቸው አድርገው እንደሚሰሩ፣ ሴቶቹ ፀጉራቸውን እንደሚያሳድጉ Bieber (1984፣59) ገልጸዋል፡፡

## 3.5. የካፊቾ ብሔረሰብ ማህበረ-ባህላዊ ሁኔታ

### 3.5.1. የካፊቾ ብሔረሰብ የጋብቻ ሥነ-ስርዓት

አንድ ህዝብ በተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ስርዓቶች ውስጥ የራሱ የሆኑ የባህል እሴቶች አሉት፡፡ ከነዚህ እሴቶች መካከል አንዱ የጋብቻ ሥነ-ስርዓት ነው፡፡ በካፊቾ ብሄር ውስጥ ሶስት የጋብቻ አይነቶች አሉ፡፡ እነዚህም እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

አንደኛው በቤተሰብ ፈቃድ የሚደረግ ጋብቻ ነው፡፡ የወንዱ ቤተሰቦች የጎሳ እኩልነትን ከግምት ውስጥ በማስገባት ልጃቸውን የምትመጥን ሴት ፈልገው ለማጋባት ይነሳሉ፡፡ በዚህም መሰረት በወንዱ ቤተሰብ በኩል ማኬ ኒሆ /Maakkee Nihoo/[1] ወደ ልጅቱ ቤተሰብ ተልኮ ልጃቸውን ለጋብቻ እንዲሰጡ በተደጋጋሚ ይጠየቃሉ፡፡ ይህ ጥያቄ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ የልጅቱ ቤተሰብም በበኩሉ የልጁን ሁኔታ፣ የቤተሰቡን ዘርና የጎሳዉን ደረጃ ያጠናል፡፡ ዘመድ አዝማዱን ያማክራል ከዚህ ውጣውርድ በኋላ ልጁ ለልጂቱ ቤተሰብ የሚስማማ ከሆነ የመቀበል ምላሽ ለማኬ ኒሆ ይሰጣል፡፡ “No yaferoo uuchoo hidibone; No yaroo kaamiyaa shaageebone”[2] ከተባለ ማኬ ኒሆ መመላለሱን ያቆማል፡፡ ለጋብቻ ስምምነት ላይ ከተደረሰ ለማኬ ኒሆ ቀጠሮ ይሰጣል፡፡ የወንዱ ልጅ ቤተሰቦች፣ ሚዜዎችና አጃቢዎች ከሀገር ሽማግሌዎች ጋር በመሆን በተሰጠው የቀጠሮ ቀን ልጅቱ ቤተሰብ ቤት

---

[1]ለሽምግልና የሚላኩ አባቶች

[2]የእጅ ጣታችን አምስቱን እንጥረግ ዘራችን ተባዝቶ እንጋባ ማለት ነው፡፡

ይደርሳሉ፡፡ የልጅቱ ቤተሰቦች በቤታቸው ያፈራዉን ድግስ ያዘጋጃሉ፡፡ እንግዶቹ እንደደረሱ ድግስ መጀመሪያ አይቀርብም፡፡ ልጅቱ ያለችበት ቦታ የአገር ሽማግሌዎችና ሚዜዎች በመሄድ ቀለበት ያስራሉ፡፡ ከዚህ በኋላ ልጅቱ የታጨች መሆኑ በሁለቱም ቤተሰቦች በኩል ዕውቅና ማግኘቱ ይረጋገጣል፡፡ ሽማግሌዎች በወሰኑት መሰረት ጥሎሽ ከወንዱ ቤተሰብ ለሴቷ ቤተሰብ ይሰጣል፤ ለሰርጉም ቀን ቀጠሮ ይያዛል፡፡

ከዚህ በኋላ ለሰርጉ የሚሆን ዝግጅት በሁለቱም ቤተሰብ በኩል ይዘጋጃል፡፡ በወንዱ በኩል የሚዘጋጀው ዝግጅት በጣም የላቀ ነው፡፡ ለልጅቱ የሚሰጠው ጌጣጌጥና አልባሳት ይዘጋጃል፡፡ በሰርጉ እለት የተዘጋጀዉን ጌጣጌጥና አልባሳት የመቁጠር ስነ-ስርዓት ይካሄዳል፡፡ የጎደለውን ለማሟላትም ሽማግሌዎች ዋስትና ይገባሉ፡፡ በዚህ ስምምነት ከተደረሰ በኃላ የሙሽራው አጃቢዎች ሙሽራውን በማጀብ ወደ ሙሽሪት ግቢ ያስገቡታል፡፡ ከሚዜዎች አንዱም ሙሽሪትን በጀርባው በማዘል ወደ ውጭ ያወጣታል፡፡ ከዛም አጃቢዎች ባዝራ ፈረስ በማቅረብ እንድትቀመጥ ያደርጋሉ፡፡ በባዝራው እንድትቀመጥ የሚደረግበትም ምክንያት ወላድ እንድትሆን ነው፡፡ ከዚያም በሁለቱም አቅጣጫዎች በግራና በቀኝ በሚዜዎች በመደገፍ ሙሽሪት ፊት ለፊት ስትሄድ ሙሽራው ከኋላ በማጀብ ይከተላል፡፡ ቀድሞ በተሰጠው ጥሎሽ ገንዘብ የተዘገጀው የአልጋ ልብስና የቤት ቁሳቁስ በበቅሎ ተጭኖ ይከተላቸዋል፡፡ ይህም ቁሳቁስ የሙሽሪት ቤተሰቦች ሰርጉ በተደረገ በአራተኛው ቀን ቡና በማፍላት ከሙሽራው ቤተሰብ ጋር የሚተዋወቁበት ነው፡፡

ሙሽራዎች በሰላም አንደገቡ ሴቶች ሙሽሪትን እንኳን ደህና መጣሽ በማለት በዘፈን ይቀበሏታል፡፡ እነዚህም ሴቶች በአበባዎች አጊጠው አንድ እንጨት መሀል ላይ በመትከል በሙሽሪት ጫጉላ ቤት ፊት ለፊት የቆመውን ሙሽራ ይዞራሉ፡፡ ከዚያ በኋላ አጃቢዎች በተዘጋጀላቸው ዋና ቦታ ከመግባታቸው በፊት በር ላይ ተቀምጠው እግራቸውን እንዲታጠቡ ይደረጋል፡፡ ሙሽራዎቹ ጫጉላ ቤት /ኮላ ከጦ/ ይገባሉ፤ ለሰርገኞችም ምግብና መጠጥ ይቀርባል፤ ይጨፈራልም፡፡ ሚዜዎች ሙሽራዎች በመኝታቸው መተኛታቸውን አረጋግጠው ይወጣሉ፡፡ ማታ ሙሽራዋ ክብረ ንፅህና ካላትና ጨኸት ካሰማለች የደስታ ጭፈራ ይቀልጣል ከሌላት ግን ልትገረፍ ትችላለች፡፡

በሚቀጥለው ቀን ሚዜዎች ከብዙ አጃቢዎች ጋር በመሆን ወደ ሙሽሪት ቤት ይሄዳሉ፡፡ በደም የተነከረው ጨርቅ ለናሙና ይቀርባል፡፡ በዚህም ወላጆቿ ይከበሩበታል፡፡ አጃቢዎች የተዘጋጀላቸውን ምግብና መጠጥ ከተጋበዙ በኋላ እንደ ሙሽራይቱ ቤተሰቦች አቅም

ከብትና ብር ለጎጆ መውጫ ይለገሳል፡፡ የልጁ ቤተሰቦችም ያላቸውን ይለግሳሉ፡፡ እስከ አራት ቀን ድረስ ሙሽሪት ከማንም ጋር የማትገናኝ ሲሆን በአራተኛው ቀን ግን ራሷ ቡና በማፍላትና ምግብ በማዘጋጀት ከሙሽራው ቤተሰብ ጋር ትተዋወቃለች፡፡ አዘጋጅታ ያመጣችውን ልብስና ቁሳቁስ ለአማቾቿ በማቅረብ ተመርቃ የቤተሰቡ አባል ለመሆኗ ዕውቅና ይሰጣታል፡፡

ሙሽራው ከሙሽሪት ቤተሰብ ጋር የሚተዋወቅበት ቀን እስኪደርስ ድረስ ከሙሽሪት ቤተሰብ ጋር አይገናኝም፡፡ ከሙሽራይቱ ቤተሰቦች ጋር የሚገናኝበት ቀን ሲወሰን ሙሉ ዝግጅት ከተደረገ በኋላ ለሙሽራው ቤተሰቦች ጥሪ ይደረጋል፡፡ በዚህ ጊዜ ሙሽራዎች ከሚዜዎችና አጃቢዎች ጋር በመሆን ማምሻውን ወደ ሙሽሪት ቤተሰቦች ቤት ይሄዳሉ፡፡ የሙሽሮች ዘመድ የሆኑ ሰዎች ከቤት ውጭ በተዘጋጀላቸው ቦታ ይቀመጣሉ፡፡ የሙሽራው አጃቢዎችና ሙሽራው የሚሽሪትን ዘመዶች ጉልበት በመሳም ይተዋወቃሉ፡፡ ከዛም ወደ ተዘጋጀላቸው ቦታ እንዲገቡ ይደረጋል፤ በመዝናናትም ሌሊቱን ያሳልፋሉ፡፡ በቀጣዩ ቀን ጠዋት ላይ ቁርስ ከተበላ በኋላ ለሙሽሪት እናትና አባት የተዘጋጀላቸው ስጦታ በሙሽራው በኩል ይቀርባል፡፡ የሙሽሪት ቤተሰብም ይመርቁታል፤ የቤተሰብነት ዕውቅናም ይሰጠዋል፡፡ የቡድን ውይይት (ጥር 18፣2006 ዓ.ም)

ሁለተኛው የጋብቻ ዓይነት የጠለፋ ጋብቻ ነው፡፡ ይህ ጋብቻ የሚከናወነው ወላጆች ልጅቱን ለመስጠት ፈቃደኛ ሳይሆኑ በሚቀሩበት ጊዜ፣ አግቢው ለጥሎሽና ለሌች ወጪዎች አቅም በሚያጣበት ጊዜ ነው፡፡ ጠለፋውም የሚከናወነው ለጋብቻ የተፈለገችው ልጅ ወደ ገበያ ወይም ውሃ ለመቅዳት በመትሄድበት ጊዜ ሲሆን ጎልማሶች ተሰብስበው መንገድ አድፍጠው በመጠበቅ ልጂቷን አስገድደው ይወስዳሉ፡፡ ለመውሰድ በሚታገሉበት ጊዜም በአብዛኛው የአካል ጉዳት ይደርስባታል፡፡ በዚህ ጊዜ በሁለቱ ወላጆች መካከል አለመግባባት ይፈጠራል፡፡ ሙሽራው የታወቁ ሽማግሌዎች ወደሚገኙበት ሩቅ ቦታ ሙሽሪትን ይዞ በመሄድ እና ሽማግሌ በመላክ እርቀ ሰላም እንዲወርድ ያደርጋል፡፡ ከዛም ጋብቻው ይፈጸማል፡፡ ከመተጫጨቱ በኋላ ያለው የሰርግ ስነ-ስርዓት ከመጀመሪያው ጋብቻ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

ሶስተኛው አይነት ጋብቻ በሁለቱ ተጋቢዎች መፈላለግና መፈቃቀር የሚፈጸም ነው፡፡ በዚህም የጋብቻ አይነት የሚካሄደው የሰርግ ስነ-ስርዓት ከሁለቱ የጋብቻ አይነቶች ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ የሻረግ ተክሌ (ቃለመጠይቅ፣ጥር 17፣2006 ዓ.ም)

በአሁኑ ወቅት ባይኖሩም ከሶስቱ ጋብቻዎች በተጨማሪ ሌሎች የጋብቻ አይነቶች ነበሩ፡፡ እነዚህም ባህላዊ የእምነት አባቶች ልጃገረዶችን በገጸበረከትነት አምጥተው ለባል በመስጠት የሚደረግና ታላቅ ወንድም በሚሞትበት ጊዜ ሀብቱን ሌላው ሰው ገብቶ እንዳይወርስና ልጆችም በባዕድ እጅ እንዳያድጉ በማሰብ በይፋ ለህዝብ ሳይታወቅ የሚደረግ የጋብቻ አይነት ነበር፡፡ የቡድን ውይይት (ጥር 18፤2006 ዓ.ም)

## 3.5.2. የካፌቾ ብሔረሰብ የለቅሶ ሥነ-ስርዓት

በካፌቾ ብሔረሰብ አንድ ሰው ሲሞት የድረሱልኝ ጥሪ የሚተላለፈው ከእንጨት ተፈልፍሎ የተሰራን ገንዳ እንደ ደወል በመምታት ነው፡፡ በጥሪው መሰረትም በመንደሩ ውስጥ የሚኖሩ ወንዶች ቀጥሎም ሴቶች ይደርሳሉ፡፡ ሟች ያገባች ወይም ያገባ ከሆነ የሩቅ ዘመድ እስኪሰበሰብ ድረስ የቀብሩ ስነ-ስርዓት አይፈጸምም፡፡ እስከዚያው ድረስ ወንዶችና ሴቶች ለየብቻቸው ክብ በመስራት በለቅሶ ስነ-ስርዓት ጊዜ የሚዘወተረውን ዜማና ውዝዋዜ ያካሂዳሉ፡፡ ይህ ዜማ የሴቶቹ ጎሞ /Gommoo/ ሲባል የወንዶቹ ደግሞ ሂቾ /Hichoo/ ይባላል፡፡

በለቅሶ ጊዜ የሟች ቅርብ ዘመዶች ሁሉ ፀጉራቸውን ይላጫሉ፤ በአንገታቸው ላይ ነጭ ክር ያስራሉ፤ ልብሳቸውንና ነጠላቸውን በጥቁር ክር ያቀልማሉ፡፡ ከቀብር በኋላ ለረጅም ጊዜ (ከወርም በላይ ሊሆን ይችላል) ጎረቤትና ዘመድ አዝማድ ምግብና መጠጥ ያቀርባሉ፡፡ ይህ ተግባር ከጉርብትናና ከዝምድና በተጨማሪ እንደ ብድርም ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በቀለ (1996፤52-53)

የሀዘኑ ክዋኔ በሞተው ሰው የስልጣን ደረጃ ወይም የዘር ሀረግ የሚወሰን ነው፡፡ በዚህም መሰረት ከነገስታት ዘር የሆነ ሰው ወይም ነገስታት በሚያርፉበት ጊዜ የሚኖረው የለቅሶ ስነ-ስርዓት የተለየ ነው፡፡ ካፋ በንጉስ በምትመራበት ወቅት አንድ ንጉስ በሚሞትበት ጊዜ የሚክረቾ /Mikkirecho/[3] አባል የሆነ በሚቀጥሉት ዘመናት ካፋን የሚያስተዳድር ሰው ተገምግሞ ስልጣኑን ከተረከበ በኋላ ሁሉም ሰው እንዲያውቀው በአርቸራሻ /Aricheraasha/[4] አማካኝነት የንጉሱን ማረፍና በምትካቸው ሌላ መተካቱን በአደባባይ ይፋ

[3] የምክር ቤት አባል ማለት ነው፡፡

[4] የማስታወቂያ ሀላፊ

ይደረጋል፡፡ ከዛም ለ12ቱ ወራፎዎች /Woraafoo/[5] ጥሪ ተደርጎ በወራፌራሾ /Woraafee rashoo/[6] አማካይነት ፈረሰኞችና አጃቢዎች ወደ ቤተ መንግስት ገብተው ሀዘናቸውን ከገለጹ በኋላ አስክሬኑ ወደሚያርፍበት ሾሻ (ጠሎ ወረዳ የሚገኝ ቀበሌ) ተወስዶ ሞጎ /Moogo/ በሚባል ልዩ የነገስታት መቃብር ስፍራ ላይ እንዲያርፉ ይደረጋል፡፡

የተለያዩ የፈረስ አልባሳትና ጌጣጌጦች እንዲሁም የጦር መሳሪያዎች በመቃብሩ ዙሪያ ይተከላሉ፡፡ ከዚያ በኋላ በዋናው የልቅሶ ቦታ ትልቅ አዳራሽ ይሰራል፡፡ በዚህም አዳራሽ ውስጥ ሟቹ በህይወት ዘመናቸው ይገለገሉባቸው የነበሩ አልባሳትና ጌጣጌጥ እንዲሁም የጦር መሳሪያዎች ለህዝብ በሚታይ መልኩ ይቀመጣሉ፡፡ በርካታ ፈረሶችም የተለያዩ ጌጣጌጦችን ተላብሰው በአደባባይ እንዲወጡ ይደረጋል፡፡ ከዚህ ዝግጅት በኋላ እያለቀሱ ሀዘናቸውንና ለንጉሱ ያላቸውን ፍቅር ይገልጻሉ፡፡

ከለቅሶው ቀጥሎ ወንዶች ለብቻ ሴቶች ለብቻ እንደየመጡበት አካባቢ በህብረት በመሆን ወንዶቹ ጦርና ጋሻ በመያዝ ክብ ሰርተው ባልተለያየ የእግር አረጋገጥ እና ሻመቶ ተብሎ በሚታወቀው ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ታጅበው ሂቾ የሚባለውን ማስተዛዘኛ ዘፈን /ሙሾ/ ያወርዳሉ፡፡ በሂቾ ወቅት የሚገጠመው ግጥም የሟችን ክብርና ዝና፣ ደግነትና ጀግንነት የሚያንጸባርቁ ናቸው፡፡ ሴቶችም እንደዚሁ በየቡድናቸው በመሆን ከበሮ እየመቱ ጎሞ በመባል የሚታወቀውን የሴቶችን የማስተዛዘኛ ዘፈን ይዘፍናሉ፡፡ የሚገጥሙትም ግጥም እንደወንዶቹ የሟቹን ዝና፣ ደግነትና ጀግንነት የሚያንጸባርቁ ናቸው፡፡ በመጨረሻም ወንዶቹ ወደ ሴቶቹ በመሄድ ተቀላቅለው በጋራ የማስተዛዘኑ ሁኔታ ይቀጥላል፡፡ በላይበሽ ተክሌ (ቃለመጠይቅ፣ጥር 19፣2006 ዓ.ም)

የእምነት አባቶች በሚሞቱበት ጊዜ የሚኖረው የቀብር ስነ-ስርዓትም የተለየ ነው፡፡ በመጀመሪያ አላሞው በጠና ሲታመም ከዋናው መኖሪያ ቤቱ ውጪ ወደ ፊት ሌላ ሰው የማይኖርበት አዲስ ቤት ተሰርቶ በክብር እንዲያርፍ ይደረጋል፡፡ ነፍስና ስጋው ሲለያይም ወዲያውኑ ለህዝብ ይፋ አይደረግም፡፡ ምክንያቱም በሟቹ ላይ የነበረው መንፈስ በሌላ ሰው ላይ እስኪያርፍ ባህላዊ ፀሎት እየተደረገ በሚስጢር መጠበቅ ስላለበት ነው፡፡ በህልምና በተለያዩ ምልክቶች መንፈሱ የሚያርፍበት ሰው ከተለየ በኋላ ሰውየው በሚስጢር ጥበቃ

[5]ክፍለ ግዛት

[6]የክፍለ ግዛት መሪዎች

ይደረግለታል፡፡ ከዛም ለቀብሩ አስፈላጊ የሆኑ ዝግጅቶች ተደርጎ ከተጠናቀቀ በኋላ የእምነት መሪው ሞት በይፋ ለህዝብ ይገለጻል፡፡ አገላለጹም እንደ እምነት መሪው ማዕረግና ደረጃ ይወሰናል፡፡ ለምሳሌ የእምነቶች የበላይ ጠባቂ ወይም መራቂ በሚሞቱበት ጊዜ ጥሪው በመላው ካፋ ግዛትና በአጎራባች ቤንች ማጂ፣ ዳውሮና ሸካ እንዲሁም የእምነቱ ተከታዮች ባሉበት ሌሎች አካባቢዎች ሁሉ ጥሪው ይተላለፋል፡፡ ጥሪው የተደረገላቸው ህዝቦች ለቀብር በተወሰነው ቀን በፈረሰኞች ታጅበው በቦታው ይደርሳሉ፡፡

መንፈሱ ያረፈበት ሰው ለህዝቡ በይፋ ባለመገለጹ ጠዋት ላይ የለቅሶና የሀዘኑ ሁኔታ የደመቀ አይሆንም፤ መንፈሱ እንዲቀርብ በፀሎት ይለመናል፡፡ ከዛም በቃል አቀባዩ በኩል መንፈሱ ያረፈበትን ሰው ማንነት ለሀዘንተኞች ይነገራል፡፡ ከዚህ በኋላ መንፈሱ ያረፈበት አዲሱ ሰው ከፊት፣ ከኋላና በሁለቱም ጎኖቹ በአራት ጃንጥላ ታጅቦ ለህብረተሰቡ ይገለጻል፡፡

የተወሰኑ ሰዎች አስክሬኑ ወዳረፈበት ቤት በመግባት አስክሬኑን ይገንዙታል፡፡ መንፈሱ በይፋ በመገለፁ ህዝቡ ከለቅሶ ይልቅ ደስታቸውን ‹‹Woohoo emiiritone woohoo ejjoominote››[7] በማለት ይገልጻሉ፡፡ የመቃብሩ ዝግጅት መጠናቀቁ በቃል አቀባዩ በኩል ሲገለጽ ህዝቡ ሀዘኑን በደመቀ ለቅሶ ይገለጻል፡፡ ከዛ በኋላ አስክሬኑ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡ ለቀብሩ ስርዓት የተዘጋጁ ሁለት ኮርማዋች በፈረሰኞችና በህዝቡ ታጅበው ከአስክሬኑ ፊት ለፊት እየተነዱ ወደ እምነት አባቶች መቃብር ቦታ ይወሰዳሉ፡፡ ከዛም ሁለቱ ኮርማዎች ዳቦ /Dabbo/ በሚባለው ባህላዊ ስርዓት መሰረት ልባቸው ተሰንጥቆ ወጥቶ ከአስክሬኑ ጋር ይቀበራል፤ የቀረው የኮርማዎቹ ስጋ በመቃብሩ ጎንና ጎን ይሰቀላል፡፡ ወደ መቃብሩ ስፍራ የሚሄዱ ሰዎች የተወሰኑ ጎሳዎች ሲሆኑ ሌሎቹ ከሩቅ ይመለሳሉ፡፡ ምክንያቱም ባህሉ ከሚፈቅድላቸው ጎሳዎች በስተቀር በመቃብሩ አካባቢ መድረስ ያስቀስፋል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ወደዚህ የመቃብር ስፍራ በድጋሚ የሚኬደው ተተኪው የእምነት መሪ ሲሞት ብቻ በመሆኑ ስፍራው በክብርና በእምነት ይጠበቃል፡፡

አዲሱ የእምነት መሪ  መቃብሩ ቦታ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሚደርሰው በዛች የቀብር እለት ብቻ ሲሆን በህይወት እያለ የቀብር ቦታውን በድጋሚ የማየት እድል የለውም፡፡ በበፊቱ የእምነት መሪ የቀብር ስርዓት ላይም እንዲቆይ ስለማይፈቀድለት ሚቹ

---

[7]ደስ ብሎናል፣ እንደወተት ሁነዋል ማለት ነው፡፡

የሚቀበርበትን ቦታ ለተመረጠው ጎሳ አሳይቶ መቃብሩ እንዲቆፈር መታወጁን ገልጾ ከአካባቢው ይሰወራል፡፡ ማህበረሰቡ ስለሚያምንበትና ስለሚፈራው በእምነት መሪዎች የመቃብር ስፍራ ዙሪያ ያሉት የተፈጥሮ ሀብቶች አይነኩም፡፡ በዚህ አይነት ሁኔታ የቀብር ሥነ-ስርዓቱ ከተፈጸመ በኋላ እንደ እምነት መሪው ስልጣንና አቅም ለሀዘኑ መስተንግዶ የሚሆን ምግብና መጠጥ ቀርቦ በዋናው የለቅሶ ዕለት ከሩቅ ለመጡ እንግዶች ቅድሚያ እየተሰጠ መስተንግዶ ይደረጋል፡፡ ተተኪው የእምነት መሪ የቀድሞውን የእምነት መሪ ሀብትና ስልጣን እንዲሁም የእምነቱን ተከታዮች ሙሉ ሀላፊነት ወስዶ የማስተዳደር ግዴታ ይጣልበታል፡፡

የክርስትናም ሆነ ሌሎች ሀይማኖቶች ከመስፋፋታቸው በፊት በካፊቾ ብሔረሰብ ከነገስታት እና ከእምነት መሪዎች ውጪ የሆነ ሰው በሚሞትበት ጊዜ እንዲያገለግል ማሾ /Maasho/[8] በየቀበሌው ተዘጋጅቶ ይቀመጥ ነበር፡፡ የቀብር ሥነ-ስርዓቱን ስንመለከት ደግሞ አንድ ግለሰብ በሚሞትበት ጊዜ ለቀብር ሁኔታዎች እንኪመቻቹ እና ዘመድ አዝማድ እስከሚሰበሰብ ድረስ ይፋ ሳይደረግ በሚስጢር ተጠብቆ ይቆያል፡፡ የሩቅ ዘመድ በሙሉ ጥሪ ከተደረገላቸውና ከመጡ በኋላ ዳስ ተጥሎ ለቅሶ ይጀመራል፡፡ ለቅሶውም ሂቾና ጎሞ ተደርጎለት አስክሬኑ በክብር ታጅቦ በማሾ የቀብር ሥነ-ስርዓቱ ይፈጸማል፡፡ ከወረዳ ወረዳ ወጥነት ባይኖረውም በአንዳንድ ወረዳዎች ዘመድ አዝማድ ተሰብስቦ በነጋታው ቄጭ ኤፎ /Qeeci eefo/[9] ይለቀሳል፡፡ ሟቹ የዳራት ሴት ልጅ ካለችው በለቅሶው ቀን አማች /የልጅ ባል/ ክብሩን ለመግለጽ በከፍተኛ አጀብ ይመጣል፡፡ ከለቅሶው በኋላ አማችና ሚስቱ ከለቅሶው ቤት አያድሩም ከነ አጀቦቻቸው መስተንግዶ ተደርጎላቸው ወደቤታቸው ይመለሳሉ፡፡

የማስተዛዘኑን ግዴታ የሚወጡት ከጎረቤት ውጭ የሆኑ የቀበሌው ነዋሪዎች ሲሆኑ በየቀኑ ስምንት ስምንት ሰዎች በማዓፎዎች /Maa'aafoo/[10] አማካኝነት እየተመደቡ ያስተናግዳሉ፡፡ የሟቹ ጎረቤቶችና ዘመዶች እስከ አራት ቀን ድረስ ከሟቹ ቤት የሚቀመጡ ሲሆን ይህም ስርዓት ጎፖ /Goppoo/ ተብሎ ይጠራል፡፡ የቡድን ውይይት (ጥር18፣2006 ዓ.ም)

---

[8]የቀብር ስፍራ

[9]ከዋናው ለቅሶ በኋላ በቀጣዩ ቀን የሚደረግ የማስተዛዘኛ ለቅሶ

[10]የለቅሶ ስርዓት አስተባባሪ ሲሆን በህብረተሰቡ ውስጥ ይከበራል ይደመጣል፡፡ በበዓላት ጊዜና በሌሎችም አደጋና እርድ ወቅት የእንስሳት ማጅራት/Dillo/ ቤቱ ድረስ በክብር ይላክለታል፡፡

### 3.5.3. የካፊቾ ብሔረሰብ የስራ ባህል

የካፊቾ ብሔረሰብ እንደ ማንኛውም ማህበረሰብ ኑሮውን ለማሸነፍ በጋራና በተናጠል የተለያዩ ስራዎችን ያከናውናል፡፡ የካፋ ኢኮኖሚ መሰረቱ የእርሻ ስራ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ የእርሻ ስራዎች በህብረትና በተናጠል ይከናወናሉ፡፡ ስለሆነም ቀለል ያሉ ስራዎች በተናጠል ሲከናወኑ ብዙ ጉልበት የሚፈልጉ እንደ ምንጣሮ፣ ከባድ የመሬት ማጽዳት ስራ፣ ሰፋፊ ቦታዎች ላይ የመዝራት፣ የማጨድና የመሳሰሉት ስራዎች ደግሞ በጋራ ይሰራሉ፡፡ ይህም በጋራ የመስራት ባህል ዳዶ፣ ደቦና ገነሞ በመባል ይታወቃል፡፡ በቀለ (1996፣50)

ዳዶ (Daado) የሚባለው በአንድ አካባቢ ያሉ ሰዎች በጠዋት ተሰብስበው የእያንዳንዱን ሰው ማሳ ተራ በተራ በህብረት የሚያጭዱበትና የሚመነጥሩበት ሒደት ሲሆን ደፎ (Dafoo) የሚባለው ደግሞ በዳዶ ጊዜ ከነበሩት የበለጠ ቁጥራቸው የሚበዙ ሰዎች ተሰብስበው ከቀኑ 6 ሰዓት ጀምሮ የሚያከናውኑት ሰፊ ተግባር ነው፡፡ ደፎና ዳዶ ህብረተሰቡ ችግሩን በጋራ እንዲወጣ የሚረዱና ህዝቡን የሚያስተሳስሩ የስራ ማቃለያ ዘዴዎች ናቸው፡፡ አንዱ ግለሰብ ማሳ በህብረት ሲሰራ የማይመጣ ካለ እሱም በተራው አይሄድለትም፡፡ በእነዚህ ተግባራት የማይካፈል ሰው በህብረተሰቡ ውስጥ ተቀባይነት አይኖረውም፤ በእርሱ ችግር ጊዜም የሚደርስለት ሰው አይኖርም፡፡ ይህ ደፎ እና ዳዶ በአብዛኛው ወንዶች እርሻ በሚያርሱበት ጊዜ የሚከናወን ነው፡፡

ደፎ በሴቶች አይከናወንም የራሳቸው የሆነ ዳዶ ግን አላቸው፡፡ ሴቶች በዳዶ የሚሰሩት ወንዶች ደፎ በሚያከናውኑበት ጊዜ ሲሆን ተግባራቸውም ምግብና መጠጥ ማዘጋጀት ነው፡፡ በለቅሶና በሰርግ ጊዜም እንደዚሁ በህብረት በመሆን ምግብና ቡና ያዘጋጃሉ፡፡ እንዳስፈላጊነቱም በአንዳንድ ወረዳዎች በአጨዳና በጉልጓሎ ጊዜ በዳዶ የሚሰሩበት ሁኔታ አለ፡፡ የቡድን ውይይት (ጥር18፣ 2006 ዓ.ም)

ሌላው የካፊቾ የስራ ባህል ገነሞ (Ganamoo) የሚባለው ሲሆን ይህም ለአጭር ስዓት ያክል በጉርብትና ያሉ ሰዎች የሚያደርጉት የህብረት ስራ ነው፡፡ ይህም ተግባር የሚከናወነው ወደ ሌላ ስራ ከመሄዳቸው በፊት ሲሆን ስራው አጨዳ፣ ምንጣሮ እና የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡ ይህን ስራ በጠዋት ካከናወኑ በኋላ ወደ ሌላ ስራ ይሰማራሉ፡፡

የካፊቾ ህዝብ በህብረት ከሚያከናውናቸው ስራዎች መካከል ቤት ስራ ተጠቃሽ ነው፡፡ አንድ ሰው ቤት በሚሰራበት ጊዜ የመጀመሪያውን ምሰሶ ለማቆም የህዝቡን እርዳታ ይጠይቃል፡፡ ህዝቡም ጥሪውን ተቀብሎ ለትብብር ይሄዳል፡፡ በዚህም መሰረት ህዝቡ አንድ ላይ በመሆን በወፍራም ሀረግና ገመድ በማሰር እየጎተቱ ምሰሶውን ከጫካ ያመጡታል፡፡ ከዛም በተዘጋጀው ጉድጓድ ውስጥ ቤቱ ወደ ፊት እንዳይዛመም በማለት በሽማግሌ ተመርቆ መጀመሪያ ወተት፣ ቅቤና የከብት እበት ጉድጓድ ውስጥ ከገባ በሁዋላ ያመጡት ሰዎች በአንድ ላይ እየዘፈኑ አንስተው ያቆሙታል፡፡ ለቤት ስራ የሚደረገው ደቦ ቀጣይነት ያለው ሲሆን ማገሩ በሚማገርበትና ክዳኑ በሚከደንበት ጊዜ ለቤት ክዳን የሚያስፈልጉትን ግብዓቶች በጋራ በማቅረብ ቤቱ እንዲከደን ከፍተኛ የሆነ ትብብር ያደርጋሉ፡፡

በዚህ ደቦ ላይ የሀገር ሽማግሌዎችም ከምሰሶ ጉተታ ጀምሮ ይሳተፋሉ፡፡ በጉተታው ወቅት አቅም የሌላቸው ሰዎች የሌሎችን ልብስ፣ ጦርና ብትር ከኋላ ሆነው በመያዝ ያበረታታሉ፡፡ ቤት በሚሰራበት ጊዜ የሚከናወነው የደቦ ስራ ትልቁ የህብረት ስራ አይነት ነው፡፡ ሴቶችም ለዚህ የደቦ ስራ የሚያስፈልገውን ምግብና መጠጥ ለማዘጋጀት ዳዶ ያከናውናሉ፡፡ ይህ ስራ በአንድ ሰው ወይም በጥቂት ሊከናወን ስለማይችል አብዛኞዎቹ የአካባቢው ሴቶች የዳዶ ተሳታፊዎች ይሆናሉ፡፡ በዚህ የማትሳተፍ ሴት በአካባቢው ማህበረሰብ ተቀባይነቷ አነስተኛ ነው፡፡ በእሷም የስራ ጊዜ ሌሎች ሴቶች አይሳተፉም፡፡

የወንዶችና የሴቶች የስራ ክፍፍልን በተመለከተ አብዛኛውን የቤት ስራ የሚያከናውኑት ሴቶች ሲሆኑ ከቤት ውጭ የሚሰሩ እንደ ምንጣሮ፣ እርሻ የመሳሰሉትን ደግሞ ወንዶች ይሰራሉ፡፡ አልፎ አልፎ ሴቶቹ ከባሎቻቸው ጎን በመሆን ጉልጓሎ በመጎልጎል፣ አረም በማርም፣ በአጨዳ ጊዜ እህል በመሰብሰብ፣ በመውቃትና በማበጠር ስራዎች ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ፡፡

የካፋ ዞን በደን የተሸፈነ በመሆኑ ለዱር አራዊት መራባት ምቹ ነው፡፡ የዱር አራዊትም ምግብ ፍለጋ የህብረተሰቡን ማሳዎችና እንስሳት ያጠቃሉ፡፡ በዚህ የተነሳ እንስሳትንና እህልን ከጥቃት ለመከላከል የዱር አራዊቶችን በህብረትና በተናጠል ማደን የተለመደ ነው፡፡ ለዚህም ተግባር የሚያስተባብር ደቢ ታቶ የሚባል መሪ ይመሰርታሉ፡፡ ይህም መሪ አደን በሚኖር ጊዜ የአደን ጥሪ ለማስተላለፍ ትሮ የተባለ የትንፋሽ መሳሪያ በመንፋት ጥሪ ያደርጋል፡፡ ይህ ጥሪ የሚደረገው አብዛኛውን ጊዜ ከስራ ውጪ በሆኑ ቀናት ስለሆነ ጥሪው

ሲደረግ የሚቀር ሰው አይኖርም፤ ሁሉም ተገኝተው ስራውን ያከናውናሉ፡፡ ጀማል አብዱ (ቃለመጠይቅ፣ ጥር19፣2006 ዓ.ም)

# ምዕራፍ አራት

## የካፊቾ ብሔረሰብ አልባሳትና ጌጣጌጥ

## 4.1. የካፊቾ ብሔረሰብ አልባሳት

ይህ ምዕራፍ በሁለት ንዑሳን ርዕሶች ተከፍሎ የቀረበ ሲሆን አልባሳቱ ከምን ከምን እንደሚሰሩ፣ በየትኛው የሰውነት ክፍል እንደሚውሉ እና የሚለበሱባቸው አጋጣሚዎች መቼ መቼ እንደሆኑ እገልጻለሁ፡፡

### 4.1.1. የካፊቾ ሴቶች አልባሳት

ጥናቱ ትኩረት ባደረገበት አካባቢ የሚገኙ ሴቶች ከማግባታቸው በፊት፣ ካገቡ በኋላና የወጣትነት ወሰናቸውን እስከሚሸጋገሩበት ጊዜ እንዲሁም እድሜያቸው እየጨመረ ሲሄድ የሚለብሷቸው ሀገረሰባዊ ልብሶች ምን ምን እንደሆኑ በዚህ ንዑስ ክፍል እንደሚከተለው ይቀርባሉ፡፡

#### 4.1.1.1. የልጃገረዶች ልብስ

- ❖ **ኪቶ /Kitto/**

በካፊቾ ብሔረሰብ ሴቶች ትዳር ከመያዛቸው በፊት ኪቶ የሚባል ልብስ ይለብሳሉ፡፡ ይህ ልብስ ከጥጥ የሚሰራ ሲሆን ሙሉ ነጭ ይሆንና በአንገት፣ በደረት አካባቢና በቀሚሱ የታችኛው ጫፍ ዙሪያ ላይ በሰማያዊና ቀይ ቀለም ጥለት ተሰርቶለት የሚለበስ ነው፡፡ በደረት ላይ ያለው ጥለት በተለምዶ ቪ ቅርጽ ብለን በምንጠራው መልክ የሚደረግ ሲሆን ሌሎቹ ጥለቶች ደግሞ ቀጥ ባለ መስመር የሚደረጉ ናቸው፡፡ እነዚህ ጥለቶች የሴቷን ብቸኝነት (አለማግባቷን) ይገልጻሉ ተብለው ነው የሚታሰቡት፡፡ ለዚህም ነው በቀሚሷ ላይ ያለው ጥለት በአንገቷ፣ በደረቷና በቀሚሱ ጫፍ ላይ የሚደረገው፡፡ አቶ ጀማል አብዱ ይህን በተመለከተ የሚከተለውን ይላሉ፡፡

> በቀሚሱ መስመር ላይ የሚኖሩት ቀለማት ቀይና ሰማያዊ ሲሆኑ መስመሮቹ በአንገቷ፣ በደረቷና በቀሚሱ ጫፍ ላይ የሚደረገው ሆን ተብሎ መስመሮቹን ለማራራቅ ነው፡፡ ምክንያቱም መራራቃቸው ብቸኝነታቸውን ያሳያል፤ ብቸኝነታቸው ደግሞ የልጅቷን

አለማግባትና ብቸኛ መሆኗን የሚወክል ምልክት ነው፡፡ (ቃለመጠይቅ፣ ጥር 9፣ 2006 ዓ.ም)

የቀሚሱ መስመር በቀይና ሰማያዊ ቀለም እንዲሆን የተመረጠው የካፋ ባንዲራ ውስጥ ያሉ ቀለማት በመሆናቸው ነው፡፡ የካፊቾ ሴቶች በአብዛኛው ቡሮ (Buroo)[11] ይታጠቃሉ፡፡ ይህችም ያላገባች ልጃገረድ ኪቶ ከለበሰች በኋላ ቡሮ ትታጠቃለች፡፡ ይህን ማድረጓም ልብሱን ሸክፎ ይይዝላታል፡፡ አንዲት ልጃገረድ ይህን ልብስ እየለበሰች ትቆይና እድሜዋ ለአቅመ አዳም ሲደርስ የጋብቻ ጥያቄዎች ይቀርቡላታል፡፡ ይህንን ጥያቄም ቤተሰቦቿ እንዲቀበሉና እንዲድሯት ከዛም ኪቶን ትታ ገመኖ የተባለውን ልብስ እንድትለብስ የመፈለግ ስሜት በቤተ ዘመዶቿ ላይ ይንጸባረቃል፡፡ በዚህም ጊዜ ለቤተሰቦቿ የሚከተለውን ግጥም በዘፈን ያስተላልፋሉ፡፡

52.[12] Aree malli gaawee tahetane kittoon
Aroon kichibu eke imbote gammannoon

እርሷ መልከ መልካም ለብሳለች ኪቶን
እርሱን ታውልቅ እስኪ ስጧት ገመኖን

ግጥሙ ኪቶ የምትለብስ ሴት ያላገባች ልጃገረድ እንደሆነች ይጠቁማል፡፡ ይህችም ልጃገረድ ለጋብቻ የደረሰች በመሆኗ ልጃገረዶች የሚለብሱትን ኪቶ የተባለውን ልብስ አውልቃ ያገቡ ሴቶች የሚለብሱትን ገመኖ እንድትለብስ መፈለግን ይገልጻል፡፡

የካፊቾ ብሔረሰብ ባህላዊ አልባሳት የመለበሻ አጋጣሚያቸው እየቀነሰ መጥቷል፡፡ ይህ ችግር በዚህ ልብስ ላይም የሚታይ መሆኑን የተገኘው መረጃ ይጠቁማል፡፡ በቀደሙት ዘመናት ኪቶ ለመልበስ የግድ የበዓላትን ቀን መጠበቅ አያስፈልግም ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን ይህ ልብስ እየተለበሰ ያለው በበዓላት ወቅት ነው፡፡ ከበዓላት ውጪ በሆኑት ጊዜያት በዘመናዊ መልኩ በፋብሪካ እየተዘጋጁ የሚወጡ ልብሶችን መልበስ እየተለመደ መጥቷል፡፡ ይህንንም በምልከታዬ ወቅት አረጋግጫለሁ፡፡

---

[11]መቀነት ማለት ነው፡፡

[12]በዚህ መልክ ከግጥሞቹ ፊት የተጠቀሰው ቁጥር በአባሪ ውስጥ የሚገኙበትን ቦታ የሚጠቁም ነው፡፡




ፎቶ ቁ.1 ኪቶ የለበሰች ልጃገረድ

#### 4.1.1.2. ያገቡ ሴቶች አልባሳት

❖ **ገመኖ** /Gammanno/

አንዲት የካፊቾ ሴት ካገባች በኋላ በፊት የምትለብሰውን ኪቶ ትታ ገመኖ ትለብሳለች፡፡ ገመኖ ከኪቶ የሚለየው በመስመሮቹ ብዛት ነው፡፡ ገመኖ ባለብዙ መስመር ተደርጎ የሚሰራ ሲሆን መስመሮቹም የተቀራረቡ ናቸው፡፡ በዚህም ልብስ ላይ የመስመሮቹ መቀራረብ የሚኖረውን ትርጉም ወ/ሮ በላይነሽ ተክሌ እንደሚከተለው ይገልጹታል፡፡

> "ገመኖ ከኪቶ ይለያል ልንል የምንችለው በመስመሮቹ መብዛት እና በመስመሮቹ መቀራረብ ነው፡፡ የመስመሩ መቀራረብ ለባል መቅረቧን የሚያሳይ ነው፡፡ መብዛቱ ደግሞ ካገባች ትወልዳለች ተብሎ ስለሚታሰብ ከአንድ ወደ ብዙነት መቀየሯን ለማሳወቅ የሚጠቅም ነው፡፡" (ቃለመጠይቅ፣ ጥር 9፣ 2006 ዓ.ም)

የካፊቾ ሴት የምታጌጠው ከእድሜዋ ጋር በሚሄድ መልኩ ነው፡፡ ስለዚህም ማንኛዋም ያገባች ሴት ገመኖ አትለብስም፡፡ በእድሜዋ ወጣት ካልሆነች በእሷ እድሜ ያሉ ሴቶች የሚያደርጉትን ልብስ ለብሳ ትወጣለች፡፡ ይህም የሚሆንበት ምክንያት ገመኖ በተለያዩ

ቀለማት ያጌጠ በመሆኑና ደምቆ ስለሚታይ ነው፡፡ በካፋ ባህል ደማቅ ልብሶችን ለብሳ የምትወጣው ደግሞ ወጣት ሴት ናት፡፡ ይህችም ወጣት ሴት ገመኖ የምትለብሰው በተለያዩ ክብረ በዓላት፣ በሰርግ፣ በክርስትና እና በተለያዩ መሰል ዝግጅቶች ወቅት ነው፡፡ ገመኖን የለበሰች ሴት ከታየችም፡-

6. Bi kittoon qajja'a gammannoon geddetan
   Bushiishoon shiya'a woddemi shaahitan

   ኪቶዋን አውልቃ ገመኖን ለብሳለች
   ልጆችንም ወልዳ ምትበዛ መስላለች

በማለት ይገጠምላታል፡፡ ቃላዊ ግጥሙ የሚያስተላልፈው መልዕክት የተገጠመላት ሴት የልጃገረድነቷን ወቅት አልፋ ለጋብቻ በቅታለች፡፡ ለወደፊትም ወልዳ ራሷን የምትተካ፣ ዘሯንም የምታበዛ ትመስላለች የሚል ነው፡፡

ይህ ልብስ በመሰሪያ ቁሱና ቀለሙ ለውጥ እየተደረገበት ይገኛል፡፡ በድሮ ጊዜ ከሱፍ ክር ይሰራ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ግን ከሳባ ክር እየተሰራ ይገኛል፡፡ ለለውጡ ምክንያት የሆነውም አስውቦ ለማቅረብ በመፈለጉ እንደሆነ አቶ ታደሰ ጊያ "ገመኖን በፊት የምንሰራው በሱፍ ክር ነበር አሁን ግን ከሳባ ክር እንሰራዋለን፤ ይህንን የምናደርገው እንዲያምር ነው፡፡ የሳባ ክር ልብስን ያደምቃል፡፡ የበለጠ እንዲያምርም ብልጭልጭ ክር እናደርግበታለን፡፡ ሴቶቹም ይህን ይወዱታል፡፡" (ቃለመጠይቅ፣ ጥር 15፣2006 ዓ.ም) በማለት ይገልጻሉ፡፡ ገመኖ የካፋ ባንዲራን በሚወክሉ ነጭ፣ ሰማያዊና ቀይ ቀለማት ይሰራ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ግን እነዚህ ቀለማት በአረንጓዴ መደብ ላይ እንዲያርፉ ተደርጓል፡፡ የዚህን ምክንያት አቶ መሰረት ተስፋየ "የካፋን ባንዲራ የሚወክሉት ቀለማት በአረንጓዴ መደብ ላይ እንዲያርፉ የተደረገው በዞኑ ምክር ቤት ተወስኖ ሲሆን ይህ የተደረገበት ምክንያትም አረንጓዴው የካፋን ልምላሜ እንዲገልጽ ተብሎ ነው፡፡" (ቃለመጠይቅ፣ጥር13፣2006 ዓ.ም)



ፎቶ ቁ.2 ገመኖ የለበሰች ወጣት

- ***ዎንደሮ*** /Wandero/

በፊት ገመኖ ስትለብስ የነበረች ሴት እድሜዋ እየጨመረ ሲሄድ ዎንደሮ የሚባል ቀሚስ ትለብሳለች፡፡ ቀሚሱ የሚሰራው ከጥጥ ሲሆን ሙሉ በሙሉ ነጭ ሆኖ በቀሚሱ የታችኛው ጫፍ ዙሪያ እንደ ልብሱ ባለቤት ምርጫ የተለያየ አይነት ጥለት ይኖረዋል፡፡ ይህም ቀሚስ ሰፊና ልቅ በመሆኑ በቡሮ ይጠብቃል፡፡ የመለበሻ ወቅቱን ወ/ሮ አምሳለ ማሮ እንደሚከተለው ገልጸውታል፡፡

> ዎንደሮ እናት ለሆኑ ሴቶች የሚለበስ ነው፡፡ ይህንን ልብስ የሚለብሱበት የራሱ የሆነ ጊዜ አለው፡፡ አንደ የሚከበር በአል ሲኖር ይህን ልብስ ለብሰው ይወጣሉ፡፡ በተለይም ደግሞ አንዲት የካፊቾ እናት ልጇን ከዳረች የሰርጉ ቀን ይህንን አውሮ ቆሮዶ (Awuro Qoredo)[13] ነው የምትለብሰው፡፡ ይህን የምታደርገው እናትነቷን ለመግለጽ ነው፡፡ ከሁሉም ተለይታ ደምቃ ትታይበታለች፡፡ (ቃለመጠይቅ፣ ጥር 13፣ 2006 ዓ.ም)

ዎንደሮ ከመለበሻ ወቅቱ ጋር በተያያዘ የእናትነት መገለጫ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ይህም የሆነው አንዲት እናት ልጇን ስትድር የምትለብሰው ዎንደሮ በመሆኑ ነው፡፡ ይህ ልብስ በየትኛውም እድሜ ያለች ሴት ልጇን ስትድር ትልበሰው እንጅ ከሰርግ ውጭ ባለው በየትኛውም የክብረ-በዓላት ወቅት የሚለበሰው በአማካኝ ከ35-65 እድሜ ባሉ ሴቶች ነው፡፡ ዎንደሮ የለበሰች እናትም፡-

---


[13]የሚጠለቅ ሙሉ ልብስ ማለት ነው፡፡

85. Wandero gedda baarooch kechetane
Qocechi no manee amoo gaawetane

ዎንደሮ አርጋ (ለብሳ) ለበዓል ወጥታለች
ቆጨቿ የኛ እህት ምን ያህል አምራለች

ተብሎ ይዜምላታል፡፡ ግጥሙም ዎንደሮን የለበሰች ሴት ለበዓል ስትወጣ ውበት እንደሚኖራት፣ ልብሱም እንዳሳመራት የሚገልጽ ነው፡፡

በካፊቾ ባህል ጣፖ /Xappoo/[14] መደረብ የተለመደ በመሆኑ ትልልቅ እናቶች ማንኛውንም ልብስ ከለበሱ በኋላ ከላይ ጣፖ ይለብሳሉ፡፡ ዎንደሮ የምትለብስ ሴትም ለክብሯ ስትል ጣፖ ትደርባለች፡፡ ጣፖውም እንደ ዎንደሮው ሁሉ ከጫፍ ጥለት ይደረግለታል፡፡ በአብዛኛው ጣፖ የማይደርቡ ወጣቶች በመሆናቸው ዎንደሮ የለበሰች ሴት ጣፖ ካልደረበች ቀላል የሆነች (የተጋለጠች) ተደርጋ ትቆጠራለች፡፡ በየትኛውም አጋጣሚ የሚሰጣት ክብር ጣፖ ከለበሰችው ሴት ጋር እኩል አይሆንም፣ ይቀንሳል፡፡




ፎቶ ቁ.3 ዎንደሮ የለበሰች እናት


❖ ዳዶ /Daddoo/

እናቶች እድሜያቸው እየጨመረ ሲሄድና እርጅና ሲመጣ ከስራ እየራቁ ይመጣሉ፣ ወደ ገበያ መውጣታቸውንም ያቆማሉ፡፡ በዚህ ጊዜ በፊት ይለብሷቸው የነበሩ ልብሶችን መልበስ

[14] በቀሚሱ ላይ የሚደረብ ነጠላ

ያቆሙና ዳዶ የሚባል ከጥጥ የሚሰራ ቀሚስ መልበስ ይጀምራሉ፡፡ ዳዶ ረጅምና ሰፊ ሲሆን ልክ እንደ ዎንደሮ ከታች ጥለት ይደረግለታል፡፡ ከዎንደሮ የሚለየው የሚደረግለት ጥለት ቀይ ብቻ በመሆኑ ነው፡፡ ጥለቱን በቀይ ብቻ ማድረግ በልምድ የመጣ ሲሆን ቀሚሱ ረጅምና ሰፊ በመሆኑ ያለ ቡሮ አይለበስም፡፡ የቀሚሱ ጥለት ከታች ብቻ የሚሆንበት ምክንያት የምትለብሰው ሴት በዕድሜ እየገፋች የሄደች በመሆኗ እርጅናዋን ለመጠቆም ነው፡፡ ዳዶ በየትኛውም ቦታ ሊለበስ ይችላል፡፡

ይህንንም በተመለከተ ወ/ሮ የሻረግ ተክሌ "ሰው እድሜው እየገፋ በሄደ ቁጥር ለሞት ይቀርባል፤ ስለዚህም የምትለብሰው ቀሚስ ጥለት ለመሬት የቀረበ ነው፡፡ ምክንያቱም በሞቷ ጊዜ ወደ መሬት መመለሷ ስለማይቀር ነው፡፡" (ቃለመጠይቅ፣ጥር 7፣2006 ዓ.ም) በማለት ይገልጻሉ፡፡ በተገኘው መረጃ መሰረት በአሁኑ ወቅት ዳዶ እየተለበሰ አይደለም ማለት ይቻላል፡፡ በምልከታዬም ወቅት ዳዶ የለበሱ ሴቶች አላየሁም፡፡




ፎቶ ቁ.4 በእድሜ የገፉ እናቶች የሚለብሱት ዳዶ

- **ዮኮ /Yokkoo/**

ሴቶች ስራቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ የስራ ልብስ ይለብሳሉ፡፡ ከስራ ልብሶቻቸው አንዱ ዱቦ /Dubbo/ ሲሆን በሁለት አይነት መልኩ የሚዘጋጅ ነው፡፡ አንዱ ለወንድ እንዲሆን ተደርጎ የሚዘጋጅ ሲሆን ሌላው ደግሞ ለሴት የሚሆን ነው፡፡ ለሴቶች የሚዘጋጀው የዱቦ አይነት በቀጭኑ የሚገመድ ሲሆን ዮኮ ይባላል፡፡ ይህም ልብስ አንዱ ክብ፣ ሌላኛው ደግሞ ዝርግ ቅርጽ ያለው ሲሆን ክቡ በአንገት ተጠልቆ ከወገብ በላይ የሚሸፍን ነው፡፡ በዝርግ

ቅርጽ የሚዘጋጀው ደግሞ ማሰሪያ ተደርጎለት ሴቶች ስራቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ ከወገባቸው በታች ይታጠቁታል፡፡

ይህ ልብስ በሚዘጋጅበት ወቅት ለማህበረሰቡ የሚሰጠው ምልክት አለ፡፡ በካፊቾ ባህል አንዲት ሴት የወር አበባ የምታይበት ወቅት ከሆነ ከቤቷ ወጥታ በአንዲት ጎጆ ውስጥ ለብቻዋ ትቀመጣለች፡፡ በዚህም ወቅት የምትሰራው ብቸኛ ስራ ዮኮ ነው፡፡ ስለዚህም ከቃጫ የሚዘጋጀውን ዮኮ ስትሰራ የታየች ሴት የወር አበባ ጊዜዋ እንደሆነ ይታወቃል፡፡

ዮኮ የሚለበሰው ከቆሮጮ መፋቅ እና ከቦርዴ ማዘጋጀት ውጭ ያሉ ማንኛውም ስራዎች ሲከናወኑ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህም የመለበሻ ወቅቱ ከሌሎች የሴቶች አልባሳት የበዛ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ የሚከተለው ግጥም ተገጥሞለታል፡፡

73. Maache mulleechine yokkoo aalloon beetachan
    Maaxocho kexoocho aroon tahiyaaho shuunoon shuuniyaachan

    ሴት ልባም ናት ዮኮ አልባ አትኖርም
    በውጭም በቤትም እሱን ሳትለብስ ስራ አትሰራም

ይህ ግጥም ዮኮ በብዛት መኖሩን አመላካች ነው፡፡ የካፊቾ ሴትም ዮኮን አዘውትራ በመጠቀሚ ልባም ልትባል ችላለች፡፡ ይህን ልብስ ሳትለብስ ስራዋን እንደማታከናውን ግጥሙ ይነግረናል፡፡ በተጨማሪም ልብሱ የሚለበሰው በቤት ውስጥም ሆነ በውጭ በሚሰሩ ስራዎች ወቅት መሆኑን ከግጥሙ እንረዳለን፡፡



ፎቶ ቁ.5 ዮኮ የለበሰች ሴት

❖ ሸቆ /Sheqqo/

በካፊቾ ብሔረሰብ ዘንድ የእንሰት ተክል ከምግብነት አልፎ ለልብስ የሚሆኑ ውጤቶች ይገኙበታል፡፡ ከዚህ ተክል ከሚገኙ ልብሶች አንዱ ሸቆ ነው፡፡ ይህ ልብስ በአብዛኛው የሚዘወተረው የእንሰት ተክል በብዛት በሚያበቅሉ ደጋማ አካባቢዎች ላይ ሲሆን ሴቶች ቆጮ ለማዘጋጀት እንሰት ሲፍቁ እና ቦርዴ ሲያዘጋጁ ይህን ሸቆ የተባለ ልብስ ይለብሳሉ፡፡ እንሰት ለመፋቅ ወይም ቦርዴ ለመጥመቅ በሚፈልጉበት ጊዜ የእንሰቱን ቅጠል በእጃቸው በቀጫጭኑ በመተልተል አዘጋጅተው በወገባቸው ላይ ያገለድሙታል፡፡

ሸቆ የሚያገለግለው በተዘጋጀበት እለት ለሚከናወን ስራ ብቻ ነው፡፡ አንዴ ከተጠቀሙበት በኋላ ዳግመኛ አይለብሱትም፤ ስለሚደርቅ አውልቀው ይጥሉታል፡፡ የልብሱ መለበስም ሁለት ፋይዳዎች አሉት፡፡ የመጀመሪያው ከንጽህና ጋር የተያያዘ ሲሆን በልብሳቸው ላይ ያለ ቆሻሻ ከሚዘጋጀው ምግብ ጋር እንዳይነካካ ለማድረግ መርዳቱ ነው፡፡ ሌላው ደግሞ ስራውን በሚያከናውኑበት ጊዜ ሸቆ ለብሰው ካልሰሩ ቆጮው አይጣፍጥም ተብሎ ስለሚታመን ለምግቡ ጣዕም መስጠቱ ነው፡፡ "ሸቆ ሳትለብስ የምትሰራ ሴት ከታየች ያችን ሴት ማህበረሰቡ ይንቃታል፤ በእሷ እጅ የተዘጋጀ ቆጮ አይመገቡም ቦርዴውንም ቢሆን አይጠጡላትም፡፡" ወ/ሮ አረንጌ ያራንጎ (ቃለመጠይቅ፣ ጥር 4፣2006 ዓ.ም)

በካፊቾ ህዝብ ቆጮ እጅግ ተወዳጅ እና ተዘውታሪ ምግብ በመሆኑ ሸቆ የሚደረግበትን አጋጣሚ የሰፋ አድርጎታል፡፡ ምክንያቱም የቆጮ ጣዕምና የምታዘጋጀው ሴት ክብር ከምትለብሰው ሸቆ ጋር የተቆራኘ ተደርጎ ስለሚወሰድ ነው፡፡ ይህንንም ለመግለጽ ማህበረሰቡ የሚከተለውን ያዜማል፡፡

28. Sheqqo gaawucha'a qoccoon quccaabeeti
    Dubbiyoona aricheti bi kishoo gaaweti

    ሸቆን አሳምራ ቆጮን የምትፍቀው
    ባገር የታወቀች እጇም ያማረ ነው

ግጥሙ ሸቆን ለብሳ ቆጮ የምትፍቅ ሴት የምታዘጋጀው ቆጮ የሚጣፍጥ እንደሚሆንላት እና ባዘጋጀችው ምግብ አማካኝነትም የታወቀች ባለሙያ እንደሆነች የሚገልጽ ነው፡፡ ይህ ግጥም የሚዜመው እንደ ሰርግ፣ ክርስትና፣ ወዘተ ያሉ ዝግጅቶች በሚኖሩበት ጊዜ ሲሆን የሰራችውን እመቤት ለማመስገን እና ለማሞገስ ይገለገሉበታል፡፡



ሸቆ

ፎቶ ቁ.6 ሸቆ የለበሰች ሴት

## 4.1.2. የካፊቾ ወንዶች አልባሳት

ጥናቱ በተደረገበት አካባቢ የሚገኙ ወንዶች የሚለብሷቸው ሀገረሰባዊ አልባሳት በየትኛው እድሜ በሚገኙ ወንዶች እንደሚለበሱ፣ የሚለበሱበት አጋጣሚ እና ማህበራዊ ፋይዳቸው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ ያላገቡ እና ያገቡ ወንዶች የሚለብሱት ልብስ የተለያየ ባለመሆኑ አልባሳቱ የተከፋፈሉት እድሜን መሰረት በማድረግ ነው፡፡

### 4.1.2.1. የወጣት ወንዶች አልባሳት

- **ሾሮ**/Shoroo/

ሾሮ በወጣት ወንዶች ከሚለበሱት ልብሶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ይህ ልብስ ከተለያዩ የቀንድ ከብቶችና ከዱር አራዊት ቆዳ የሚዘጋጅ በጣም ለስላሳ ልብስ ነው፡፡ ሾሮ ዝርግ ሆኖ የሚዘጋጅ በመሆኑ ለማገልደም እንዲመች በሁለቱም ጫፎቹ ላይ ማሰሪያ ገመድ ይዘጋጅለታል፡፡ ከዚያም ከወገባቸው በታች አገልድመው ይለብሱታል፡፡ ይህንን የሚለብሱትም በአብዛኛው ቀፎ በሚሰቅሉበት ጊዜ ነው፡፡ ሾሮ ሁለት አገልግሎቶች ያሉት ሲሆን አቶ አሸናፊ ገ/ማሪያም እንደሚከተለው ገልጸውታል፡፡


> ከሾሮ አገልግሎት የመጀመሪያው ቀፎ ሰቅለው ወይም ቆርጠው በሚወርዱበት ጊዜ ኡዮ /Uuyo/ በሚባለው የቀፎ ገመድ ላይ በቀላሉ ተንሸራተው ለመውረድ እንዲችሉ የሚረዳ መሆኑ ነው፡፡ ሁለተኛው ጠቀሜታው ደግሞ በሚወጡበት ዛፍ ላይ ያለ እንጨት አካላቸውን እንዳይጎዳቸው ስለሚያደርግ ነው፡፡ (ቃለመጠይቅ፣ ሚያዝያ 13፣ 2006 ዓ.ም)

ሾሮን ከቀፎ ሰቀላ ጊዜ በተጨማሪም በክረምት ወራት እርሻ ለማረስ ሲወጡ ይለብሱታል፡፡ ጠንካራና ውሃን ወደ ገላ የማያስገባ በመሆኑ አገልድመው እርሻ ያርሱበታል፡፡ ከአገልግሎቱ በመነሳትም እንደሚከተለው ተገጥሞለታል፡፡

35. Shanafillon shunni shoroon shixxaayoote
Gubbicho aallegaata aaficho aalloone

ሸናፊሎ ወዳችሁ ሾሮን አትጥሉት
ኋለኛው ከሌለ የለምና የፊቱ

ይህ ግጥም የሾሮን አገልግሎት የሚገልጽ ነው፡፡ ይህንንም የሚያደርገው ሸናፊሎ የተባለውን ልብስ በማንጻሪያነት በመጠቀም ነው፡፡ ሸናፊሎ ትላልቅ አባቶች የሚለብሱት የማዕረግ ልብስ ሲሆን ሾሮ ደግሞ በቀፎ ሰቃዮችና በገበሬዎች የሚለበስ የስራ ልብስ ነው፡፡ የእነዚህን የሁለቱን ልብሶች አገልግሎት በመጠቀም ስለ ስራና ስለ ክብር ተነስቷል፡፡ ግጥሙም ያለስራ ክብር ስለማይገኝ ስራን አትጥሉ፣ ከክብር በፊት ስራ ይቀድማል የሚል መልዕክትን ይዟል፡፡




ፎቶ ቁ.7 በስራ ጊዜ የሚለበስ ሾሮ

- **ዱቦ /Dubbo/**

በወጣት ወንዶች የሚለበሰው ሌላው ልብስ ዱቦ ነው፡፡ ይህ ልብስ ከቃጫ የሚዘጋጅ ሲሆን ሴቶቹ ከሚለብሱት ዩኮ የሚለየው ሳይገመድ የሚለበስ በመሆኑ ነው፡፡ ዱቦ ክብ ቅርጽ ያለው ሆኖ በአንገት የሚጠለቅ ልብስ ነው፡፡ ይህ ልብስ በአብዛኛው እንደ ክት ልብስ የሚለበስ ነው፡፡ ወንዶቹ እንደ ለቅሶ፣ ገበያ እና ሌሎች ማህበራዊ ግንኙነቶች ወቅት ይህንን ልብስ ለብሰው የመሄድ ልምድ አላቸው፡፡ አልፎ አልፎ ደግሞ በስራ ጊዜ ይለብሱታል፡፡ በተለይም በክረምት ወራት እርሻ ለማረስ ሲወጡ ሙቀት እንዲሰጣቸው ዱቦ ይለብሳሉ፡፡

እንደኔ ያሉ ወጣቶች ስራ ሲሰሩ ዱቦ ይለብሳሉ፡፡ ምን መሰለሽ በተለይ ብርድ ሲሆን ሙቀት በመስጠት የሚወዳደረው የለም፡፡ ግን ትንሽ ለስራ ምቹ ያለመሆን ነገር ስላለው በብዛት የሚለበሰው ገበያ፣ ዘመድ ለመጠየቅ ሲኬድ ነው፡፡ ይህን ማለት ግን በስራም ጊዜ እንለብሰዋለን፡፡ ብዙ ጊዜ ባይሆንም አንተወውም፡፡ አቶ ፈቃዱ ጋዲሳ (ቃለመጠይቅ፣ ሚያዝያ 15፣2006 ዓ.ም)




ዱቦ

ፎቶ ቁ.8 ዱቦ የለበሰ ወጣት

- **ጎፈር** /Gofer/

በካፊቾ ባህል ሙሽራ ነጭ ቀለም ካለው ልብስ ውጭ ሌላ አይነት ቀለም ያለው ልብስ አይለብስም፡፡ ስለሆነም በልኩ የሚዘጋጅለትን ጎፈር ይለብሳል፡፡ ይህም ልብስ ከጥጥ የሚዘጋጅ ሲሆን የልብሱ ቀለም ሙሉ ነጭ ሆኖ በደረቱ አካባቢ፣ በእጅጌው፣ በጉልበቱ እና በላይኛው አላባሽ ጫፍ ላይ ነጭ፣ ሰማያዊና ቀይ ጥለት እንዲገባበት ይደረጋል፡፡ የጥለቶቹ መራራቅ የሚሰጠው ትርጓሜ ባይኖርም ነጭ፣ ሰማያዊና ቀይ ቀለማት የሚመረጡበት ምክንያት ግን የካፋ ባንዲራን የሚወክሉ በመሆናቸው ሀገሩን እንዲወድ ለማሳሰብ ነው፡፡ ልብሱ ሙሉ ነጭ ቀለም እንዲኖረው የሚደረግበት ምክንያት ደግሞ በካፋ ባህል ነጭ ቀለም የሰላም ምልክት ተደርጎ የሚወሰድ በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህም በሰርጉ ቀን ነጭ የለበሰ ሙሽራ በወደፊት የትዳር ህይወቱ ላይ ሰላም አብሮት ይገባል ተብሎ ይታመናል፡፡

የልብሱ ስያሜ ከቀለሙ ጋር የተያያዘ መሆኑን አቶ አሰፋ አለማየሁ "ለልብሱ ጎፈር የሚል ስያሜ የተሰጠበት ምክንያት በአካባቢው ካለው እምነት ጋር ተያይዞ ሲሆን ጎፈር ማለትም በአማርኛ ትርጉሙ ሰላም ማለት ነው፡፡" (ቃለመጠይቅ፣ ሚያዝያ 19፣ 2006 ዓ.ም) በማለት ይገልጻሉ፡፡ የአካባቢው እምነት ያሉትም ነጭ የሰላም ምልክት ተደርጎ መወሰዱን ሲሆን ጎፈር የለበሰ ሙሽራም፡-

74. Wo'ee gaxooch beeto goferina gaawe
    Worganoona yechi amoo emirikkiihe

ሙሽራዋ ጎን ያለው በጎፈር ተውቦ
በአግራሞት አስይዞ እንዴት ያስደስታል

እየተባለ ይሞገሳል፡፡ ግጥሙም ጎፈር ለሙሽራው ያጎናጸፈውን ውበት የሚገልጽ ነው፡፡ የሚያየው ሰው ሁሉ በቁንጅናው እንደተገረመ እና አስደሳች ሙሽራ እንደሆነም ግጥሙ ይነግረናል፡፡



ፎቶ ቁ.9 ጎፈር የለበሰ ወጣት

- ❖ **ካፊ ቆጨ ኮቶ /Kafi Qoce Kooto/**

ወጣት ወንዶች በተለያዩ በዓላት ጊዜ ካፊ ቆጨ ኮቶ የተባለ ልብስ የሚለስቡ ሲሆን ልብሱ በሰደርያ፣ በኮትና በሱሪ መልኩ የሚዘጋጅ ነው፡፡ ይህ ልብስ የተለያዩ ቀለማት ካለው ክር ይዘጋጃል፡፡ በዚህም መሰረት ልብሱ ነጭ ሁኖ በአረንጓዴ መደብ ላይ ነጭ፣ ሰማያዊ እና ቀይ ጥለት እንዲያርፍ ይደረጋል፡፡ እነዚህ ቀለማት የተመረጡበት ምክንያት የካፋ ባንዲራን የሚወክሉ በመሆናቸው ሲሆን በአረንጓዴ መደብ ላይ እንዲያርፍ የሚደረግበት ምክንያትም የካፋን ልምላሜ ለመግለጽ እንደሆነ አቶ አሰፋ አለማየሁ (ቃለመጠይቅ፣ ሚያዝያ 19፣ 2006 ዓ.ም) ይገልጻሉ፡፡

ልብሱ ልክ እንደ ገመኖ ሁሉ በመሰሪያ ቁሱ ለውጥ የታየበት ነው፡፡ እንደ አቶ ታደሰ ጊያ ገለጻ ይህ ልብስ በሱፍ ክር ይሰራ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ግን በሳባ ክር እየተሰራ ይገኛል፡፡



ፎቶ ቁ.10 ካፊ ቆጬ ኮቶ የለበሰ ወጣት

### 4.1.2.2. በዕድሜ የገፉ አባቶች አልባሳት

- ❖ ሸናፊሎ /Shanaafillo/

በካፊቾ ማህበረሰብ የእምነት መሪዎች እና ነገስታት ከነቤተሰቦቻቸው እንዲሁም የሚክረቾ አባላት በጥቅሉ ትልልቅ ሰዎች የሚባሉት የሚለብሱት የማዕረግ ልብስ አላቸው፡፡ ይህ የማዕረግ ልብስ ሸናፊሎ ይባላል፡፡ ሸናፊሎ የተለያዩ ቀለማት ካሉት የሱፍ ክር የሚዘጋጅ ሲሆን በአብዛኛው ከቢጫ፣ ቀይና ጥቁር ቀለማት ይዘጋጃል፡፡ ይህም የሚሆነው ሸናፊሎ ለብሶ የሚወጣው ሰው ከሌሎች ሰዎች በተለየ ደምቆ እንዲታይ ሲሆን ይህን ልብስ ለብሶ የታየን ሰው ማንኛውም የካፊቾ ህዝብ ያከብረዋል፤ በየትኛውም ቦታ ቢሆን ቅድሚያ ይሰጠዋል፡፡ ሸናፊሎ የለበሰ አባት ከላይ ማንኛውንም አይነት ፎጣ ይለብሳል፡፡ ይህም አለባበሳቸው አረቦ /Araboo/ በመባል ይታወቃል፡፡ ይህ ልብስ ከስራ ውጪ ባሉት በማንኛውም ጊዜያት የሚለበስ ነው፡፡

ይህ ልብስ በካፊቾ ብሔረሰብ ይለበስ የነበረው የካፋ የንግስና ዘመን በነበረበት ወቅት ሲሆን በአሁኑ ወቅት እየጠፋ የሚገኝ ልብስ ነው፡፡ አቶ አሰፋ አለማየሁ (ቃለመጠይቅ፣

ሚያዝያ 19፣ 2006 ዓ.ም)፣ ሻውጅራሻ አሸብር ሀይሌ (ቃለመጠይቅ፣ ጥር10፣ 2006 ዓ.ም)፣ አቶ አሰፋ ወ/ማሪያም (ቃለመጠይቅ፣ ጥር 14፣ 2006 ዓ.ም) እና ሌሎችም መረጃ ሰጭዎች ይገልጻሉ፡፡

የካፊቾ ብሔረሰብ ቃላዊ ግጥሞች በአብዛኛው አገልግሎትን መሰረት አድርገው የተገጠሙ እንደሆኑ ከተገኘው መረጃ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የሚከተለው ግጥምም በሸናፊሎ እና በሾሮ የመደረጊያ አጋጣሚና በሚሰጡት አገልግሎት ላይ ተመስርቶ የተገጠመ ነው፡፡

41. Shanaafillon tahee gochemtaa gettimmo mullaallo konine
Shoroono edde'i gaarooch hammi beeto amoommi anaamone

ሸናፊሎ ለብሶ አርሳለሁኝ የሚል ልብ አልባ ሰው ማነው
ሾሮንም ታጥቆ ከሰርግ የሚሄደው ምን ያለ ወንድ ነው

ይህ ግጥም ልብሶቹ መደረግ ከሚገባቸው ወቅት ውጭ መደረግ እንደማይገባቸው የሚገልጽ ነው፡፡ ሁለት መልዕክቶችንም ያዘለ ነው፡፡ የመጀመሪያው ሸናፊሎ የክብር ልብስ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን የሚሰራበት ቁስ ስስ በመሆኑ በእርሻ ወቅት አድርገውት ሊወጡ የማይቻል መሆኑን፣ ሾሮም እንደዚሁ ለስራ እንጂ ለሰርግ የሚለበስ የጌጥ ልብስ አለበሆኑን የሚገልጽ አንድምታ አለው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ አድራጊውን ሰው የሚወቅስ ነው፡፡ ልብሶቹን ማድረግ ያለበት የት እንደሆነ ለይቶ የማያውቅ ሰው ወንድ አይባልም፤ ከንቱ ሰው እንጂ የሚል መልዕክት የያዘ ነው፡፡



ፎቶ ቁ. 11 ሸናፊሎ

❖ **ተነፋነፍ** /Tanafaanafo/

በካፊቾ ባህል መሰረት አንድ ወንጀል ሲፈጸም በባህላዊ የእርቅ ሥነ-ስርዓት ይዳኛል፡፡ በዚህ የእርቅ ሥነ-ስርዓት ላይ በዳኝነት ቦታ የሚሰየሙ (የሚቀመጡ) አባቾች የሚለብሱት ልብስ አላቸው፡፡ ይህም ልብስ ተነፋነፍ ሲባል የፋብሪካ ውጤት ከሆነ ጥጥ ይዘጋጃል፡፡ ከላይ የሚደረበው አላባሽ እጅጌው ሙሉ በሆነ ሸሚዝ በልክ የሚሰራ ሁኖ በሁለቱም ጎኖቹ ቅድ እንዲኖረው ተደርጎ የሚዘጋጅ ነው፡፡ ሱሪው ደግሞ ከላይ ሰፊ ሆኖ ከጉልበት በታች በለባሹ ልክ አጥብቆ እንዲይዘው ተደርጎ የሚሰፋ ነው፡፡

> በእኛ ባህል መሰረት በማህበረሰቡ ዘንድ ተመርጦ ለባህላዊ ዳኝነት የሚቀመጥ ሰው ወደ ዳኝነት ቦታው ሲሄድ ተነፋነፍ የሚባለውን ባህላዊ ልብስ መልበስ ግዴታው ነው፡፡ ይህን ካላደረገ በተፈጠረው ችግር መካከል ገብቶ ፍርድ እንዲሰጥ አይፈቀድለትም፡፡ ሻውጅራሻ አሸብር ሀይሌ (ቃለመጠይቅ፣ጥር 10፣ 2006 ዓ.ም)

የካፋ ማህበረሰብ ተነፋነፍን ከእውነት ጋር ያያይዙታል፡፡ ስለዚህም ለዳኝነት የሚመረጡትና ይህንን ልብስ የሚለብሱት ቢያንስ እድሜያቸው ከሀምሳ በላይ የሆኑ አባቶች ናቸው፡፡ ሰው በዕድሜ እየገፋ ሲሄድ ውሸት፣ ክህደት ወዘተ. መሰል ነገሮችን ትቶ ለነፍሱ ኗሪ ይሆናል ተብሎ ስለሚታመን ነው ተነፋነፍ እንዲለብስ የሚፈቀድለት፡፡ ተነፋነፍ ለብሶ የሚፈርድ ሰው ልብሱ ይከብደዋል፤ አይዋሽም፤ የፈጠረውን አምላክ ይፈራል ብለውም ያምናሉ፡፡ ስለዚህም ታላቅ ክብር ይሰጠዋል፤ ማህበረሰቡን በእውነት እንደሚያገለግልም ይታመንበታል፡፡ ተነፋነፍ የለበሰ ሰው ጣፖ ይደርባል፤ በራሱ ላይ ጨርቅ ይጠመጥማል፤ ጭራና በትርም ይይዛል፡፡ ይህም የክብሩ መገለጫ ነው፡፡ ይህ ልብስ በሰዎች ላይ ምን ያህል ጫና የመፍጠር ሀይል እንዳለውም በቃላዊ ግጥም አማካኝነት እንደሚከተለው ተገልጿል፡፡

75. Konina tuneba asho kaareegata
    Kote gaata geeno tanafaanafoona
    Kaarem taane getti qajjemo aalloone

    ከምንም ጋር ቢሆን ሰው ከተጣላ
    ሽማግሌ ከተቀመጠ በተነፋነፍ
    እጣላለሁ ብሎ የሚተው አይኖርም

ግጥሙ የተነገረው ተነፋነፍ የተባለው ልብስ በማህበረሰቡ ዘንድ የሚሰጠው ቦታ ታላቅ እንደሆነ ለመግለጽ ነው፡፡ ለብሶት ለሚሰየመውን ባህላዊ ዳኛ የሚያጎናጽፈውን ክብርም

ይገልጻል፡፡ ምክንያቱም ዳኛው ማንኛውንም ጠብ ሊፈታ የሚችለው ልብሱን ሲለብስ ነውና፡፡ ግጥሙ የተጣሉት ግለሰቦች ተነፋነፍ የለበሰን ዳኛ ረግጠው መሔድ እንደማይቻላቸውም ጭምር ይገልጻል፡፡



ፎቶ ቁ.12 በዳኝነት ጊዜ የሚለበስ ተነፋነፍ

- **ካፊ ቆጨ ኮቶ** /Kafi Qoce Kooto/

አባቶች በበዓላት ጊዜ የሚለብሱት ልብስ ከወጣቶቹ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ በመሆኑም 4.2.1 ወጣቶች ይለብሱታል ተብሎ የተገለጸውን ካፊ ቆጨ ኮቶ የተባለ ልብስ ይለብሳሉ፡፡ የልብሱ መሰሪያ ቁስ፣ የመለበሻ አጋጣሚው እና ልብሱ ላይ ላሉት ለቀለማት የሚሰጠው ትርጓሜ ሁሉ ተመሳሳይ ነው፡፡

## 4.2. የካፊቾ ብሔረሰብ ጌጣጌጥ

ይህ ክፍል በአምስት ንዑስ ርዕሶች ተከፍሎ ቀርቧል፡፡ በውስጡም የሴቶችንና የወንዶችን ጌጣጌጦች፣ የጸጉር አሰራርና አቆራረጥ አይነቶች እንዲሁም ለቁሶቹ መለወጥና መጥፋት ምክንያት የሆኑ ጉዳዮች ከማህበረሰቡ አስተያየት ጋር ቀርበዋል፡፡

## 4.2.1. የካፊቾ ሴቶች ጌጣጌጥ

❖ **የወገብ ጌጦች**

በአሁኑ ጊዜ በዘመናዊነት እሳቤ ምክንያት ዘመናዊ ጌጣጌጦችን[15] የሚጠቀሙ ሴቶች እየበዙ ቢሆንም በካፊቾ ብሔረሰብ ባህል መሰረት ግን ያላገባች ሴት ምንም አይነት ጌጣጌጥ አታደርግም፡፡ ጌጣጌጥ ማድረግ የምትጀምረው ከሰርግ ቀን ጀምሮ ነው፡፡ ሙሽሪት ከሰርጓ ቀን ቀደም ብላ አባቷ የሚገዛላትን ጨሌ በምትፈልገው መልኩ ታዘጋጃለች፤ ስሙም ጊጆ /Gijjoo/ ይባላል፡፡ ይህ ጌጥ የተለያየ አይነት ቀለም ባለው ጨሌ የሚዘጋጅ ሲሆን ይህም የሚደረገው በአንድ አይነት ቀለም አያምርም በሚል ውበቱን ለመጨመር ታስቦ ነው፡፡

ይህ ጌጥ ሙሽሪት የተዳረችበትን የሰርግ አይነት ጠቋሚ ነው፡፡ ምክንያቱም እንድታደርገው የሚፈቀድላት የጊጆ መጠን እንደ ሰርጉ አይነት ይለያያል፡፡ ልጅቷ ያገባችው በቤተሰብ የመጣላትን ወንድ ከሆነ በወጉ መሰረት የተጋባች ሴት ናት ተብሎ ስለሚታመን የምታደርገው የጨሌ ብዛት በሌላ አይነት ሰርግ ያገባች ሴት ከምታደርገው ጊጆ የበለጠ ነው፡፡ ስለሆነም ባለሰላሳ ዙር ጨሌ ታደርጋለች፡፡ ራሷ ያመጣችውን ወንድ ቤተሰብ ተስማምቶበት የምታገባ ከሆነ ደግሞ ባለ ስምንት ዙር ጨሌ የምታደርግ ሲሆን ያመጣችውን ወንድ ቤተሰብ ያልወደደላት ከሆነና በግዴታ የምታገባ ከሆነ ባለ ሶስት ዙር ጨሌ ታደርጋለች፡፡ በሰርጓ ቀን ጊጆ ያላደረገች ሴት ቶኖ (የተረገመ) ልጅ ትወልዳለች ተብሎ ስለሚታመን የጨሌው ብዛት ይለያይ እንጂ ማድረጓ የግድ እንደሆነ አቶ በየነ በቀለ (ቃለመጠይቅ፣ጥር 8፣2006 ዓ.ም) ይገልጻሉ፡፡

በተጨማሪም ይህ ጌጥ በሰርጓ ቀን ሙሽሪት ለሚወጣላት ስም ወሳኝ ነው፡፡ ሙሽሪት ባለ ሰላሳ ዙር ጨሌ ያደረገች ከሆነች የተከበረች ናት ተብሎ ስለሚታሰብ የሚወጣላትም ስም ከክብሯ ጋር የሚመጣጠን ነው፡፡ ባለ ስምንትና ባለ ሶስት ዙር ጨሌ አድራጊዎችም እንደዚሁ በሚሰጣቸው የክብር ደረጃ መሰረት ይገባቸዋል ተብሎ የታሰበው ስም ይወጣላቸዋል፡፡ ይህም ጌጥ በጊዜ ብዛት በራሱ ተበጣጥሶ ካልወደቀ በስተቀር እስከለተሞት ድረስ ታደርገዋለች፡፡ በዚህም የተነሳ ማህበረሰቡ “የእድሜ እርዝማኔ ሰላሳ ዙር ጨሌ

---

[15]ዘመናዊ ጌጣጌጥ የተባሉት ከብርና ከወርቅ እየተዘጋጁ በየገበያው የሚሸጡትን ነው፡፡

ያስጨርሳል፡፡” የሚል አባባል አለው፡፡ የሚከተለው ግጥምም ሰላሳ ዙር ጨሌ ላደረገች ሙሽራ የተገጠመላት ነው፡፡

21. Shaashee guude gijjoon gedetane bushee
    Shimo eboominan indeen yeelliyaane

    ባለ ሰላሳ ዙር ጨሌን አርጋለች ልጅቷ
    መውለድ እንዲህ ነው እናት ማታሳፍሪቷን

የግጥሙ መልዕክት ከጋብቻው አይነት ጋር የተገናኘ ነው፡፡ ከላይ እንደተገለጸው ሙሽራዋ በወግ በማዕረግ አገባች የሚባለው በቤተሰቦቿ የመጣላትን ወንድ ስታገባ ነው፡፡ ባለሰላሳ ዙር ጨሌ የምታደርገውም በዚህ ጊዜ ነው፡፡ ስለዚህም ግጥሙ ባለሰላሳ ዙር ጨሌ ያደረገችውን ሴት የሚያሞግስ ሲሆን ከቤተሰቦቿ ፈቃድ ሳትወጣ ያገባች በመሆኗ ከራሷ አልፋ እናቷን እንዳስከበረች የሚገልጽ ነው፡፡



ፎቶ ቁ.13 ጊጆ ለመስራት የሚያገለግል ጨሌ

**ሸሾ /Shashoo/፡-** ይህ ጌጥ ከቁርበት፣ ዶቃ፣ ጨሌ፣ የዝሆን ጥርስ፣ የነብር ጠፍር፣ የአንበሳ ጎፈር፣ ዛጎል እና ቃጭል በአንድ ላይ በወፍራም ክር ላይ ተደርገውበት የሚዘጋጅ ጌጥ ነው፡፡ የሚደረገውም በአንደኛው ትክሻ በኩል አልፎ በወገብ እንዲወርድ ተደርጎ ነው፡፡ ሸሾ በውድ ጌጣጌጦች የተሞላ በመሆኑ የሚደረገው ለዝና ነው፡፡ በመሆኑም ሀብታም የሆነች ሴት ወደተለያዩ ቦታዎች ስትሄድ ሸሾ አድርጋ ሀብቷን ለሌሎች ታሳያለች፡፡ “ሸሾ ምታደርግ ሴት ሀብታም የሆነች ናት፡፡ ገንዘብ ያላት ካልሆነች ደሀ ሴት ላድርግ ብትል በውስጡ ያለውን ውድ ጌጥ ከየት ታመጣለች፡፡ ደግሞም ሸሾ ያደረገች ሴትኮ በእግሯ አትሄድም በበቅሎ እንጂ” አቶ በየነ በቀለ (ቃለመጠይቅ፣ጥር 8፣ 2006 ዓ.ም)፡፡ ሸሾ ያደረገች ሴት የሚከተለው ግጥም ተገጥሞላታል፡፡

77. Shashoon geddeet maacheen ciinaano konini
Showee toommooch beeti gaannoo taheti tone

*ሸሾን ያደረገች ሴት ማይመለከት ማነው*
*በሀገር ያለውን ሀብት የለበሰች አይደለችም ወይ*

የዚህ ግጥም መልዕክት ከላይ ከቀረበው ትንታኔ ጋር የተዛለደ ነው፡፡ ሸሾን የምታደርግ ሴት ሀብታም ናት፡፡ የምትሔደውም በበቅሎ በመሆኑ ለጌጡ መታየት አስተዋጽኦ አለው፡፡ እንደ አቶ በየነ በቀለ ገለጻ ከሆነ ይህች ሴት ሸሾ አድርጋ በበቅሎ ስትሔድ ጌጡ የሚያሰማው ድምጽ አለ በዚህ ጊዜ ታዲያ በምታልፍበት አካባቢ ያሉ ሰዎች ሁሉ ወጥተው ያዩዋታል፡፡ ምክንያቱም ያደረገችው ጌጥ በውድ ቁሶች የተሞላ ነውና፡፡ ግጥሙ የሚገልጸውም ይህንኑ ነው፡፡

❖ **የእግር ጌጥ**

**አሉቦ / Allubboo/**:- ይህ ጌጥ ያገቡ ሴቶች በእግራቸው ላይ የሚያደርጉት ነው፡፡ ጌጡ ከወርቅ፣ ከብርና ከነሐስ ሊዘጋጅ ይችላል፡፡ ከወርቅ የሚዘጋጀው አሉቦ አቼ አሉቦ /Aache Allubboo/፣ ከብር የሚዘጋጀው ብሬዌ አሉቦ /Birewee Allubboo/ ሲባል ከነሀስ የሚዘጋጀው ደግሞ ጊቦ አሉቦ /Gibbo Allubboo/ ይባላል፡፡ ይህ ጌጥ ብዙ ጊዜ ከአባቶች ለልጆች የሚሰጥ ስጦታ በመሆኑ የጌጡ አይነት እንደ ልጅቷ አባት የኢኮኖሚ ሁኔታ ይወሰናል፡፡ ይህንን በተመለከተ ወ/ሮ አገሬ በለጠ በሚከተለው መልኩ ይገልጹታል፡፡

> *የኔ አባት ለኔ የሚሰጠኝ አሉቦና የጓደኛየ አባት ለጓደኛየ የሚሰጣት አሉቦ ሊለያይ ይችላል፡፡ ምክንያቱም የጓደኛየ አባት ሀብታም ከሆነ የወርቅ አሉቦ ሊያደርግላት ይችላል፡፡ የኔ አባት ደግሞ እንደአቅሙ የብር ሊያደርግልኝ ይችላል፡፡ የግድ የወርቅ እንዲያደርግልኝ አልጠይቅም፤ የብር ለማድረግ ያልቻሉ የነሀስ የሚያደርጉም እኮ አሉ፡፡ (ቃለመጠይቅ፣ጥር 1፣ 2006 ዓ.ም)*

የአሉቦ የመደረጊያ ጊዜ የተወሰነ አይደለም፤ በማንኛውም ጊዜ ሊደረግ ይችላል፡፡ ነገር ግን በአሁኑ ወቅት የካፊቾ ጌጣጌጦች የመደረጊያ አጋጣሚያቸው እየቀነሰ በመምጣቱ ለብዙ ጌጦች መጥፋት ምክንያት እየሆነ ነው፡፡ የዚህ ሰለባ ከሆኑት መካከልም አሉቦ አንዱ ነው፡፡ ማህበረሰቡም ይህንን ሁኔታ በግጥም እየገለጸው ይገኛል፡፡ ቀጣዩም ግጥም ይህንኑ የሚገልጽ ነው፡፡

61. Andire gooroocha bull maache duubete
Allubboon qajji'i hulle baat sha'ete

በአሁኑ ጊዜ ሁሉ ሴቱ ተበላሽቷል
አሉቦውን ትቶ ባዶ እግር ተራምዷል

ከግጥሙ እንደምንረዳው በአሁኑ ወቅት የካፊቾ ሴቶች አሉቦን ማድረግ አቁመዋል፡፡ ግጥሙ የተዜመውም ይህንን በመቃወም ነው፡፡ አሉቦን የማታደርግ ሴት ባህሏን የተወች በመሆኗ “ተበላሽታለች” በመባል እየተወቀሰች ነው፡፡



ፎቶ ቁ.14 ብረዌ አሉቦ



ፎቶ ቁ.15 ጊቦ አሉቦ

❖ **የጣት ጌጥ**

**አጣሚቶ** / Axxaamittoo/፡- ከወርቅ፣ ከብርና ከነሀስ የሚዘጋጅ ሆኖ በትንሽ ጣት ላይ የሚደረግ ጌጥ ነው፡፡ የካፊቾ ህዝብ የሀብትን መጠን መሰረት በማድረግ ህዝቡን በሶስት ይከፍላል፡፡ የአላሞ /Allaamoo/[16] ቤተሰብ ወይም ሀብታም የሆኑትና የወርቅ ጌጥ የሚያደርጉት ኦጎጌ አሾ /Ogooge Asho/፣ መካከለኛ ገቢ ያላቸው እና የብር ጌጥ የሚያደርጉት ደግሞ ሸራሬ አሾ /Sharaare Asho/ ሲባሉ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውና የመዳብ ጌጥ የሚያደርጉት ጊሺሽ አሾ /Gishiishi Asho/ ይባላሉ፡፡ በዚህም መሰረት የካፊቾ ህዝብ ቀለበት የሚያደርገው እንደደረጃው ሲሆን ተበድሮ ከደረጃው በላይ የሆነ ጌጥ ያደረገ ሰው ካለ በማህበረሰቡ ይወገዛል፡፡ በተገለጸው ደረጃ መሰረት ከሆነ ግን አጣሚቶ በማንኛውም ወቅት ሊደረግ ይችላል፡፡

በድሮ ጊዜ የወርቅ ቀለበት እንዲያደርግ የሚፈቀድለት ንጉሱና የንጉሱ ቤተሰቦች (የማቶ /Maatto/፣ ሚንጆ /Minjjoo/፣ ሂናሮ /Hinnaroo/) ጎሳ የሆኑ ብቻ ነበሩ፡፡ ከንጉሱ ዘር ያልሆኑ ሌሎች የካፊቾ ህዝቦች ቢኖራቸውም ባይኖራቸውም የብር ቀለበት የሚያደርጉ ሲሆን

[16]የሀይማኖት መሪ

የነሐስ ቀለበት ማድረግ አይፈቀድም ነበር፡፡ ለዚህም ምክንያት የሆነውን ጉዳይ "በልተን ጠጥተን እያደርን ከብር ያነሰ ነገር ብናደርግ እግዚያብሄር ይጣላናል፤ በሀገራችን ላይም ችግርና መከራ እንጠራለን ተብሎ ስለሚፈራ ነው፡፡" አቶ ቆጭቶ ኢሞ (ቃለመጠይቅ፣ታህሳስ 30፣2006 ዓ.ም) በማለት ይገልጹታል፡፡ ከኦጎጌ አሾ ወገን የሆነች እና የወርቅ አጣሚቶን ያደረገች ሴት፡-

76. Axxaamitto beete ta genneenoochi kishooch
Aacheechone wotta phaqqi bi bekkeemooch

አጣሚቶ አለ ከእመቤቴ እጅ
የወርቅ ነው ደግሞ ደምቆ እንዲታይ

ተብሎ ተዘፍኖላታል፡፡ እመቤቴ የሚለው ቃል ታላቅ ከሚባል ወገን (ኦጎጌ አሾ) የምትመደብ መሆኗን አመላካች ነው፡፡ ይህን ትርጉም የሚሰጠውም ከሁለተኛው ስንኝ ጋር ሲጎዳኝ ነው፡፡ በተጨማሪም የወርቅ አጣሚቶን ያደረገችው ደምቆ ስለሚታይ ከየትነቷን እንዲገልጽላት መሆኑንም ይጠቁመናል፡፡

❖ **የእጅ ጌጥ**

ጎሾ /Gooshoo/፡- ከብር የሚሰራ ጌጥ ሆኖ በወፍራሙ ተሰርቶ በእጅ የሚደረግ ነው፡፡ ይህ ጌጥ በአድራጊው ልክ በክብ ቅርጽ ይዘጋጃል፡፡ አንዲትን የካፌቾ ሴት የለበሰችውን ጎሾ በማየት የሀብት መጠኗን ማወቅ ይቻላል፡፡ ጌጡ የሚደረገው በግራ እጅ ሲሆን ሀብታም ከሆነች በቁጥር ብዙ የሆነ ጎሾ በግራ እና በቀኝ እጇ ታደርጋለች፡፡ ጌጡን በብዛት የምታደርገው በበዓላት፣ በሰርግ ወቅትና አልፎ አልፎ ገበያ ስትወጣ ሲሆን ራሷን ከሌሎች ሴቶች ከፍ አድርጋ ለማሳየትና ለማጌጥ ትጠቀምበታለች፡፡




ፎቶ ቁ.16 ጎሾ

❖ **የአንገት ጌጦች**

**ጋፊዮ** /Gaafiyoo/ **እና ጊሺሺ ጊጃፎ** /Gishiishi Gijjaafo/፡- ጋፊዮ እና ጊሺሺ ጊጃፎ ሙሉ በሙሉ ከጨሌ የሚሰሩ ሲሆን በአንገት ላይ የሚደረጉ ጌጦች ናቸው፡፡ እነዚህ ጌጦች በአንድ ላይ የሚደረጉ (የማይለያዩ) ናቸው፡፡ ጋፊዮ የሚባለው ከትላልቅ ጨሌዎች የሚዘጋጅ ሲሆን ከትናንሽ ጨሌዎች የሚዘጋጀው ደግሞ ጊሺሺ ጊጃፎ ይባላል፡፡ እነዚህ ጌጦች የማይለያዩበት ምክንያት ከእናት የሚበረከቱ ስጦታዎች በመሆናቸው ነው፡፡ የሙሽሪት እናት ሴት ልጇን ስትድር ጋፊዮና ጊሺሺ ጊጃፎን ትሰጣታለች፡፡ ይህን ጌጥ የምትሰጣት ሙሽሪት በምትታጭበት ወቅት ሲሆን ጌጡን መስጠቷም ልጄ ብቁ ሆናለች፤ ትልቅ ሰው ሆናለች የሚል ትርጓሜን ይይዛል፡፡ ሙሽሪትም በውርስ መልክ ከእናቷ የተቀበለችውን ጋፊዮና ጊሺሺ ጊጃፎ ከሰርጓ እለት ጀምሮ በአንገቷ ላይ አድርጋ ታጌጥበታለች፡፡ ሴት ልጅ ወልዳ ስትድር እሷም በተራዋ ለልጇ እንደምታስተላልፈውም ወ/ሮ አምሳለ ማሮ እንዲህ ይገልጹታል፡፡

> እናት ለልጇ ጌጡን የምትሰጥበት ምክንያት እንደ አደራ ስለምትቆጥረው ነው፡፡ ጌጡ ከእናቷ የሚሰጣት ውርስ በመሆኑ እሷም ለልጇ በውርስ መልኩ ትሰጣታለች፡፡ ብዙ ልጆች ካሏት ደግሞ ጋፊዮውም ሆነ ጊሺሺ ጊጃፎው ሊያንሳት ስለሚችል ገዝታም ቢሆን ትሰጣለች፤ይህን የምታደርገው መስጠቷ እንደ ግዴታም ስለሚቆጠር ነው፡፡ አሁን ሙሽራ የምትሆነዋ እኮ ነገ ሴት ልጅ ይኖራታል፡፡ በዛን ወቅት ለልጇ ከየት አምጥታ ትሰጣታለች፡፡ (ቃለመጠይቅ፣ጥር 13፣2006 ዓ.ም)

የጌጡን ስጦታነት ልክ እንደናትየዋ ሁሉ ልጅቱም እንደግዴታ ነው የምትቆጥረው፡፡ ይህንንም በግጥም፡-

39. Gijjaafoo tunebaan taach ne immeemmo
Giisheebe oogebe amoon taan giddeemmo

ጊጃፎ ይሁን እንጅ ለኔ የምትሰጠኝ
ትንሹ ይሁን ትልቁ እኔ ምን ጨነቀኝ

በማለት ትገልጻለች፡፡ ግጥሙ ጊጇፎ እንዲሰጣት መፈለጓንና ስለሚሰጣት የጊጃፎ አይነት ግን አለመጨነቋን የሚገልጽ መልዕክት አለው፡፡




ፎቶ ቁ.17 ጋፊዮ እና ጊሺሺ ጊጃሮ

**ቲፎ** /Tiiffoo/፡- ይህ ጌጥ በአንገት ላይ የሚደረግ ሲሆን የተለያየ ቀለም ካላቸው ጨሌዎች እና ከዛጎል የሚዘጋጅ ነው፡፡ ቲፎ በውስጠኛው በኩል የቪ ቅርጽ ሲኖረው ከካፊቾ የአንገት ጌጦች ሁሉ ረዥሙ ነው፡፡ ይህን ጌጥ የሚያደርጉት የአላሞ ሚስቶች ብቻ ሲሆኑ በማንኛውም ጊዜ ሊያደርጉት ይችላሉ፡፡ ከሁሉም ጌጦች በተለየ ረዥም የሚሆንበት ምክንያትም ለአላሞ ሚስቶች ያለን ታላቅነት እና ማህበረሰቡ ለአላሞዎችም ሆነ ለአላሞ ሚስቶች ያላቸውን አክብሮት ለመግለጽ ነው፡፡ ወ/ሮ ቆጬች ኢሚቶ ስለ ጌጡ እንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡

> ቲፎ የሚባለው ጌጥ የአላሞ ሚስቶች ብቻ የሚያደርጉት ነው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ባለቤታቸው አላሞ በመሆኑ ነው፡፡ የአላሞ ስራ ማህበረሰቡ ከአምላኩ እንዲቀርብ ማድረግ ስለሆነ የተከበረ ነው፡፡ እኔም ሆንኩ ሌላው ሰው ያከብረዋል፡፡ ለዚህ ክብሩ መግለጫ ደግሞ ሌላ ሴት የማታጌጥበትን ቲፎ ሚስቱ በአንገቷ አድርጋ እንድታጌጥ ማህበረሰቡ ፈቅዶላታል፡፡ እንደኔ አይነቷ ይህን ጌጥ በፍጹም አታደርግም (ቃለመጠይቅ፣ጥር 3፣2006 ዓ.ም)

ቲፎን ከአላሞ ሚስት ውጭ የሆነች ሴት የማታደርግበት ምክንያት አላሞ የሀይማኖት መሪ በመሆኑ የአላሞ ሚስት ያደረገችውን ጌጥ ማድረግ ከእሷ ጋር እኩል ነኝ ብሎ ማሰብ በመሆኑ እሷንም ባሏንም መዳፈር ነው፡፡ አላሞን መዳፈር ደግሞ ሀይማኖትን መዳፈር ነው ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡ ሀይማኖትን መዳፈር ደግሞ ሀጢያት በመሆኑ ከዚህ ለመጠበቅ ስትል ይህን ጌጥ ከማድረግ ትቆጠባለች፡፡



ቲፎ

ፎቶ ቁ.18 ቲፎ ያደረገች የአላሞ ሚስት

❖ **የጆሮ ጌጥ**

**ጉቲቾ** /Guttiicho/፡- ከወርቅ፣ ከብር እና ከነሀስ የሚሰራ ሲሆን እንደየአቅማቸው በጆሯቸው የሚያደርጉት ጌጥ ነው፡፡ ይህ ጌጥ በአሁኑ ወቅት በተለያየ አይነት ቅርጽ መሰራት የተጀመረ ቢሆንም ከጥቂት አመታት ቀደም ብሎ ግን የሚሰራው በመስቀል ቅርጽ ብቻ ነበር፡፡ የዚህን ጌጥ ለውጥ በተመለከተ አቶ አሰፋ አለማየሁ "በእኔ እድሜ ይህ ጌጥ ከታች ክብ ጠፍጣፋ ነገር ተደርጎለት ከላይ በመስቀል ቅርጽ ነበር የሚሰራው፡፡ አሁን ግን በዘመናዊ መልክ በተለያየ ቅርጽ እየተሰራ ይገኛል፡፡ ሴቶቹም በማንኛውም ወቅት ያደርጉታል፡፡.....በመስቀል ቅርጽ መሰራቱም ከክርስትና እምነት ጋር የተያያዘ ነው፡፡" (ቃለመጠይቅ፣ጥር 19፣2006 ዓ.ም) በማለት ይገልጻሉ፡፡ በተወሰነ መልኩም ቢሆን አሁንም በመስቀል መልክ የሚሰሩ የጆሮ ጌጦች አሉ፡፡ በመስቀል ቅርጽ መሰራቱም ከክርስትና ሀይማኖት ጋር የተያያዘ እንደሆነ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

❖ **በእጅ የሚያዝ ጌጥ**

**ደንጊቺ ጌሾ** /Dengichi Geshoo/፡- ይህ ጌጥ የሚሰራው ከቃጫ ሲሆን ሞላላ ቅርጽ ያለው ሆኖ ለመያዣ የሚሆን ቀጭን ማንጠልጠያ የተበጀለት ነው፡፡ ደንጊቺ ጌሾ በእጅ የሚያዝ ሲሆን ማንኛዋም ያገባች ሴት ልትይዘው ትችላለች፡፡ ይህ ጌጥ ከጌጥነት ባለፈ ሁለት አገልግሎቶች አሉት፡፡ ለስንቅ ማቀበያነት መዋሉ የመጀመሪያው ሲሆን በቤት ውስጥ ለሴቶቹ የሽቶ ማስቀመጫ በመሆን ማገልገሉ ደግሞ ሌላው ጠቀሜታው ነው፡፡ ወ/ሮ አለሚቱ አያና የደንጊቺ ጌሾን ጠቀሜታ እንደሚከተለው ገልጸውታል፡፡

> ወንዶች ለእርሻ ስራ ሲሄዱ እኛ ደግሞ በቤታችን ውስጥ ሆነን ምግብ እናዘጋጃለን፡፡ ያዘጋጀነውን ምግብ ደግሞ ለባሎቻችን የመውሰድ ግዴታ አለብን፡፡ ምግቡን ለመውሰድ ደግሞ ደንጊቺ ጌሾ እንጠቀማለን፡፡ በእጅ የሚያዝ በመሆኑ ሸክሙን ያቀልልናል፡፡ (ቃለመጠይቅ፣ጥር 6፣2006 ዓ.ም)

ሴቶች በቤታቸው ውስጥ ያዘጋጁትን ምግብ በዚህ ቦርሳ ይዘው ወደ ባለቤታቸው ይሔዳሉ፡፡ የሚሔዱት በህብረት ነው፡፡ በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሴቶች ይህን ቦርሳ ይዘው ሲሔዱ ከታዩ፡-

60. Bunoon qullooch geddi dangichi gesh daggooch
Bo tiinjaanoon yechi dangichi gesh daggooch
Bo keneenon ciinooch hammitone goyooch

ቡናን በቁሎ አርገው ደንጊቺ ጌሾ ውስጥ
ስኒአቸውን ይዘው ደንጊቺ ጌሾ ውስጥ
ባላቸውን ሊያዩ ሄደዋል ከእርሻው

እየተባለ ይገጠምላቸዋል፡፡ ግጥሙም ለባለቤታቸው ይዘውት የሚሔዱትን መጠጥ ገላጭ ነው፡፡ ደንጊቺ ጌሾ ውስጥ ቡና ይዘዋል የተባለውም ቡና ብቻ ይይዙበታል ለማለት ሳይሆን የካፋ ሴት በምንም አይነት ሁኔታ ቡና ሳትይዝ ወደ ባሏ ስለማትሔድ ነው፡፡




ፎቶ ቁ.19 የሴቶች ቦርሳ (ደንጊቺ ጌሾ)

## 4.2.2. የካፊቾ ወንዶች ጌጣጌጥ

### 4.2.2.1. በአደን ጊዜ የሚደረጉ ጌጦች

- **የወገብ ጌጦች**

ወንዶች ወደ አደን ለመሄድ በሚወጡበት ጊዜ የተለያየ አገልግሎት ያላቸውን ቁሳቁሶች በአንድነት የያዘ ትጥቅ በወገባቸው ታጥቀው ያጌጣሉ፡፡ ቁሳቁሱን ለመያዝ የሚጠቀሙበት

ጂናሮ /Jinnaaro/ ከቆዳ የሚዘጋጅ ሲሆን ጌጣጌጦችን ለመያዝ የሚችሉ የተለያዩ ክፍሎች አሉት፡፡ ይህም ትጥቅ የሚከተሉትን ማጌጫዎች ይይዛል፡፡

**ሺኮ** /Shikkoo/፡- ሺኮ ከብረት የሚሰራ አንዱ ማጌጫቸው ሲሆን ከጌጥነቱም ባሻገር ግዳይ ከጣሉ በኋላ ስጋውን ለመቆራረጥ የሚጠቀሙበት ጩቤ ነው፡፡

**ኩሾ** /Kushoo/፡- ይህ ጌጥ ከብረት የሚሰራ ሲሆን እጀታው ደግሞ ከዝሆን ጥርስ ይሰራል፡፡ ይህን ትልቅ ጎራዴ ለአደን የሚወጡ ወንዶች እንደአቅማቸው በሚፈልጉት መጠን አሰርተው ይይዙታል፡፡ ከጌጥነቱም ባሻገር በችግር ጊዜ ራሳቸውን ለመከላከል ይረዳቸዋል፡፡ ይህ ጌጥ ከቆዳ በተሰራ ጎንኖ (Goninoo)[17] ውስጥ ተደርጎ በጂናሮ ይያዛል፡፡

**ባሩድ** /Baaruudo/፡- ባሩድ ከጌጥነቱ በተጨማሪ በምሽት እሳት ለማመንጨት የሚጠቀሙበት የለሰለሰ ድንጋይ ነው፡፡

**ቃጴቶ** /Qaapheto/፡- ቃጴቶ ከጌጥነቱ በተጨማሪ እሾህ ለመንቀል የሚገለገሉበት ቁስ ሲሆን ከብረትና ከእንጨት ይዘጋጃል፡፡

- **የእጅ ጌጦች**

**ቆፎ** /Qoofo/፡- ይህ ጌጥ በክብ ቅርጽ ከዝሆን ጥርስ የሚሰራ ሲሆን በክንድ ላይ የሚደረግ ጌጥ ነው፡፡ ቆፎ ከማጌጫነቱ በተጨማሪ ጦር ሲወረውሩ ክንዳቸው እንዲበረታና ሀይል እንዲሰጣቸው የማድረግ ጠቀሜታ አለው፡፡

**ጉጦ** /Guxoo/፡- ጉጦ ከአንድ ሜትር በላይ ሆኖ በእንጨቱ በኩል ጫፉ ላይ ዘንግ መሰል የብር ጌጥ ይደረግለታል፡፡ ይህንም የሚያደርጉት ለክብራቸው ነው፡፡


እነዚህ ቁሳቁሶች የተለያየ አገልግሎት ቢኖራቸውም በአንድ ላይ አብረው አደን ለሚወጣው ሰው ውበት የሚሰጡ በመሆናቸው እንደ ጌጥነት ያገለግላሉ፡፡ አንድን ወንድ ለማሞገስ ሲፈለግም እነዚህን ጌጦች መጠቀም የተለመደ ነው፡፡ ምክንያቱም ጌጦቹ የጀግንነት መገለጫ ተደርገው ይወሰዳሉና፡፡ ቀጣዩ ግጥምም ከነዚህ ጌጣጌጦች ውስጥ ጩቤና ኩሾን በመጠቀም የተገጠመ ነው፡፡

[17]ከቆዳ የሚሰራ ሆኖ በሚያዘው ጎራዴ ልክ ውስጡ ክፍት የሆነ ነው፡፡

32. Cooxooch xumooch getti shaton bekkiyano
Cuboona kushoonon magee mucciyaano
Ciixeti anaamo ebine no bushoo

አውሬ ምሽት ብሎ ፍርሃት ማያሳየው
ጩቤና ኩሾውን ከቤት የማያጣው
አዋቂ ወንዳወንድ የኛ ልጅ ይሄ ነው

ይህ የሙገሳ ግጥም ሲሆን ልጁ ጩቤና ኩሾ ከቤቱ የማይለየው በመሆኑ አይፈራም፤ ስለዚህም ሁሉን ነገር የሚያውቅ የወንድን ባህሪ የተላበሰ ነው፡፡ የሚል መልዕክትን የሚያስተላልፍ ነው፡፡




ፎቶ ቁ.20 በአደን ጊዜ የሚያዙ ጌጦች

### 4.2.2.2. በስራ ጊዜ የሚደረጉ ጌጦች

❖ የራስ ጌጦች

ኡኮ /Uko/፡- ይህ ጌጥ የጉሬዛን ቆዳ ከነፀጉሩ በመጠቀም የሚዘጋጅ ሲሆን በአደባባይ የሚለበስ ነው፡፡ የሚያደርጉትም ትልልቅ አባቶችና አዳኞች ናቸው፡፡ በተለያዩ በዓላት ጊዜ ከባህላዊ ልብሳቸው ጋር አድርገው ለጌጥነት ይጠቀሙበታል፡፡ በተለይም ፉከራና ሽለላ ማድረግ ሲፈልጉ ጀግንነታችንን ይገልጽልናል ብለው ስለሚያስቡ ያደርጉታል፡፡ ኡኮ ከጉሬዛ ቆዳ ብቻ ሳይሆን ከፍየልና ከበግ ቆዳም የሚዘጋጅ ሲሆን ከፍየልና ከበግ ቆዳ

የሚሰራው ኡኮ በአደባባይ አይለበስም፡፡ ምክንያቱም በቆዳቸው ላይ የሚገኘው ፀጉር አነስተኛና ውበቱ ያነሰ በመሆኑ ከጌጥነት ይልቅ በስራ ጊዜ ራሳቸውን ከዝናብ ለመከላከል ይጠቀሙበታል፡፡



ፎቶ ቁ.21 ኡኮ

**ኦጎ /Oggoo/፡-** በደጋማ አካባቢ በተለይ በክረምት ወራት የካፊቾ ወንዶች እርሻቸው በዝናብ ምክንያት እንዳይቋረጥ በራሳቸው ላይ በዝርግ ቅርጽ የሚሰራ ኮፍያ ይለብሳሉ፡፡ ዱቦ ከላይ ለብሰው ሾሮ ከታች አገልድመው ከላይ ከቀርቀሃ ሽፋን የሚዘጋጀውን ኦጎ (የዣንጥላ ያህል ስፋት ያለው ኮፍያ) በልካቸው አዘጋጅተው ያደርጋሉ፡፡ ይህም ከዝናብ ራሳቸውን ለመከላከል ይጠቅማቸዋል፡፡

በተጨማሪም በክረምት ወቅት ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ ይህንኑ የዝናብ መከላከያ ያደርጋሉ፡፡ እረኞችም እንደዚሁ በክረምት ወራት ይህንን ኮፍያ በማድረግ ከብት ሲጠብቁ ይውላሉ፡፡ በተለያዩ አካባቢዎች እንደሚታወቀው ሁሉ የካፊቾ እረኞችም የተለያዩ የቃል ግጥሞችን እየገጠሙ ያንጎራጉራሉ፡፡ ኮፍያውን በተመለከተም፡-

12. Phashee oggoon geddi gijjoon dabbitone
    Phixxaasho no bushoo amo gaawetone

    የቀርከሃ ኦጎ አድርጎ ከብቱን ተከትሏል
    ጎበዙ የኛ ልጅ እንዴት መልካም ሆኗል

በማለት ያንጎራጉራሉ፡፡ ግጥሙን የገጠሙት ራሳቸውን ለማሞገስ ሲሆን በግጥሙም አማካኝነት ከብት በመጠበቃቸው ጎበዝ እንደሆኑ፣ ይህንን ማድረግም የመልካም ልጅ ባህሪ መሆኑንና ኦጎው ያላበሳቸውን ውበት ገልጸዋል፡፡



ፎቶ ቁ.22 በራስ ላይ የሚደረግ ኦጎ

### 4.2.3. የካፊቾ ብሔረሰብ ህጻናት ጌጣጌጥ

❖ **የእጅ ጌጥ**

**ዛጎሎ** /Zaagoolo/፡- የህጻናት እጅ ላይ የሚታሰር ሲሆን ከቆዳና ከዛጎል የሚሰራ ነው፡፡ በህጻናት እጅ ላይ የሚደረግበት ምክንያትም ከጌጥነት ባሻገር ህጻናትን እንዲጠብቅ ተብሎ ነው፡፡ አንዲት የካፊቾ እናት ለልጇ ዛጎሎ ካደረገች ልጇን ከርኩስ መንፈስ እንደተከላከለችላት/ለት/ ታስባለች፡፡ ምክንያቱም በብሔረሰቡ ዘንድ ህጻኗ ይህን ጌጥ አድርጋ ብትወጣ የሰው አይን ጌጡ ላይ ስለሚያርፍ ያንን ሰው ተከትሎ የሚመጣ ርኩስ መንፈስ በጌጡ ላይ ያርፋል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡




ፎቶ ቁ.23 ዛጎሎ ያደረገች ህጻን

## 4.3. የካፊቾ ብሔረሰብ ሴቶችና ወንዶች የፀጉር አቆራረጥ እና አሰራር

በካፊቾ ብሔረሰብ የተለመዱት ባህላዊ የፀጉር አቆራረጥና አሰራር አይነቶች ከእድሜና ከማህበራዊ እርከኖች ጋር ተያይዘው የሚከወኑ ናቸው፡፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ ውስጥም የፀጉር አቆራረጥና አሰራር አይነቶቹ ምን አይነት እንደሆኑና ምን አይነት ማህበራዊ ትርጓሜ እንዳላቸው ቀርቧል፡፡

### 4.3.1. የሴቶች የፀጉር አቆራረጥና አሰራር

**ጌፖ /Geppoo/፡-** በአማካኝ ከአምስት እስከ አስራ ሁለት አመት የሚሆናቸው ሴት ህጻናት ይህን የፀጉር ቁርጥ ይቆረጣሉ፡፡ ጌፖ ከግንባር ጀምሮ እስከ አናት ድረስ ያለውን ፀጉር በክብ ቅርጽ በማስቀረት ዙሪያውን የሚላጭ የፀጉር ቁርጥ አይነት ነው፡፡ ህጻናት ጌፖ የሚቆረጡት የቅርብ የሆነ ዘመድ ሲሞትባቸው ብቻ ነው፡፡ ፀጉራቸውን በዚህ ሁኔታ ተቆርጠው እንዲቆዩ የሚደረገውም ሟቹ ከሞተበት እለት ጀምሮ እስከ አንድ ወር ብቻ ነው፡፡ የቅርብ ዘመድ በሚሞትመት ጊዜም በሀዘን እንደሚከተለው ያንጎራጉራሉ፡፡

82. Geppoo kuchebote bushiishena'ote
    Biiyeto qitite no aafooche aallete

    ጌፖን ተቆረጡ ልጆች ሆይ
    የታመመው ሞቷል ጠፍቷል ከፊታችን

ግጥሙ ዘመድ ስለሞተ ልጆች ጌፖን እንዲቆረጡ የሚያሳስብ ነው፡፡ ጌፖ የሀዘን መግለጫ እንደሆነም ከግጥሙ መገዳት ይቻላል፡፡



ፎቶ ቁ.24 ህጻናት የሚቆረጡት ጌፖ

**ጌንጎ /Gengoo/፡-** አንዲት ሴት ያላገባች ልጃገረድ ከሆነች ጌንጎ የሚባል የፀጉር አሰራር ትሰራለች፡፡ ይህ የፀጉር አሰራር በግራ ወይም በቀኝ በኩል ጫፍ ላይ ተጀምሮ በክብ ቅርጽ እየተሰራ ወደ መሀል የሚዘልቅ ነው፡፡ በመጨረሻም ክቡ እየጠበበ ይሄድና መሀል አናቷ ላይ ሲደርስ ያቆማል፡፡ ሴቷ ጌንጎ መሰራት የምትጀምርበት ወቅት ለመታጨት መድረሷን አመላካች ነው፡፡ በመሆኑም ወደ ውጭ ወጥታ ከጓደኞቿ ጋር መጫወቷን አቁማ ራሷን

እየጠበቀች ከእናቷ ጋር ቤት ውስጥ መዋል ትጀምራለች፡፡ በዚህ ወቅትም ትታጫለች፡፡ ባል ካገባች በኋላ ጌንጎ የተባለውን ስሬት መሰራት ታቆምና ዲጶ ትሰራለች፡፡

**ዲጶ** /Diphoo/፡- ዲጶ ፀጉሩ ሙሉ በሙሉ ከራሷ ጋር መጣበቁን ለመግለጽ የሰጡት ስያሜ ነው፡፡ ዲጶ የምትሰራ ሴት ከግንባሯ ጀምሮ እስከ መሀል አናቷ ድረስ ፀጉሯ እኩል ለሁለት ይከፈላል፡፡ ከዛም ለሁለት ከተከፈለው ፀጉር እያንዳንዱ ክፋይ እንደገና ለሁለት ተከፍሎ ወደ ጎን ይሰራል፡፡ ስሬቱም በግራ በኩል ሁለት በቀኝ በኩል ሁለት ሆኖ ጆሮዋ ድረስ የሚወርድ ይሆናል፡፡ ይህ የፀጉር ስሬት የሴቷን ማግባት አመላካች ነው፡፡ ለሁለት የመከፈሉና የመሰራቱ ተምሳሌትም ከአንድ ወደ ሁለትነት መቀየሯን ነው፡፡ ከአናቷ ጀምሮ ወደ ኋላ የሚቀረው ፀጉር ደግሞ ለአራት ተከፍሎ ይሰራል፡፡ ለአራት መሰራቷም ብቻዋን የነበረች ሴት ስታገባ ወደ ሁለትነት እንደተቀየረችው ሁሉ ወልዳ ዘሯ እንዲበዛ መፈለግን (ምኞትን) ገላጭ ነው፡፡

ጌንጎ ተሰርታ ስትሄድ አይቶ በፍቅሯ የወደቀ ወንድ እንደሚከተለው በማለት ያንጎራጉራል፡፡

4. Aallet taane bushoo
   Allet tanne hadur
   Amoommi shifone qellon bishippeto
   Amoommi pha'one phaqibeeto baroo

   ጠፍቻለሁ ልጄ
   ጠፍቻለሁ ዘንድሮ
   እንዴት ያለ ስሬት ነው ጸጉሯን የተሰራችው
   ኸረ እንዴት እንዴት ነው ሚያበራው ግንባሯ

ግጥሙ ፀጉሯ ላማረላት ሴት በደፈናው የተገጠመ ቢመስልም በካፊቾ ባህል መሰረት ግን ላላገባች ልጃገረድ ተገጠመ ተብሎ ነው የሚነገረው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ግጥሙ የተገጠመው አንዲትን ሴት በወደደ ወንድ በመሆኑና በባህሉ መሰረት ደግሞ ማንኛውም ወንድ ያገባችን ሴት እንዲመኛት፣ ቢመኛት እንኳን በይፋ እንዲገልጽ የማይፈቀድለት በመሆኑ ነው፡፡ ግጥሙም የተመለከታት ሴት የተሰራችው የፀጉር ስሬት ውበት እንደሰጣትና በውበቷም መማረኩን የሚገልጽ ነው፡፡



ምስል ቁ.25 ጌንነ



ምስል ቁ.26 ዲጶ

## 4.3.2. የወንዶች የፀጉር አቆራረጥ

ህጻናት ወንዶች 5.4.1 ላይ እንደተገለጸው አይነት ጌፖ የሚባለውን የጸጉር ቁርጥ ይቆረጣሉ፡፡ የሚቆረጡትም ከአምስት እስከ አስራ ሁለት አመት የሚሆናቸው ልጆች ናቸው፡፡ የሚቆረጡበት ወቅት እንደ ሴቶቹ ሁሉ የቅርብ የሆነ ዘመድ ሲሞትባቸው ሲሆን ፀጉራቸውን በዚህ ሁኔታ የሚያቆዩትም ለአንድ ወር ያክል ነው፡፡

**ቦሮ /Booro/፡-** ይህን የፀጉር ቁርጥ የሚቆረጡት ወጣት ወንዶች ናቸው፡፡ ቦሮ በፊት ለፊት በአናታቸው ላይ በክብ በክብ ቅርጽ አስቀርተው ሌላውን ፀጉር ሙሉ በሙሉ የሚቆረጡት የፀጉር ቁርጥ አይነት ነው፡፡ የሚተወው የፀጉር ክፍል ጠባብ በመሆኑ ከጌፖ ቢለየውም የመደረጊያ አጋጣሚው ግን ልክ እንደ ጌፖ የቅርብ የሆነ ዘመድ በሞት ሲለያቸው ብቻ ነው፡፡ ይህንን የፀጉር ቁርጥ ተቆርጠው ለአንድ ወር ያክል በገበያ ላይ ይታያሉ፡፡ የሚቆረጡበትም ሆነ በገበያ ላይ ወጥተው የሚታዩበት ምክንያት ሀዘናቸውን ለመግለጽ እና ዘመድ እንደሞተባቸው ላልሰማ ሰው ለማሰማት ነው፡፡

በምዕራፍ አራት በሰፊው ዳሰሳ የተደረገበት የካፊቾ ባህላዊ አልባሳት፣ ጌጣጌጥ፣ የፀጉር አቆራረጥና አሰራር ትንትና የቁሶቹን ስያሜ፣ የመሰሪያ ቁስ፣ የመደረጊያ አጋጣሚ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃዎችን፣ እሴቶችንና የለውጥ ሁኔታዎችን የገለጸ በመሆኑ በምዕራፍ ሁለት ከቀረቡት ትውሮች ጋር ይጠራራል፡፡

## 4.4. የአልባሳቱና የጌጣጌጦቹ የለውጥ ሁኔታና የማህበረሰቡ አስተያየት

ይህ ክፍል በዋናነት በቂሶቹ ላይ እየተደረገ ላለው ለውጥ መከሰት ምክንያቱ ምንድን ነው? በለውጡ ዙሪያ ማህበረሰቡ ምን አስተያየት አለው? ለውጡን ተቀብሎታል ወይስ ተቃውሞታል? ከተቃወመው ለውጡን ለመግታት ምን መደረግ አለበት ይላሉ? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት የተዘጋጀ ነው፡፡

በቀደሙት ምዕራፎች አልባሳቱና ጌጣጌጦቹ ለውጥ እየተካሄደባቸው መሆኑንና ወደ መጥፋት እያመሩ ያሉ ቂሶች መኖራቸው ተጠቁሟል፡፡ ይህ ጉዳይ በተለይም በከተማ አካባቢዎች በሰፊው የታየ ሲሆን በገጠር ቀበሌዎች ግን በስፋቱም ሆነ በፍጥነቱ የተሻለ ነው፡፡ በካፈቾ በቅርቡ ይደረጉ ከነበሩት ቂሶች መካከል ሙሉ በሙሉ የለውጥ አደጋ የደረሰበት ሴቶች በሰርግ ጊዜ ይለብሱት የነበረው ጎፈር የተባለው ልብስ ነው፡፡

ከአገልግሎት ውጭ ከሆነው ጎፈር በስተቀር ጥናቱ በተደረገበት አካባቢ አልባሳቱና ጌጣጌጦቹ ለውጥ የተደረገባቸውም ለውጣቸውን ይዘው ለውጥ ያልተካሄደባቸውም በነበሩበት ሁኔታ አሁንም ድረስ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡

የለውጡን ሁኔታ ስንመለከት ደግሞ የአልባሳቱም ሆነ የጌጣጌጦቹ ለውጥ የሚታየው በመሰሪያ ቁስና ቅርጽ፣ በቀለም ምርጫ፣ በብዛት መቀነስ እና በመለበሻ አጋጣሚ መቀነስ ነው፡፡ ስለለውጡ ሁኔታ የሽመና ባለሙያ የሆኑት አቶ ታደሰ ጊያ እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡

> የምንሰራበት መሳሪያ አልተለወጠም፤ የተለወጠው ልብሶቹን የምንሰራበት ቁስ ነው፡፡ በፊት አብዛኛውን ልብስ የምንሰራው በሱፍ ክር ሲሆን አሁን ደግሞ በሳባ ክር ነው የምንሰራው፡፡ በብዛት ደግሞ ብልጭልጭ ክሮችን እንጠቀማለን፡፡ የምንጠቀመው የክር ቀለም የግድ እንደድሮው የካፋን ባንዲራ የሚጠቁም ላይሆን ይችላል፤ እኛ ያምራል ብለን ያሰብነውን ቀለም እንጠቀማለን፡፡ (ጥር 15፣2006 ዓ.ም) በማለት ይገልጻሉ፡፡

ለባህላዊ አልባሳቱና ጌጣጌጦቹ መለወጥ ወይም መጥፋት በምክንያትነት ከሚነሱት መካከል ሀይማኖት፣ የዘመናዊነት እሳቤ (የአመለካከት ዝንፈት)፣ ለባህሉ ክብር አለመስጠት፣ ልብሶቹ በዘመናዊ ዲዛይን እየተሰሩ መቅረባቸው እና የዋጋ ውድነት የሚሉት ናቸው፡፡

የመጀመሪያው የለውጥ ምክንያት ሀይማኖት ነው፡፡ የሀይማኖት ተጽዕኖ የሚደርስባቸው በተለያየ አይነት ቀለም የሚሰሩ ልብሶች ናቸው፡፡ እነዚህ ልብሶች የሚሰሩበት የክር ቀለም

ደማቅና የተዥጎረጎረ በመሆኑ የሀይማኖት አባቶች ከጥንቆላ ጋር ያያይዟቸዋል፡፡ እነዚህ ሰዎች ደግሞ በማህበረሰቡ ዘንድ ተሰሚነት ያላቸው በመሆናቸው በልብሶቹ ላይ በቀላሉ ተጽዕኖ መፍጠር ችለዋል፡፡ ችግሩ የሚታየው በሁሉም የሀይማኖት ተከታዮች ላይ መሆኑ ደግሞ የለውጡን ሁኔታ የተባባሰ አድርጎታል፡፡ በሀይማኖት ምክንያት ልብሶቹ እየጠፉ መምጣታቸውን የተለያዩ የአካባቢው ነዋሪዎች ይናገራሉ፡፡ አቶ አስራት ሀይሌም የሚከተለውን ይላሉ፡፡

> ባህላዊ ልብሶቹ በቀይ፣ ነጭ፣ ሰማያዊና ጥቁር ቀለም የተዥጎረጎረ በመሆኑ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሁሉም ሐይማኖት ውስጥ የሚገኙ የሐይማኖት አባቶች እነዚህን ቀለማት ከጥንቆላ ጋር በማያያዝ ህዝቡ ይህንን ልብስ እንዳይለብስ እየከለከሉ ይገኛሉ፡፡ ጨሌዎችንም ቢሆን እንደዚሁ፡፡ (ቃለመጠይቅ፣ጥር 6፣2006 ዓ.ም)

ሁለተኛው ምክንያት የዘመናዊነት እሳቤ (የአመለካከት ዝንፈት) ሲሆን ይህም በብዛት በወጣቶች ላይ የሚስተዋል ነው፡፡ “ወጣቶቹ ባህላዊ ልብሶቹንም ሆነ ጌጣጌጦችን መልበስን እንደ ኋላቀርነት ይቆጥሩታል፡፡ አሁን አንድን ወጣት ባህላዊ ልብስ ልበስ ብትይው አይለብስም፡፡ ምክንያቱም ኋላቀር የሆነ መስሎ ይሰማዋል፡፡ ይህ ችግር በተለይም በከተማ አካባቢ የከፋ ነው፡፡” ወ/ሮ አቦነሽ አትርሴ (ቃለመጠይቅ፣ጥር 11፣2006 ዓ.ም)

በሶስተኛነት የሚነሳው ደግሞ ለባህሉ ክብር አለመስጠት (ልብሶቹን አሳንሶ ማየት) ሲሆን አቶ አስራት ሀይሌ ይህንን ችግር “የካፋ ህዝብ በተለይም ወጣቱ ስለባህላዊ ልብሶቹ የማወቅ ጉጉት የለውም፡፡ ለባህሉ ክብር ያለመስጠት ችግር አለ፡፡ ልብሶቹንም እንደዚሁ አሳንሶ ማየቱ ለልብሶቹ አለመለበስ ምክንያት ይሆናል፤ ካልተለበሱ ደግሞ ቀስ በቀስ እየጠፉ ነው የሚሔዱት፡፡” (ቃለመጠይቅ፣ጥር 12፣2006 ዓ.ም) በማለት ይገልጹታል፡፡

አራተኛው ምክንያት ደግሞ ልብሶቹ በዘመናዊ ዲዛይን እየተሰሩ መቅረባቸው ሲሆን ይህንንም በተመለከተ አብዛኞቹ የአካባቢው ነዋሪዎች የተቃወሙ ሲሆን የተወሰኑት ነዋሪዎች (የዘመናዊ ልብስ አዘጋጆችን ጨምሮ) ግን ልብሶቹ በዘመናዊ መልኩ መሰራታቸውን ከመቃወም ይልቅ ተቀብለውታል፡፡ ለዚህም ምክንያት የሚያደርጉት ሙሉ በሙሉ መለበሳቸው ከሚቀር በአማራጩ መጠቀም የተሻለ እንደሆነ እና ዘመናዊ ልብሶች በሌላ አካል (በባለሙያ) ተሰርተው በቀላሉ መገኘታቸውን ነው፡፡ ይህን ሀሳብ ከሚደግፉት መካከል አንዱ የሆኑት አቶ ታደሰ ጊያ ሀሳባቸውን በሚከተለው መልኩ ገልጸዋል፡፡

> ባህላዊ ልብሶችን በዘመናዊ መልኩ ሰርተን ማቅረባችን ባህላዊውን አያጠፋውም፡፡ በርግጥ ልብሶቹ በተወሰነ መልኩ የድሮ ይዘታቸውን ይለቃሉ፡፡ ግን ጭራሹን ከሚጠፉ በተወሰነ መልኩም ቢሆን ለውጥ ተደርጎባቸውና በዘመናዊ መልክ ተሰርተው ቢለበሱ የተሻለ ይሆናል፡፡ በፊት ጭራሽ የማይለበሱ የነበሩ ልብሶች በዘመናዊ መልክ በመሰራታቸው አሁን እየተለበሱ ነው፡፡ (ቃለመጠይቅ፣ጥር 15፣2006 ዓ.ም)

ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የተነሳ የሽማ ውጤት የሆኑ አልባሳት ከአዘቦት ልብስነት ወደ የክት ልብስነት ተሸጋግረዋል፡፡ በምትካቸው ዘመናዊ አልባሳት እየተዘወተሩ መጥተዋል፡፡ ወጣት ሴቶች የሚለብሱትን ልብስ (ገመኖ) ህጻናት ሲለብሱት መታየት ተለምዷል፡፡

የመጨረሻው በምክንያትነት የሚነሳው ጉዳይ የዋጋ ውድነት ነው፡፡ ይህ በተለይም በጌጣጌጦቹ ላይ ተጽዕኖ ያሳደረ ሲሆን በፊት በብር ብቻ ይሰሩ የነበሩ ጌጣጌጦች ከብር ውጭ በሆኑ ቁሶች ተተክተው እንዲሰሩ ሆኗል፡፡ በተጨማሪም እንደ ሽሾ ያሉ ጌጦች የሚሰሩበት የቁስ አይነት መብዛትና በቀላሉ አለመገኘት የበፊቱን የመሰሪያ ቁስ ለቀው በጨሌ እንዲቀየሩ እና ጌጦቹ በብዛት እየቀነሱ እንዲመጡ ምክንያት ሆኗል፡፡

ጥናቱ በተደረገባቸው ወረዳዎች ያሉ መረጃ አቀባዮች በአልባሳቱና ጌጣጌጦቹ ላይ እየተደረጉ ካሉት ለውጦች መካከል መገታት አለባቸው ያሏቸውን ለውጦች ከራሳቸው ጀምረው ለመግታት እንደሚጥሩ ተናግረዋል፡፡ መንግስትም በበኩሉ ትምህርት እንዲሰጣቸውና ባህላቸውን ለመጠበቅ የሚያስችላቸውን መንገድ ለመቀየስ እገዛ ሊያደርግላቸው እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡ ለአብነትም አቶ አሰፋ ወ/ማሪያም ያሉትን እንደሚከተለው አስፍሬዋለሁ፡፡

> እኔ በበኩሌ ዘመናዊውን አለባበስ የምቃወም ነኝ፡፡ በበአላት ጊዜ ወጣቶች ባህላዊ ልብስ ለብሰው እንዲወጡ እመክራለሁ፡፡ ለውጥ የሚጀመረው ከራስ ነው፤ እኔም የራሴን ቤተሰብ ለመለወጥ እጥራለሁ፡፡ ለብዙ ጊዜያት መንግስት ይህንን ችግር ችላ ብሎት ቆይቷል፡፡ አሁን እንኳን ትንሽም ቢሆን እየተሰራ ነው፡፡ ነገር ግን ለህዝቡ በሰፊው ትምህርት ቢሰጥ ጥሩ ለውጥ ይመጣል፡፡ ለለውጡ መምጣት መንግስት ሊረዳን ይገባል፡፡ (ቃለመጠይቅ፣ጥር 14፣2006 ዓ.ም)

በመንግስት ደረጃም ማህበረሰቡ ልብሶቹን እንዲለብስ ለማነሳሳትና ግንዛቤ ለማስጨበጥ እየተሰራ ነው፡፡ ለዚህም ይረዳ ዘንድ የካፋ ባህል ቱሪዝምና ኮሚዩኒኬሽን ቢሮ በቦንጋ ከተማ የባህላዊ ልብስ ማህበር ለማቋቋም ወጣቶቹን እያደራጀ ያገኛል፡፡ በተጨማሪም የባህል ምክር ቤት በማቋቋም ያለውን የግንዛቤ ችግር ለመቅረፍ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያና የይሁንታ ሀሳቦች

በዚህ ምዕራፍ እስካሁን በቀረቡት ምዕራፎች የተነሱት ሀሳቦች ተጠቃለው የሚቀርቡበት እንዲሁም ደግሞ ከጥናቱ ግኝት በመነሳት ሀገረሰባዊ አልባሳቱና ጌጣጌጦቹ የተሻለ ደገኛ ላይ እንዲገኙ ለማድረግ ይጠቅማሉ ተብለው የታሰቡ የመፍትሔ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

### 5.1. ማጠቃለያ

በጥናቱ የመጀመሪያ ምዕራፍ እንደተገለጸው የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ዋና አላማ የካፊቾ ብሄረሰብ የሴቶችና የወንዶች የአለባበስና አጊያጊያጥ ባህሎችን በመመርመር ልብሶቹና ጌጣጌጦቹ እንዲሁም የፀጉር አሰራር አይነቶቹ በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸውን ማህበራዊ ፋይዳ ማሳየት እንዲሁም ሰንዶ ማኖርን አላማው አድርጎ ነው፡፡ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ ቁሶቹን፣ የቁሶችን መሰሪያ፣ የቁሶቹን ተግባር፣ በቁሶቹና በማህበረሰቡ መካከል ያለውን ግንኙነት እና የተደረገባቸውን ለውጥ ለማሳት የሚያስችሉ ዝርዝር አላማዎች ተዘጋጅተው ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡

አላማዎቹን ከግብ ለማድረስም በምልከታ፣ በቃለመጠይቅና በተተኳሪ ቡድን ውይይት መረጃዎች ከመስክ ተሰብስበዋል፡፡ መረጃዎቹም በገለጻና በትርጓሜ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ በትንተናው የተገኙት ውጤቶችም እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

በጥናቱ 12 አልባሳት (6 የሴቶችና 6 የወንዶች)፣ 19 ጌጣጌጦች (10 የሴቶች፣ 8 የወንዶች እና 1 የህጻናት) እና 4 የፀጉር አሰራሮች (2 የሴቶች፣ 1 የወንዶችና 1 የጋራ) ትንተና ተደርጎባቸዋል፡፡ አልባሳት በሸማኔ የሚዘጋጁ፣ የፋብሪካ ውጤቶች ከሆኑት ጨርቆች የሚሰፉ እና በራሱ በማህበረሰቡ የሚዘጋጁ ናቸው፡፡ እነዚህም አልባሳት በሚይዙት ቅርጽና በሚዘጋጁበት ቁስ ተለያዩ ናቸው፡፡ አልባሳቱ ከጾታና ከእድሜ አንፃርም የወንድ፣ የሴት፣ የወጣቶች፣ የአባቶች፣ ያገቡ እና ያላገቡ የሚለብሷቸው ተብለው ተለይተዋል፡፡ ከሚለበሱበት አጋጣሚ አንፃርም የስራ፣ የሰርግ፣ የበዓላት ተብለው የተቀመጡ ናቸው፡፡

ማጌጫዎቹም እንደዚሁ ከሚውሉበት ሰውነት ክፍል አንፃር የራስ፣ የአንገት፣ የጆሮ፣ የእጅ፣ የጣት፣ የወገብ እና የእግር ተብለው ተከፍለዋል፡፡ እነዚህም ጌጣጌጦች ከጨሌ፣ ከብር፣ ከነሀስ፣ ከዝሆን ጥርስ፣ ከብረታ ብረት፣ ከቆዳ፣ ከዛጎል ወዘተ. ይሰራሉ፡፡

ቁሶች በማህበረሰቡ ዘንድ የተለያዩ ተግባራት ያሏቸው ናቸው፡፡ ተግባራቸውም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃዎችን ማሳየት፣ እምነቶችን መግለጽ፣ ተግባቦትን መፍጠር፣ ወዘተ. ናቸው፡፡ ለምሳሌ ተነፋነፍ እና ሽናፌሎ ማህበራዊ ደረጃዎችን አመላካች ሲሆኑ ሽሾ እና አሉቦ ደግሞ ኢኮኖሚያዊ ደረጃን ገላጭ ናቸው፡፡ ጎፌር የለበሰ ሙሽራ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ቲሮ የለበሰች ሴት ከታየች የአላሞ ሚስት መሆኗ ይታወቃል፡፡ ኪቶ የለበሰች ያላገባች ገመኖ የለበሰች ደግሞ ያገባች መሆኗ ተለይቶ ይታወቃል፡፡ የፀጉር ስሬቱም እንደዚሁ ያገባች እና ያላገባች መሆኗን የሚያሳውቅ ነው፡፡ ጎፖ እና ቦሮ መቆረጥ ሀዘንተኝነትን ያመላክታል፡፡

እነዚህ ቁሶች ያሏቸው ተግባራት በርካታ ቢሆንም ከዘመናዊነት እሳቤ ጋር ተያይዞ ልብሶቹ በመሰሪያ ቁሳቸውና ቅርጻቸው፣ በመለበሻ አጋጣሚያቸውና በቁጥራቸው ለውጥ እየታየባቸው ነው፡፡ ከመሰሪያ ቁሳቸውና ቅርጻቸው፣ ከመደረጊያ አጋጣሚያቸውና ከቁጥራቸው አንፃር ከአልባሳቱ ይልቅ ጌጣጌጦቹ የበለጠ የመለወጥ ሁኔታ ታይቶባቸዋል፡፡ ከአልባሳት ደግሞ ገመኖና ኪቶ በመሰሪያ ቁሳቸው በእጅጉ ተለይተዋል፡፡

ስለአልባሳቱ፣ ጌጣጌጦቹ እና የፀጉር አሰራር አይነቶቹ የጠገጠሙ 98 ግጥሞች የተሰበሰቡ ሲሆን ከነዚህም መካከል 19ኙ ተተንትነዋል፡፡ እነዚህም ግጥሞች የአልባሳቱንና የማጌጫዎቹን ተግባራት የሚገለጹ ሁነው ተገኝተዋል፡፡

## 5.2. የይሁንታ ሀሳቦች

የካፊቾ ብሔረሰብ አልባሳትና ጌጣጌጦች በሌላ ሳይተኩ ባህላቸውን ጠብቀው እንዲቆዩ እና ለተተኪው ትውልድ እንዲተላለፉ ለማድረግ ይጠቅማሉ የተባሉ ሀሳቦች በሚከተለው መልኩ ቀርበዋል፡፡

- ❖ በተገኘው መረጃ መሰረት በአሁኑ ወቅት ወጣቶቹ ስለ ሀገረሰባዊ አልባሳቱም ሆነ ጌጣጌጦቹ ጥልቅ ግንዛቤ የላቸውም፡፡ ስለዚህም ወጣቶቹ ስለ ባህላቸው እንዲያውቁ የተለየ ስልጠና እና ትምህርት ቢሰጣቸው፡፡ ታዳጊዎቹም ባህላቸውን አውቀው እንዲያድጉ እና ለወደፊትም ቁሶቹን እንዲጠብቋቸው በተለይም በትምህርት ቤቶች አካባቢ ትምህርት መሰጠት ቢችል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

- የአካባቢውን ባህል ለማሳደግ በሚደረገው ጥረት ማህበረሰቡ ተሳታፊ እንዲሆን የዞኑ ማስታወቂያ ጽህፈት ቤት በሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ጋዜጣ፣ መጽሔቶችንና በራሪ ጽሁፎችን በመጠቀም ማህበረሰቡ ሀገሰረባዊ አልባሳቱንና ጌጣጌጦችን ለመጠበቅ እንዲነሳ ማነቃቃት ቢችል መልካም ነው፡፡
- የሸማ አልባሳትን የሚያዘጋጁ ባለሙያዎች ተበታትነው የሚገኙና በቁጥርም አናሳ እንደሆኑ ከተገኘው መረጃ ማወቅ ተችሏል፡፡ በመሆኑም እነዚህን ባለሙያዎች በማህበር በማደራጀትና ልብሶቹን ለመስራት የሚያስችላቸውን አቅም በመፍጠር እየሰሩ ለገበያ እንዲያቀርቡ ቢደረግ ማህበረሰቡ ቁሶቹን እንዲጠቀም እድሉን ይከፍታል፡፡
- ስለ አልባሳቱ እና ጌጣጌጦቹ የሚነገሩ ጥሩ ያልሆኑ አመለካከቶችን ለመቀየር እና የልብሶቹን ተጠቃሚዎች ለማብዛት በተለያዩ የእምነት ቦታዎች አካባቢ ትምህርት ቢሰጥ እላለሁ፡፡
- በመጨረሻም በባህልና ቱሪዝም ቢሮ አማካኝነት እየተመዘገቡ የሚገኙት ሀገረሰባዊ አልባሳትና ጌጣጌጦች ተሰብስበው በቦንጋ ከተማ እየተገነባ ባለው ብሔራዊ የቡና ሙዚየም ውስጥ የራሳቸው ቦታ ተሰጥቷቸው ቢቀመጡ፣ ከዚያም ለህዝብ እይታ የሚቀርቡበት መንገድ ቢፈለግ ጠቃሚ ነው የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች


ሂኖክ ስዩም፡፡ <u>የኢትዮጵያ ተፈጥሮና ፓርኮች ማውጫ</u>፡፡ ሀገሬ ሚዲያ ኮሙኒኬሽን፣ ዘመን የለውም፡፡

በቀለ ወ/ማሪያም፡፡ <u>የካፋ ህዝቦች እና መንግስታት አጭር ታሪክ</u>፡፡ ሜጋ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣ 1996 ዓ.ም፡፡

በካፋ ዞን ባህል ቱሪዝምና የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች መምሪያ፡፡ ‹‹ቡኖ››፣ ቅጽ1 ቁጥር 10፣ አቤንኤዘር ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣ መጋቢት 2003 ዓ.ም፡፡

ሰይድ ይማም፡፡ "በከሚሴ ከተማ ዙሪያ በሚገኙ ገጠር አካባቢዎች የወጣት ወንዶችና ሴቶች አለባበስና አጊያጊያጥ"፤ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ- ጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2002 ዓ.ም፡፡

አመልማል ተሻለ፡፡ "በባንጃ ወረዳና አካባቢዋ የአዊ ብሄረሰብ አለባበስና ጌጣጌጦች ገላጭ-ጥናት"፤ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2004 ዓ.ም፡፡

አያል አድማሱ፡፡ "የጎጃም አካባቢ የአልባሳት ስያሜ"፤ የባችለር ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1992 ዓ.ም፡፡

አፀደ ያረጋል፡፡ "የኮንሶ ሃገረሰባዊ አልባሳት እና ጌጣጌጦች፡- ገላጭ-ተንታኝ ጥናት"፤ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ የኢትዮጵያ ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2003 ዓ.ም፡፡

ውብሸት አሰፋ፡፡ "የወይዛዝርት አልባሳትና ጌጣጌጥ ስሞች በአማራው ባህል"፤ የባችለር

ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1978 ዓ.ም፡፡

የኔአለም አረዶ፡፡ "የአርሲ ሴቶች ጌጣጌጥ ጥናት በኮኮሳና ገደብ ሀሰሳ ወረዳዎች"፤
የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ክፍለ ትምህርት
፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2000 ዓ.ም፡፡

ያሬድ ተፈራ፡፡ "በሰቆጣና በአበርገሌ ገጠራማ ወረዳዎች የሴቶችና የወንዶች የአለባበስና
አጊያጊያጥ ማህበራዊ እሴቶች"፤ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ የኢትዮጵያ
ቋንቋዎችና ስነ- ጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2002 ዓ.ም፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ የስነ ቃል መምሪያ፡፡ አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፣ 1991፡፡

Ames, L. Kenneth. "Meaning in Artifacts: Hall Furnishings in Victoria America."
Journal of Interdisciplinary History; vol lx; No. 1,pp. 19-46; 1978.

Bieber, Otto. Secret Kafa In The Home of The Emperor-Gods. Vienna Austria,
1948.

Brandshaw, Angela. World Costumes. New York: the Macmillan Company. 1965.

Bronner, Simon J. Concepts in the Study of Material Aspects of American Folk
Culture. Online available at: http://WWW.loc.gov/folklife/source/index.php.
ዘመን የለውም

Clark, Gahame. Symbols of Excellence. London: Cambridge Univeristy Press.
1986.

Cleary, Ann MC. "Method and Theory of Material Culture Studies." Course note

online at- URL: http://WWW.bliklist. Comart aide/theories/ (n.d). 2004.

Dorson, Richard M. "Introduction: Concepts of Folklore and Folk Life Studies" In Richard Dorson. (ed). Folklore and Folk Life; An Introduction. Chicago and London: the University of Chicago Press. 1972.

Evans, Joan. A History of Jewellery: (1100-1870). Boston: Boston Book and Publisher. 1970.

Glassie, Henry. Material Culture. Blomington and Indianapolis. Indiana University Press. 1999.

Goldstein, Kenneth S. A Guide for Field Work in Folklore. Hatboro Pennsylvania: the American Folklor in Society, 1964.

Gracia, Maria Inglessis. "Communicating through Clothing: the Meaning of Clothing among Hispanic Women of Different Levels of Acculturation." College of communication; Florida University, 2008.

Huntingford, G.W.B. History of The Galla (Oromo) of Ethiopia with Ethnology and History of South West Ethiopia. Oakland, California: Africa Sun Publishing, 1993.

Lange, W. Hstory of Southern Gonga. Wisbaden: Frant steiner verlag Gmbh, 1982.

Lurie, Alison. The Language of Clothes. NewYork: Random House Inc, 1981.

Mayo, Edith. American Material Culture: the Shop of Things Around Us. Bowling

Green State: Bowling Green State University Popular Press. 1984.

Prown, Jules David. “Mind in Matter: An Introduction to Material Culture Theory and Method.” Online Availble at: http://WWW.jstor.Org /stable/11807661. 1982.

Schlereth, J. Thomas. “Material Culture Research and Historical Explanation.” on line. Available at: http://www. Jstor. Org/stable/ 33775481. 1985.

------------------------------ “Understanding the Nine Models of Material Culture Interpretation.” Online. Available at: http://www.btneporg. 1980.

Wilson, William A. “Documenting Folklore.” In Folk Groups and Folklore Genres: An Introduction. In Elliot Oring, (ed). Logan：Utah State University Press.1986.

Woodward, Ian. Understanding Material Culture. Los Angles: SAGE Publication, 2007.

Yoder, Don. “Folk Costume’’. Folklor and Falklife; An Introduction. Richard M. Dorson (ed.). University of Chicago, 1972.

# አባሪዎች

## አባሪ 1. ለመረጃ አቀባዮች የቀረቡ ጥያቄዎች

### ሀ. ግላዊ መረጃዎችን ለማግኘት የቀረቡ ጥያቄዎች

1. ሙሉ ስም?
2. እድሜ?
3. የትውልድ ስፍራ (የመኖሪያ ስፍራ)?
4. ሀይማኖት?
5. መተዳደሪያ?
6. የቤተሰብ ሁኔታ?

### ለ. አካባቢያዊና ባህላዊ መረጃዎችን ለማግኘት የቀረቡ ጥያቄዎች

1. ያላገቡ ወንዶችና ሴቶች ምን ይለብሳሉ? በምን ያጌጣሉ? በምን መልኩ? ለምንድን ነው በዚህ መልኩ ብቻ የሚያጌጡት/ የሚለብሱት?
2. ያገቡ ወንዶችና ሴቶች ምን ያለብሳሉ? በምን ያጌጣሉ? በምን መልኩ? ለምንድን ነው በዚህ መልኩ ብቻ የሚያጌጡት/ የሚለብሱት?
3. በእድሜ የገፉ እናትና አባቶች ምን ይለብሳሉ? በምን ያጌጣሉ? በምን መልኩ? ለምንድን ነው በዚህ መልኩ ብቻ የሚያጌጡት/ የሚለብሱት?
4. ህጻናት ምን ይለብሳሉ? በምን ያጌጣሉ?
5. በበዓላት ወቅት የሚለበሱ ልብሶች አሉ? ካሉ ምን አይነት ናቸው?
6. በሀዘን ወቅት ምን ይለበሳል?
7. በሰርግ ወቅት ምን ይለበሳል?
8. የአዘቦት ልብሶች ምን ምን ናቸው? በምን መልኩ ይለበሳሉ?
9. አልባሳቱና ማጌጫዎቹ ምን አየተባሉ ይጠራሉ? የተሰጣቸው ስያሜ የተለየ ምክንያት ይኖረዋል?
10. አልባሳቱና ማጌጫዎቹ ከምን ይሰራሉ? ተምሳሌታዊነታቸውስ ምንድን ነው?
11. በነጠላ፣ በቀሚስ፣ በመቀነት፣ ወዘተ. ላይ የሚደረጉ የቀለም አይነቶች ምን ምን ናቸው? ቀለም ባይኖረውስ? ቀለሙ ከልብስ ልብስ ይለያያል? ለምን?

12. አልባሳቱና ማጌጫዎቹ በምን አጋጣሚና ወቅት የሚለበሱና የሚደረጉ ናቸው? እንዴት ይደረጋሉ?
13. ጌጣጌጦች በየትኛው የሰውነት ክፍል ይደረጋሉ? ለምን?
14. የወንዶች ፀጉር በምን መልኩ ይያዛል፣ ይቆረጣል? ለምን?
15. የሴቶች ፀጉር በምን መልኩ ይቆረጣል? ህጻን ከሆነች፣ ልጃገረድ ከሆነች፣ በእድሜ የገፋች ከሆነች? ምን አይነት የፀጉር አሰራር ትሰራለች? በዚህ መልኩ መሰራታቸው የሚያመለክተው ነገር አለ ወይ?
16. ባህላዊ አልባሳቱንና ጌጣጌጦቹን በማየት የሰዎችን እድሜ፣ ሀይማኖት፣ የኑሮ ደረጃ መገመት የሚቻልበት ሁኔታ አለ?
17. ስለ አልባሳትና ማጌጫዎች የተገጠሙ ግጥሞች ካሉ ቢነግሩኝ?
18. በዘመናዊ መልኩ እየተሰሩ ስለሚገኙት አልባሳት ምን አስተያየት አለዎት?
19. በርስዎ እድሜ  አልባሳቱና ማጌጫዎቹ የተለወጡበት ሁኔታ አለ? ምክንያቱስ ምንድ ነው ብለው ያስባሉ? ለወደፊት ከዚህ የበለጠ እንዳይለወጡ ማድረግ ይቻላል ብለው ያምናሉ?
20. የካፊቾ ብሔረሰብ ባህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጦች ባህላዊነታቸውን ጠብቀው እንዲቆዩ ምን መደረግ አለበት ይላሉ?

## ሐ. ለተተኳሪ ቡድን ውይይት የቀረቡ ጥያቄዎች

1. የካፊቾ ብሔረሰብ የጋብቻ ሁኔታ ምን ይመስላል?
2. የካፊቾ ብሔረሰብ የለቅሶ ሁኔታ ምን ይመስላል?
3. የካፊቾ ብሔረሰብ የስራ ባህል ምን ይመስላል?
4. በአካባቢው የተለመዱት የአለባበስና የአጊያጊያጥ አይነቶች ምን አይነት ናቸው? ምን ምን ይባላሉ? ስያሜያቸውስ ከምን የመነጨ ነው?
5. በሚደረጉበት አጋጣሚ፣ በፆታ፣ በቀለም፣ በሚሰሩበት ቁስና በአሰራራቸው፣ ወዘተ. ይለያያሉ? በምንስ ይለያያሉ?
6. አልባሳቱና ማጌጫዎቹ የተለወጡበት ሁኔታ አለ? ካለ ምክንያቶቹ ምንድን ናቸው ብላችሁ ታስባላችሁ?
7. ባህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጦች ባህላዊነታቸውን ጠብቀው እንዲቆዩ ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ?
8. ከአልባሳቱና ጌጣጌጦቹ ጋር በተያያዘ የተነገሩ ግጥሞች ካሉ ብትነግሩኝ?

# አባሪ 2. የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር

| ተ.ቁ | ስም | እድሜ | ጾታ | ሀይማኖት | ስራ | ቃለ መጠይቅ የተደረገበት ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | መሰረት ተስፋየ | 26 | ወ | ኦርቶዶክስ | የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሰራተኛ | በካፋ ሙዝየም ግቢ ውስጥ |
| 2 | ሰሎሞን ተክሌ | 58 | ወ | ኦርቶዶክስ | የጥበቃ ሰራተኛ | በመኖሪያ ቤታቸው |
| 3 | ሳደም አደም | 19 | ወ | ሙስሊም | ነጋዴ | በስራ ቦታቸው |
| 4 | ሶስና ሀይሌ | 17 | ሴ | ኦርቶዶክስ | ተማሪ | በካፋ ሙዝየም ግቢ ውስጥ |
| 5 | ሶፍያ ሽኩር | 39 | ሴ | ሙስሊም | ነጋዴ | በመኖሪያ ቤታቸው |
| 6 | ሻውጀራሻ አሸብር ሐይሌ | 53 | ወ | ኦርቶዶክስ | የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሰራተኛ | በመኖሪያ ቤታቸው |
| 7 | ቆጪች ኢሚቶ | 71 | ሴ | ባህላዊ እምነት ተከታይ | አርሶ አደር | በስራ ቦታቸው |
| 8 | ቆጭቶ ኢሞ | 78 | ወ | ባህላዊ እምነት ተከታይ | አርሶ አደር | በስራ ቦታቸው |
| 9 | በላይነሽ ተክሌ | 55 | ሴ | ኦርቶዶክስ | የገቢዎች መምሪያ ሰራተኛ | በስራ ቦታቸው |
| 10 | በየነ በቀለ | 57 | ወ | ኦርቶዶክስ | ትራንስፖርትና መንገዶች ቢሮ ሰራተኛ | በስራ ቦታቸው |
| 11 | ታደሰ ጊያ | 31 | ወ | ኦርቶዶክስ | የሽመና ስራ ባለሙያ | በስራ ቦታቸው |
| 12 | ቹቹ ማገቶ | 24 | ሴ | ኦርቶዶክስ | ነጋዴ | በስራ ቦታቸው |
| 13 | አለሚቱ አያና | 50 | ሴ | ኦርቶዶክስ | ጠጅ በመጣል የምትተዳደር | በመኖሪያ ቤታቸው |
| 14 | አምሳለ ማሮ | 23 | ሴ | ኦርቶዶክስ | የካፋ ባህል ቡድን የሙዚቃ ባለሙያ | በስራ ቦታቸው |
| 15 | አሰፋ አለማየሁ ጋነች | 47 | ወ | ኦርቶዶክስ | ጠበቃ | በመኖሪያ ቤታቸው |
| 16 | አሰፋ ወ/ማርያም | 61 | ወ | ኦርቶዶክስ | ጡረተኛ | በካፋ ሙዚየም ግቢ ውስጥ |
| 17 | አስማረች | 16 | ሴ | ኦርቶዶክስ | ተማሪ | በመኖሪያ ቦታቸው |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ተሰማ | | | | | |
| 18 | አስራት ሐይሌ | 47 | ወ | ኦርቶዶክስ | የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሃላፊ | በስራ ቦታቸው |
| 19 | አረንጌ የራንጎ | 82 | ሴ | ባህላዊ እምነት ተከታይ | አርሶ አደር | በመኖሪያ ቤታቸው |
| 20 | አሸናፊ ገ/ማርያም | 26 | ወ | ኦርቶዶክስ | የካፋ ባህል ቡድን ሙዚቀኛ | በስራ ቦታቸው |
| 21 | አቦነሽ አትርሴ | 52 | ሴ | ኦርቶዶክስ | የቤት እመቤት | በመኖሪያ ቤታቸው |
| 22 | አዳነች አደቆ | 64 | ሴ | ኦርቶዶክስ | አርሶ አደር | በመኖሪያ ቦታቸው |
| 23 | አድማሱ መኩሪያ | 68 | ወ | ኦርቶዶክስ | አርሶ አደር | በስራ ቦታቸው |
| 24 | አገሬ በለጠ | 54 | ሴ | ኦርቶዶክስ | ነጋዴ | በስራ ቦታቸው |
| 25 | የሻረግ ተክሌ | 37 | ሴ | ኦርቶዶክስ | ነጋዴ | በመኖሪያ ቤታቸው |
| 26 | ደስታ ታከለ | 68 | ሴ | ፕሮቴስታንት | የቤት እመቤት | በመኖሪያ ቤታቸው |
| 27 | ጀማል አብዱ | 35 | ወ | ኦርቶዶክስ | መምህር | በመኖሪያ ቤታቸው |
| 28 | ግርማ ደምሴ | 77 | ወ | ኦርቶዶክስ | አርሶ አደር | በመኖሪያ ቦታቸው |
| 29 | ወርቁ አለሙ | 29 | ወ | ኦርቶዶክስ | የሴቶችና ህጻናት መምሪያ የወጣቶች ዘርፍ መምሪያ ሃላፊ | በስራ ቦታቸው |
| 30 | ወርቁ ወ/ማርያም | 50 | ወ | ኦርቶዶክስ | የባህል ቢሮ ሰራተኛ | በመኖሪያ ቤታቸው |
| 31 | ውዴ ሙሉጌታ | 47 | ሴ | ኦርቶዶክስ | አርሶ አደር | በመኖሪያ ቦታቸው |
| 32 | ፈቃዱ ጋዲሳ | 25 | ወ | ኦርቶዶክስ | የካፋ ባህል ቡድን የሙዚቃ ባለሙያ | በስራ ቦታቸው |

## አባሪ 3. ግጥሞች

1. Allubboo aalloone gettemmo konine
   Showoon ceenni beeto aroo baach toone
   አሉቦ የለም የሚል ሰው ማነው
   እሱ ብቻ አይደል ወይ ሀገሩን የሞላው
2. Aache allubboona birewee allubboonon bariibeeto amooneene
   Amoona aalloone bulli showoocheeniye
   የወርቅ አሉቦና የብርን አሉቦ የሚለይ ምንድን ነው
   ምንም ነገር የለም ሁሉም ከመሬት ነው
3. Taacho desh worefa neecho damb angesha
   Tahoon aabich ciinot amooch damersha
   የኔ ታች ቆላ ያንች እላይ ደጋ ነው
   ልብሱን በምን ልየው በየትስ ላግኘው
4. Aallet taane bushoo
   Allet tanne hadur
   Amoommi shifone qellon bishippeto
   Amoommi pha'one phaqibeeto baroo
   ጠፍቻለሁ ልጄ
   ጠፍቻለሁ ዘንድሮ
   እንዴት ያለ ስሬት ነው ጸጉሯን የተሰራችው
   ኸረ እንዴት እንዴት ነው ሚያበራው ግንባሯ

5. Ebine no bushee
   Ebe'i malli gaawee
   Eecha'a bi kittoon
   Ella noon ciichitan
   ይህች ነች የኛ ልጅ
   ይህቻት መልከ መልካሟ
   ኪቶዋን እንዲህ አ'ርጋ
   እንግዲህ ጨረሰችን
6. Bi kittoon qajja'a gammannoon geddetan
   Bushiishoon shiya'a woddeemi shaahitan
   ኪቶዋን አውልቃ ገመኖን ለብሳለች
   ልጆችንም ወልዳ ምትበዛ መስላለች
7. Ne buroon cuyiree eke waa kaay taanna
   Ne aafoon ciinna'a qitit taane wonna
   እስኪ ቡሮ ታጥቀሽ ነይ ተጫወች ከ'ኔ

ድሮ አይንሽን አይቼ ሞቻለሁኝ እኔ

8. Neexebe ta gaxooch gammannoon geddetine
Ne kenoo ta tunoon bulli ashooch bekkiibone
ገመኖ ለብሰሽ ነይ ከጎኔ ቁሚ
ያንቺ ባል መሆኔን ለሰው ሁሉ እናሳይ
9. No indeenon be'ot wanderoona gaawee
No showee oogiittinoon ebina ariibone
እናታችንን እዩ በዋንደሮ አምረው
ያገራችንን ታላቅነት በዚህ እንወቀው
10. Bo bushiishoon diirii kenooch immitone
Buroon wanderoona oogitinoon tahee
Xaappoon toommooch geddi
Xallee sha'ebeetinone
ልጆቻቸውን መርቀው ለባል ሰጥተዋል
ቡሮን በዋንደሮ ታላቅነት ለብሰው
ጣፖን ከላይ አርገው
ንጹህ ሆነው እየተራመዱ ነው
11. Kafechi bushoochan ebi aabich beete
Kemee daniyaani shoroo nowaan beete
ለካፋ ልጅ እንጂ ይኼ ከየት አለ
ተገዝቶ የማይገኝ ሾሮ ከኛ አለ
12. Phashee oggoon geddi gijjoon dabbitone
Phixxaasho no bushoo amo gaawetone
የቀርከሃ ኦጎ አድርጎ ከብቱን ተከትሏል
ጎበዙ የኛ ልጅ እንዴት መልካም ሆኗል
13. Gishiishi gijjaafon biqettooch geda'a
Gaafiyoon bitoommooch gaawucha xappa'a
Gooshoon bi kishooch geddaa bekkabeeti
Shaawujje raashechi boochi baach tuneti
ትንንሹን ጨሌ ከአንገቷ አድርጋ
ትልልቁን በላይ በውበት ደርባ
ከእጇ ጎሾን አድርጋ ምትታይ
የሻውጄራሻ የሳቸው ብቻ የሆነች ነች
14. Amoommi gaannoone wo'ee nihooch beeto
Areen baach be'ona bulli arichebeeto
ምን ያህል ሀብታም ነው የሙሽሪት አባት
እሷን ብቻ በማየት ሁሉ የሚታወቅ

15. Kishooch gooshee gumboon
Kushoon shoophooch geddi
Sha'ebeeti boshoo
Malletechi asho
በጁ ጎሼ ጉምቦን
ኩሾን ብብቱ አድርጎ
ሚራመደው ልጅ
መልከ መልካም ሰው

16. Geendoon uuyoon shaaggi shoroono edde'i bushoo hammitone
Gennoo mullo deqqi mixooch kechitone
ቀፎና ገመዱን ተሸክሞ ሾሮንም ታጥቆ(ልጁ) ሄዷል
የሴቱን ልብ ወስዶ ከዛፉ ላይ ወጥቷል

17. Gattee goyochani shoroon ta geddeto
Gafooch hamoch gaata kon baroo mucceto
በሬ (እርሻ) ለማረስ ነውንጂ ሾሮን ያደረግኩት
ከመንደር ለመሄድ ማነው ሌላ ያጣው

18. Kokkelloon xoobaabe duuboono duubbaabe
Kafoon yookkeet taane
Aaabooch amihoocho oggoon gedeettaane
Amoona tuneba taan shattiyeemmo aalloone
ኮኬሎ እየመታሁ ዘፈን እየዘፈንኩ
ወፍ አባርሬያለሁ
ለፀሀይ ለዝናብ ኦጎን አድርጌያለሁ
ምንም ይሁን አሁን የሚያስፈራኝ የለም

19. Tifoon bo qettoocha axxaamiton kishooch
Tuneeti xaa'oocha hammi waabeetinooch
Tii diggoo getonan doonoochi mecheenoch
ቲፎን ካንገታቸው አጣሚቶን ከእጅ
የሆነ ቦታ ሄደው እየመጡ ላሉት
ተነስተን ሰላም እንበል ለጌቶች ሚስት

20. Amoommi gaaweto no showee qocoone
Ashicho toonoone wnderoowo xaappoo nocho baachiye
ምን ያክል መልካም ነው የኛ ሀገር ባህል
የሰው እኮ አይደለም ዋንደሮውም ጣፖውም የኛ ብቻ እኮ ነው

21. Shaashee guude gijjoon geddetane bushee
Shimo eboominan indeen yeelliyaane
ባለ ሰላሳ ዙር ጨሌን አድርጋለች ልጅቷ

*መውለድ እንዲህ ነው እናት ማታሳፍረዋን*

22. Ebi bulli gooshoon bi kishooch geddeti
Emiroo bi aafooch ceenni bekkabeeti
Ebine no indee bi shimon quyeti
*ይህን ሁሉ ጎሾ ከእጇ ያደረገች*
*ደስታ በአይኖቿ ሞልቶ ምትታየው*
*ይህቻት እናታችን ልጆቿን የጠበቀች*
23. Shoroon sharaateto shuunoon shachaweeto
Shiichi aricheehe mooyon ariibeeto
*ሾሮን የናፈቀ ስራን የተጠማ*
*ቀድሞ ይታወቃል ነገርን የሚያውቅ*
24. Shanaafillo shoroo nihoo bushooch wojjii
Shametoona shaaga shuuno showoon shunni
*ሸናፊሎ ሾሮን አባት ለልጅ ያውርስ*
*በሸሜቶ ያግባ ስራ ሀገርን ወድዶ*
25. Daaheree gooqqooche shuuneeti shoroona
Damba dubboon geddi asho sha'emona
Daniyaani mooyo shuniyano aalla
*ከአንበሳ ቆዳ የተሰራን ሾሮ*
*ከላይ ዱቦን አርጎ ሰው ሲንቀሳቀስ*
*የማይገኝ ነገር የማይሰራ የለም*
26. Gooshoon kemeemmoocho ekee daambe taana
Guttichoon kemeemmo waare daambe taana
*ጎሾን የምትገዛው እስቲ ና ውሰደኝ*
*ጉትቻን ምትገዛው ናና እኔን ውሰደኝ*
27. Shammaanoo nooch beeba qoreddoon shuunebe
Showoon tahiibeeto noocho aroo tone
*ሸማኔ ይኑር ለኛ ልብስ እየሰራልን*
*ሀገር የሚያለብሰው እርሱ አይደለም ወይ የኛ*
28. Sheqqo gaawucha'a qoccoon quccaabeeti
Dubbiyoona aricheti bi kishoo gaaweti
*ሽቆን አሳምራ ቆጮን የምትፍቀው*
*ባገር የታወቀች እጇም ያማረ ነው*
29. Areddoono xumo phaqqibeeti shashoo
Aaache axxaamittoon kemebe ta bushoo
*ቀንም ሆነ ማታ ሚያብረቀርቀውን*
*የኔ ልጅ ግዛ የወርቅ አጣሚቶን*

30. Eeyon kuxooch hammi bi shoroono edde'i
Ella wottiyaanoone anaamo kechii
ማር ለመቁረጥ ሄዶ ሾሮውን ታጥቆ
እንግዲህ አይመለስም ወንድ ከቤት ወጥቶ
31. Nuucheena'o wobot xibeenaa'o ciinon
No bushoo deebite bulla shashee wo'een
ጓደኞች ሆይ ኑ ዘመዶችም እዩ
ልጃችን አምጥቷል ጌጥ በጌጥ የሆነች ሙሽራን
32. Cooxooch xumooch getti shaton bekkiyano
Cuboona kushoonon magee mucciyaano
Ciixeti anaamo ebine no bushoo
አውሬ ምሽት ብሎ ፍርሃት ማያሳየው
ጨቤና ኩሾውን ከቤት የማያጣው
አዋቂ ወንዳወንድ የኛ ልጅ ይሄ ነው
33. Gooqqoono qucote qoreddoon shifote
Gaawuchire bullin shoween geeciibote
ቆዳንም ፋቁ ልብስንም ስፉ
ሁሉን አሳምሩ ሀገሩንም አኩሩ
34. Shoroon shixxibeeto anaamo konine
Showoon maanjibeeto aroon tahetone
ሾሮን የሚጠላ እስኪ ወንድ ማነው
አገር ሚቀልበው ያን የለበሰ ነው
35. Shanafillon shunni shoroon shixxaayoote
Gubbicho aallegaata aaficho aalloone
ሸናፊሎ ወዳችሁ ሾሮን አትጥሉት
ኋለኛው ከሌለ የለምና የፊቱ
36. Daaddoona xaappoonon biindich gettito
Daneba bi qaawoon biicho tunebeeton
ዳዶና ጣፖውን ለእናቱ ያለ
ፍለጋውን ያግኝ ለእርሱ የሚሆነውን
37. Andiree qoreddoon taheree bekkebe
Ashi daggoch gibe ne qelloon bekiibe
አዲሱን ልብስሽን ልበሽና ታዪ
ከሰው መሀል ግቢ ራስሽን አሳዪ
38. Shiijjebe neechoommo ta bushoocho humo
Shoroona phaqqemmo shananfilloonomo
ይወለድ የኔ ልጅ እንዳንተ ያለ ሽህ ሰው

*በሾሮው የሚደምቅ በሸናፌሎው*

39. Gijjaafoo tunebaan taach ne immeemmo
    Giisheebe oogebe amoon taan giddeemmo
    *ጊጃፎ ይሁን እንጅ ለኔ የምትሰጠኝ*
    *ትንሹ ይሁን ትልቁ እኔ ምን ጨነቀኝ*
40. Ikke mooyo beete kechi bekkebeeto
    Indindeeno qettoch shashoo phaqqibeeto
    *አንድ ነገር አለ ወጥቶ የሚታይ*
    *ከአያታችን አንገት ሚያብረቀርቅ ጌጥ*
41. Shanaafillon tahee gochemtaa gettimmo mullaallo konine
    Shoroono edde'i gaarooch hammibeeto amoommi anaamone
    *ሸናፌሎ ለብሶ አርሳለሁኝ የሚል ልብ አልባ ሰው ማነው*
    *ሾሮንም ታጥቆ ከሰርግ የሚሄደው ምን ያለ ወንድ ነው*
42. Maraakommo ebi no Kafechi bushoo
    Maahoon wuxitone shoophooch beete kusho
    *መልአክ የመሰለው ይህ የካፋ ልጅ*
    *ነብር የገደለ ነው ኩሾ ከብብቱ አለ*
43. Indee gaxooch kotaa mooyo doyabeeti
    Iiwee xalle bushee shashoo baach tuneti
    Ikkekaal bi keyigaa bullin keqqiyaabeeti
    *ከእናቷ ጎን ሁና ሙያ ምትማረው*
    *ጤናማ ንፁህ ልጅ ጌጥ ብቻ የሆነችው*
    *አንድ ጊዜ ብትወጣ ሁሉን ምታስደነግጠው*
44. Buroon immi beeto biindi geenemmona
    Bulli diiroon daami geenittinooch beeba
    *ቦሮን የሚሰጣት እናቱ ስታረጅ*
    *ምርቃቱን ሁሉ ወስዶ ይኑር እስከሚያረጅ*
45. Anaamo bi kishoon qoofoona kuphii'i
    Awurebeet gino eke amoon mucce'i
    *ወንድ የሆነ እጁን በቆፎ አጠንክሮ*
    *ሚወረውረው ጦር እስኪ ምን ይስታል*
46. Dubboo tahee keyot showee asheena'ote
    Dobbiyoocho getii waa baaroon goyote
    *የሀገር ሰዎች ሆይ ዱቦ ለብሳችሁ ውጡ*
    *ለሀገር ነግራችሁ ኑ በቆሎ ዝሩ*
47. Amoommo gaaccite ebi shanaafillo
    Ashi daggoch keyoch noon gaawuchibeeto

ምን ያህል ይጠቅማል ይሄ ሸናፊሎ
ሰው መሀል ለመውጣት እኛን ሚያሳምረው

48. Ne achooch shoroon
Ne qelloocho oggoon
Gedi keye bushoo
Geendoon yeshi uyoo
Ebin ciinni asho bulli worganeeba
Eke ne anaamittino shuunoona aricheba
ለሰውነትህ ሾሮን
ለራስህም ኦጎን
አርገህ ውጣ አንተ ልጅ
ከቀፎ ጋር ኡዮን ይዘህ
ይህን አይቶ ሰው ሁሉ ይገረም
እስቲ ወንድነትህ በስራ ይታወቅ

49. Tibe ta manoocho ne shoroon eddere
Teephoon gaashoon goyi showoon geeciibone
ተነስ የኔ ወንድም ሾሮህን ታጥቀህ
ስንዴ ጤፍን ዘርተን ሀገሩን እናኩራ

50. Asho bulli deejjooch kechi hammitone
Aroo shanaafilloon edde kechitone
Aree gammannoona gaawa sha'etane
ሰው ሁሉ ለመስዋዕት ወጥቶ ሄዷል
እርሱ ሸናፊሎን ለብሶ ወጥቷል
እርሷ በገመኖ አምራ ተራምዳለች

51. Gaaroon batt ciinneton showoo ariyaano
Gaanno birewoona aachoona tahee'i bekketo
ሰርግ ገና አየን ባገር ያልታወቀ
ሀብት በብርና በወርቅ ተለብሶ የታየበት

52. Aree malli gaawee tahetane kittoon
Aroon kichibu eke imbote gammanoon
እርሷ መልከ መልካም ለብሳለች ኪቶን
እርሱን ታውልቅ እስኪ ስጧት ገመኖን

53. Qocoone no tahoo oogoone no showoo
Qoolloone no quyo gijjaafo no shashoo
ባህል ነው የኛ ልብስ ትልቅ ነው ሀገራችን
አድባር ጠባቂያችን ጊጃፎ ጌጣችን

54. Qoce tahon gedda baarooch kechetane

Qocechi no manee amoo gaawetane
የባህል ልብስ አርጋ (ለብሳ) ለበዓል ወጥታለች
ቆጨቺ የኛ እህት ምን ያህል አምራለች

55. Deechechine ebi woyee Addiyeexine
Dangich gesho yecha gooshoon geddetane
የዴቻ ነች ይህቺ ወይንስ የአዲያ
ደንጊች ጌሾን ይዛ ጎሾን አድርጋለች

56. Qelli shifo gaata no shaahoo konine
Qocoon bekkiibeeto gengoo diphoo beete
ፀጉር አሰራር እንደሁ እኛን መሳይ ማነው
ባህልን የሚያሳየው ጌንጎም ዲጶም አለ

57. Maachee no showoocha phixxee gettiyaabeeti
Maaccaa beeti qoccoon sheqqono taheti
ሴት በኛ ሀገር ጎበዝ ምትባለው
ቆጮን የምትፍቅ ሸቆንም ለብሳ

58. Taandi taan dojjitan shaashe gedi mooyoon
Tahoon gedo gaata qello asho shippemmon
እናቴ እኔን አስተምራኛለች ጌጥ የማድረግን ነገር
ልብስ መልበስም ቢሆን ፀጉር ሰው ሚሰራውን

59. Bunoon qullooch geddi dangichi gesh daggooch
Bo tiinjaanoon yechi dangichi gesh daggooch
Bo keneenon ciinooch hammitone goyooch
ቡናን በቁሏቸው አርገው ደንጊቺ ጌሾ ውስጥ
ስኒአቸውን ይዘው ደንጊቺ ጌሾ ውስጥ
ባላቸውን ሊያዩ ሄደዋል ከእርሻው

60. Ginoon bi kishoocha kushoon bi shoophoocha
Geddi bekkemmona aafoo shattiimmoocha
Gooqqee ukon imbot geda bi qelloocha
ጦርን በእጁ ይዞ ኩሾን ከብብቱ
አርጎ ሲታይ አይኑ ለሚያስፈራው
የቆዳ ኡኮን ስጡት ያድርግ ከጭንቅላቱ

61. Andire gooroocha bulli maache duubete
Allubboon qajji'i hulle baat sha'ete
በአሁኑ ጊዜ ሁሉ ሴት ተበላሽቷል
አሉቦውን ትቶ ባዶ እግር ተራምዷል

62. Ta xibeena'ote qocoon qajjaayote
Tahoon shoroon gedi beebot kuphebote

ዘመዶቼ ባህልን አትተው
ልብስን ሾሮን አድርጋችሁ ኑሩ ጠንክሩ
63. Kittoon daaddoon geddi maacho bekkemmona
Kafecho no tunoon ceenniye geecoona
ኪቶን ዳዶን አርጎ ሴቱ ሲታይ
ካፋ መሆናችንን ይሞላዋል በኩራት
64. Awuree qoreddoon bimecheech kemeto
Arooche beshe'i kishee axxaamittoon allubboon immito
Anaamo gaaweto bi kexon shunnito
አውሬ ቆሬዶን ለሚስቱ የገዛ
ከዚህም አልፎ አጣሚቶንና አሉቦን የሰጠ
ወንድ ጥሩ ነው ቤቱን የወደደ
65. Showoo shimaayoona newaan beqqibeete
Shashoo ne qoreddoo ashi mullo deqqite
መሬትና ሰማይ ወዳንቺ እየተመለከተ ነው
ጌጥሽ ልብስሽ የሰውን ልብ ወስዷል
66. Gaafiyoo noochone allubboo noochone
Gijjaafoo noocho aakka gaawiyaachone
ጋፊዮ የኛ ነው አሉቦም የኛ ነው
ጊጃፎም የኛ ለምን አንዋብም
67. Madee kaamo goora maayo maanjjeemmona
Maacho qocee tahoon geddi bekemmona
Meenon kuxxi mamooch amoommo emirikkihe
በፋሲካ ወቅት ምግብ ሲበላ
ሴቱ የባህል ልብስ ለብሶ ሲታይ
ስጋ ቆርጦ ለመብላት እንዴት ያስደስታል
68. Eke amoo halleehe huphichoon baach giddiyoo
Eddo qayigaata sheqqoon tifi gedo
Ella aata shaaweeshe qucceebeeti qoccoo
እስቲ ምን ያደርጋል ሁጲችን ብቻ ማዘጋጀት
መታጠቅ ከቀረ ሼቆን አስሮ ማድረግ
እንግዲህ መች ጣፍጦ የሚፋቀው ቆጮ
69. Kelloona huphichoona giddiyo ikkoone
Kuxxi sheqqoon shuunoom battiyaachemmone
ኬሎና ሁጲችን ማቅረቡ አንድ ነው
ቆርጦ ሽቆን መስራትም የማይረሳ ነው
70. Taabbi wane doyiit qoce tahee mooyoon

Tawoo tahaa kechet ooge shanaafilloon
ካባቱ ዘንድ ተምሬያለሁ የባህል ልብስን ነገር
እኔም ለብሼ ወጥቻለሁ ትልቅ ሸናፊሎን

71. Bushee aafoon ciino sharaatiite taana
Buroon kittooch cucha gandoon bekkiitina
የልጅቱን አይን ማየት ናፍቆኛል እኔን
ቡሮን ከኪቶ አስራ ቂጧን ያሳየችውን

72. Qocon bi inde waan gaawucha doyaane
Qoredoon duubiya godooch kechahane
ባህልን ከናቷ በደንብ ያልተማረች
ልብሷን አስተካክላ ሳትለብስ ገበያ ትወጣለች

73. Maache mulleechine yokkoo aalloon beetachan
Maaxocho kexoocho aroon tahiyaaho shuunoon shuuniyaachan
ሴት ልባም ናት ዮኮ አልባ አትኖርም
በውጭም በቤትም እሱን ሳትለብስ ስራ አትሰራም

74. Wo’ee gaxooch beeto goferina gaawe
Worganoona yechi amoo emirikkihe
ሙሽራዋ ጎን ያለው በጎፈር ተውቦ
በአግራሞት አስይዞ እንዴት ያስደስታል

75. Konina tuneba asho kaareegaata
Kote gaata geeno tanafaanafoona
Kaarem taane getti qajjeemmo aalloone
ከምንም ጋር ቢሆን ሰው ከተጣላ
ሽማግሌ ከተቀመጠ በተነፋነፍ
እጣላለሁ ብሎ የሚተው አይኖርም

76. Axxaamitto beete ta genneechi kishooch
Aacheechone wotta phaqqi bi bekkeemooch
አጣሚቶ አለ ከእመቤቴ እጅ
የወርቅ ነው ደግሞ ደምቆ እንዲታይ

77. Shashoon geddeet maacheen ciinaano konine
Showee toommooch beeti gaannoo taheti toone
ሸሾን ያደረገች ሴት ማይመለከት ማነው
በሀገር ያለውን ሀብት የለበሰች አይደለችም ወይ

78. Ella geenet taane gammanoo amoo halleehe
Eenona tuneemmon daaddoon taach imbote
እንግዲህ አርጅቻለሁ ገመኖ ለእኔ ምን ያደርግልኛል
ከእድሜ ጋር ሚሆነውን ዳዶን ለእኔ ስጡኝ

79. Ne gooshoon ged eke keyi hambon gaarooch
Ne daqqo bekkeba keya ashi daggooch
ጎሾሽን አርጊና እስኪ ውጭ እንሂድ ከሰርግ
ደረጃሽ ይታይ ይውጣ ከሰው መሀል

80. No doonochi mecheenoch qettooch beeti tifoo
Naachoono nuuchoono battii kaqqii beeto
ከጌታችን ሚስት አንገት ያለው ቲፎ
አማትም ጓደኛም አስረስቶ የሚያስደነግጥ ነው

81. Waamoocha guttichoon gedaan aabi maache
Woraafoona guudoon qaawi daniyaache
Wotta ebin mucceti kafecho beeto aabichiye
በጆሮዋ ጉቲቾን የማታደርግ የቷ ሴት ናት
በወረዳ ዙሪያ ቢፈልጉ አይገኝ
ደግሞ ይህን ያጣ ካፋ ያለው የት ነው

82. Geppoon kuchebote bushiishena'ote
Biiyeto qitite no aafooche aallete
ጌፖን ተቆረጡ ልጆቻችን ሆይ
የታመመው ሞቷል ጠፍቷል ከፊታችን

83. Guudoona beet asho bulla ayiniba
Borono kuchere eefoocha koteba
በዙሪያ ያለ ሰው ሁሉም ይዘን
ቦሮንም ተቆርጦ ለቅሶ ይቀመጥ

84. Goosho geduwani alluboo geduwani
Gaarooch hammaabeeti gaawa keyuwani
ጎሾ ታድርግ እንጂ አሉቦ ታርግ እንጂ
ሰርግ የምትሄደው ቆንጆታ ትውጣንጂ

85. Wandero gedda'a baarooch kechetane
Qocechi no manee amoo gaawetane
ዎንደሮ አርጋ (ለብሳ) ለበዓል ወጥታለች
ቆጨቺ የኛ እህት ምን ያህል አምራለች

86. Budoo axxaamitoon geddeemmo taan daambe
Budoochi attoone birewoon ukkibe
የነሀስ ቀለበት የሚያጠልቅ ይውሰደኝ
የቡዳ መድሀኒት ብርም ያፍስስልኝ

87. Woraafa no bushee wodoo neech tunebe
Wo'ee Neechomine ubba tunet shashee
ማን ብሎሽ የኛ ልጅ መዳን ይሁን ላንች

ሙሽራ እንዳንች ነው ሙሉ ጌጥ የሆነች

88. Andire qoreddoo amo halleehe taacha
    Abbichon taach deebot deejjiish bo qoolloocha
    አዲስ ልብስ ለኔ ምን ያደርግልኛል
    ያባቴን አምጡልኝ ላምላካቸው ሰዉና
89. Oggon qellooch geddit no kafechi bushoo
    Oogeton doyite qocoon bekkiibeeto
    ኦጎን ከራሱ ያረገው ይህ የካፋ ልጅ
    እጅጉን ተምሯል ባህልን ሚያሳየው
90. Dubboon macho woderii
    Dubbiyoono yechi
    Aroo goyee goyoch
    Aree qoccee qucoch
    ዱቦን ሴቱ ገምዶ
    ሀገሩንም (ወረዳውን) ይዞ
    እርሱ ወደ እርሻ ማረስ
    እርሷም ወደ ቆጮ መፋቅ
91. Shooween aachoo geddi yeeri immi'i noocha
    Shuuneetone alluboon giyeemmo baatoocha
    መሬቱን (ሀገሩን) ወርቅ አርጎ እግዜር ሰጥቶን ለኛ
    ሰርተናል አሉቦን ሚገባ ከእግራችን
92. Ta doonocho wobit hach xaa'oo beete
    Taatoommo taheree showooch kotaayite
    የኔ ጌታ ይምጡ ከዚህ ቦታ አለ
    እንደ ንጉስ ለብሰው መሬት አይቀመጡ
93. Tifoon qettooch geddaa ebi bekkabeeti
    Taachi bi tuneega amoo gaawabeeti
    ቲፎን ካንገቷ አርጋ ይህች ምትታየው
    የኔ ብትሆን እንዴት መልካም ነበረች
94. Bo qettoochi tifoo wohooche bekkehe
    Bo kishooch phaqqahan aachee axxaamitte
    ያንገታቸው ቲፎ ከሩቁ ይታያል
    ከጃቸው ታበራለች የወርቅ አጣሚቶ
95. Gooshee gumbon yechi
    Gooqqe jinnaaro yechi
    Kechiye kafecho
    Kelloon quyemnocho

ጎሾ ጉምቦን ይዞ
የቆዳ ጃናሮ ይዞ
ይወጣል ካፈኞ
በራፍ ሚጠብቀው

96. Dubboon bi toommoocha oggoon bi qelloocha
Daado dafooch hamba kotaaya kexoocha
ዱቦን ከላዩ ላይ ኦጎን ከራሱ ላይ
ለደቦ ለዳዶ ይሒድ አይቀመጥ ከቤት

97. Eke wob ta bushee
Ebin ciini dice
Sheqqoo cuchemona
Shaawujja qucceemona
እስኪ ነይ የኔ ልጅ
ይህን አይተሽ እደጊ
ሽቆ ሲታሰር
አጣፍጦ ሲፋቅ (ቆሎ)

98. Shuddille demmooch gijjoon shashetine
Shugime qeenoochaa kayo gaawetine
በቀጭን ወገብ ላይ ጊጆ ያሰርሺቱ
በትልቅ አልጋ ላይ ጨዋታ አዋቂተ

## አባሪ 4. ፎቶግራፎች



የሸመና ባለሙያ የሆኑት አቶ ታደሰ ጊያ



የካፋ ዞን ባህል ቱሪዝምና ኮሚዩኒኬሽን ሀላፊ አቶ አስራት ሀይሌ



ወ/ሮ አለሚቱ አያናን ቃለመጠይቅ ሳደርግላቸው



ለአቶ አሰፋ አለማየሁ ቃለመጠይቅ ሳደርግላቸው



ለሻውጀራሻ አሸብር ሀይሌ ቃለመጠይቅ ሳደርግላቸው



ለአቶ አሰፋ ወ/ማሪያም ቃለመጠይቅ ሳደርግላቸው



ለወ/ሮ አቦነሽ አትርሴ ቃለመጠይቅ ሳደርግላቸው



ለአቶ ወርቁ ወ/ማሪያም ቃለመጠይቅ ሳደርግላቸው



ለአቶ ወርቁ አለሙ ቃለመጠይቅ ሳደርግላቸው



ለአቶ በየነ በቀለ ቃለመጠይቅ ሳደርግላቸው



ጉዞ ወደ ካፋ ዞን



አቶ አሰፋ አለማየሁ ካፊ ቆጪ ኮቶ ለብሰው ያነሳኋቸው ፎቶግራፍ

ይህ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት የኔ ወጥ ስራ ሲሆን ከዚህ በፊት በሌላ ሰው ተሰርቶ አልቀረበም፡፡ ለጥናቱ በምንጭነት የተጠቀምኩባቸውን መረጃዎችም በሙሉ በተገቢው መንገድ መጥቀሴን አረጋግጣለሁ፡፡

ስም አዜብ ወርቅነህ ፀጋ

ፊርማ ____________________

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት

ግንቦት፣ 2006 ዓ.ም